# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 304 ሐምሌ 4 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# ወጣቶች የኢትዮጵያ አንድነትና አብሮነት እንዲጠናከር ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው ተገለጸ



አቶ ብናልፍ አንዷለም

አዲስ አበባ፡- «አገር ተረካቢ ወጣቶች የኢትዮጵያ አንድነት፣ አብሮነት እና መተባበር እንዲጠናከር ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው» ሲሉ የሰላም ሚኒስትር ብናልፍ አንዷለም ገለጹ።

የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዷለም የአራተኛው ዙር የብሔራዊ በጎ ፈቃድ የማኅበረሰብ ልማት አገልግሎት ስልጠና በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሲጀመር እንደገለጹት፤ የስልጠናው ዓላማ ኢትዮጵያ የጀመረችውን የአገር ግንባታ ሥራ ማሳለጥና ከግብ እንዲደርስ ማድረግ ነው። ወጣቶች አብሮ ለመሥራት፣ ያላቸውን ዕውቀት እና ልምድ ለመለዋወጥ እንዲሁም ሕዝባቸውን በቅንነት ለማገልገል ይረዳል።

የነገ አገር ተረካቢ ወጣቶች የኢትዮጵያ አንድነት፣ አብሮነት እና መተባበር እንዲጠናከር የበኩላቸውን መወጣት እንዳለባቸው አመልክተዋል።

በአራተኛው ዙር የብሔራዊ በጎ ፈቃድ የማኅበረሰብ ልማት አገልግሎት ሦስት ሺህ ወጣቶች ለአንድ ወራት በጅማ ዩኒቨርሲቲ ስልጠና ይወስዳሉ።

በተመሳሳይ በጎ ፈቃድ የማኅበረሰብ ልማት አገልግሎት ስልጠና በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ መስጠት ተጀምሯል።

ወጣቶች የኢትዮጵያ አንድነትና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ እንግዳው ጠገናው

# በክልሉ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን የተካሄደው የሕግ ማስከበር ዘመቻ አመርቂ ውጤት ማስገኘቱ ተገለጸ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ከ6ነጥብ2 ሚሊዮን በላይ ዜጎች በመድረክ ላይ በቀጥታ ላቀረቡት «የሕግ ይከበር ጥያቄ» ምላሽ የሚያስገኝ አመርቂ ውጤት መመዝገቡን የክልሉ ፀጥታ ቢሮ ገለጸ።

የአማራ ክልል ሠላምና ፀጥታ ቢሮ ሕዝብ ግንኙነት

በክልሉ ዘላቂ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ከውጭ አገር የትምህርት ዕድሎች አገር የምትጠቀምበት አሠራር መዘርጋት እንደሚገባ ተጠቆመ

ፍቃዱ ዴሬሳ

አዲስ አበባ፡- በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ በማዕረግ ተመርቀው የውጭ አገር የትምህርት ዕድል የሚያገኙ ተማሪዎች ተመልሰው አገራቸውን የሚጠቅሙበት አሠራር መዘርጋት እንዳለበት ተጠቆመ።

በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ በቅርስ ጥናት ትምህርት ክፍል በመምህርነት ሲያገለግሉ የቆዩት ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በከሪ ጉዳዩን በማስመልከት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ያስመዘገቡት ውጤት የላቀ መሆን በችሎታቸውና በጥረታቸው በመሆኑ ዕድሉን ማግኘታቸው መደገፍ ያለበት ጉዳይ ነው።

ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ አሠራር ተማሪዎቹን የሚጠቅም ቢሆንም በአገር ደረጃ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊ አገራትን የሚጎዳ፣ በጣም ያደጉ አገራት የሚባሉትን ደግሞ የበለጠ የሚጠቅም ስልት እንደሆነ መታዘባቸውን አስታውቀዋል።

እንደ ዶክተር አየለ ገለጻ፤ በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በከፍተኛ ማዕረግ የሚመረቁ ተማሪዎች የግል ጥረታቸውንና ታታሪነታቸውን የሚያሳይ በመሆኑ እስኮላርሺፕ አግኝተው መሄዳቸውና ተገቢውን እውቀት መቅሰማቸው ተገቢ ነው።

በመሆኑም ተማሪዎቹ የውጭ የትምህርት ዕድል አግኝተው በሚሄዱበት ወቅት መንግሥት ጉዳዩን በሚመለከት ፖሊሲ በማውጣት ተማሪዎቹ አስፈላጊውን ውል ፈፅመው እንዲሄዱ ማድረግ እንደሚጠበቅበት ተናግረዋል። በዚህ ረገድ የሚወጡ ፖሊሲዎች ተማሪዎቹን የሚጎዱ አለመሆናቸውን በተገቢው በማጤን ወደ ውጭ ሄደው የላቀ እውቀት የሚቀስሙበትን ሂደት መከተል

ከውጭ አገር የትምህርት ዕድሎች... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በከሪ



## «ዘላቂ ሰላም ለማስፈን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ማስወገድ ያስፈልጋል»

- አቶ ከበደ ቀጀላ
የአፍሪካዊ ሙከራ ለዲሞክራሲያዊ የዓለም ሥርዓት (አሙዲአስ) ሥራ አስፈፃሚ

ገጽ 4






## እውቀታችንን ለነውጥ ሳይሆን ለለውጥ እንጠቀም

ገጽ 7

## «እነሱ እየተቹ እኛ እየሰራን ፍሬ ስናመጣ የነሱ ልጆች ለኛ ዘብ ይቆማሉ»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ


ገጽ 10


ዶክተር አናንያ ሰለሞን


ወይዘሮ ሃይማኖት ካሣ


ፎቶ፡- ሃዲስ አብርሃ

ወይዘሮ ማስተዋል ይላቸው


ወይዘሮ ዘሃራ ሱሌማን

# በሳቀ አገልግሎት ለልህቀት ማዕከልነት እየተጋ የሚገኘው ተቋም

**ፋንታነሽ ክንዴ**

‹‹የብዙዎች እናት›› የሚል ቅጽል ስም ያተረፉ መልካም እናትን ስም አንግቦ ለእናቶችና ለእምቦቃቅላ ልጆቻቸው አገልግሎት ከሚተጋ ተቋም ውስጥ ተገኝተናል። በየካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ስር በሚገኘው አበበች ጎበና የእናቶችና ሕፃናት ሆስፒታል ቅጥረ ግቢ ውስጥ።

የሆስፒታሉ ቅጥረ ግቢ ውበትና ንጽህና የመረጋጋት ስሜትን ስለሚፈጥር ያለነው መዝናኛ ቦታ እንጂ ሕክምና ተቋም ውስጥ መሆኑን ያስረሳል።

በቦታው የመገኘታችን ዓላማ ሆስፒታሉ የሚሰጠው አጠቃላይ አገልግሎት ምን ይመስላል የሚለውን ለመቃኘት ነበር። በሆስፒታሉ ውጫዊ ውበት እየተደመምን አገልግሎት አሰጣጡስ ያነገበውን እናት ስምና ውጫዊ ውበቱን የሚመጥን ይሆን የሚል ጥያቄ በአዕምሯችን ማጫሩ አልቀረም።

ለአእምሯችን ጥያቄ መልስ ለማግኘት በሆስፒታሉ ከተመደበልን ባለሙያ ጋር በመሆን አገልግሎት መስጫ ቦታዎችን ተዘዋውረን ጎበኘን።

በየደረስንበት የታመሙትን ፈጣሪ ይማራችሁ፣ ወደ ማዋለጃ ክፍል ለመግባት የሚጠብቁትን ‹‹ማርያም ትቅረባችሁ››፣ ፈጣሪ ከእናንተ ጋር ይሁን እያልን ጉብኝታችንን ቀጥለናል። በምጥና በቀዶ ጥገና ልጆቻቸውን የተገላገሉ እናቶች ማረፊያ ስንደርስም ‹‹እንኳን ማርያም ማረችሽ››፣ ‹‹እንኳን አላህ በሰላም ገላገለሽ›› የሚሉና ሌሎችንም መልካም ምኞቶቻችንን እየገለጽን የሆስፒታሉን እንቅስቃሴ እያየን ነው።

ከመልካም ምኞታችን ጎን ለጎንም አገልግሎት አሰጣጡን እንዴት እንዳገኙት አወራናቸውና የተወሰኑትን ሀሳብ በመቅረጸ ድምጻችን አስቀረን።

ወይዘሮ ሃይማኖት ካሣ በእርግዝና ወቅት የስኳር አለመስተካከል ገጥሟቸው ከአንድ ወር በላይ በአበበች ጎበና የእናቶችና ሕፃናት ሆስፒታል ቆይተዋል። የሆስፒታሉ አገልግሎት አሰጣጥ በጣም እንዳስደሰታቸውና ሕመማቸውንም እንዲረሱት እንዳደረጋቸው ይገልጻሉ።

በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ አንድ አልጋ ብቻ በመኖሩና የሻወርና ሌሎችም አገልግሎቶች የተሟሉለት በመሆኑ ቤትን ያስረሳል የሚሉት ወይዘሮዋ፤ በየደረጃው ያሉት ባለሙያዎች የሚያደርጉላቸው የሕክምና ክትትል፣ የሚሰጧቸው ፍቅርና የሚያሳይዋቸው አክብሮት አስደምሟቸዋል።

እርግዝና ውጤቱ አስደሳች ቢሆንም ሂደቱ አዳጋች ነው የሚሉት ወይዘሮ ሃይማኖት፤ መሰል አገልግሎቶች የእናቶችን ሸክም የሚያቀሉ በመሆናቸው ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል። እስካሁን በሆስፒታሉ ለተሰጣቸው መልካም አገልግሎትም ምስጋና አቅርበዋል።

ሌላኛዋ ተገልጋይ ወይዘሮ ማስተዋል ይላቸውን ያገኘናቸው ከመኝታ ክፍላቸው ወጥተው በኮሪደር ላይ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ነበር። ከአንድ ቀን በፊት በቀዶ ጥገና ወንድ ልጅ መገላገላቸውን የሚናገሩት ወይዘሮዋ፤ የሆስፒታሉ አገልግሎት አሰጣጥ ከአቀባበል ጀምሮ አስደስቷቸዋል።

ከዚህ ቀደም በሌላ ሆስፒታል የመጀመሪያ ልጃቸውን መገላገላቸውን የሚያስታውሱት ወይዘሮዋ፤ በአበበች ጎበና ሆስፒታል ያዩት አጠቃላይ አገልግሎት አሰጣጥ ላቅ ያለ ነው።

ሆስፒታሉ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ የባለሙያዎች እገዛና እንክብካቤ ያልተለያቸው ሲሆን፣ የመውለጃና የማረፊያ ክፍሎችም ለእናቶች ምቹ ናቸው። ቢስተካከል የሚሉት ነገር እንደሌለ ቢገልጹም፤ ያለውን መልካም አገልግሎት አጠናክረው እንዲቀጥሉ አደራ ማለታቸው ግን አልቀረም።

መንታ ልጆችን ተገላግለው ያገኘናቸው ወይዘሮ ዘሀራ ሱሌማን ደግሞ ወደ ሆስፒታሉ የመጡት ከአንድ ሳምንት በፊት መሆኑን ይናገራሉ።

ልጆቻቸው ያለ ቀናቸው ስለተወለዱ በሆስፒታሉ ክትትል እየተደረገላቸው ነው የሚሉት የመንቶቹ እናት፤ ክትትል ያደርጉበት ከነበረው የጤና ተቋም ወደዚህ ሆስፒታል ‹‹ሪፈር›› ተብለው ከመጡ በኋላ ያገኙት አገልግሎት አሰጣጥ ከጠበቁት በላይ መሆኑን ይገልጻሉ።

የወይዘሮ ዘሀራ መንታ ልጆች ማሞቂያ ክፍል ገብተው አስፈላጊው ክትትል እየተደረገላቸው ሲሆን፣ እናት ዘሀራም በቀዶ ጥገና ስለወለዱ አልጋ ይዘው ከቁስላቸው እያገገሙ ይገኛሉ።

ይሁን እንጂ እናት ያረፉበት ክፍልና ልጆቹ ሕክምና የሚከታተሉበት ክፍል መራራቅ ፈተና እንደሆነባቸው አልደበቁም። በመሆኑም እናቶች ልጆቻቸውን እያጠቡ አብረው ሕክምናቸውን ሊከታተሉ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ቢቻል መልካም መሆኑን ጠቁመዋል።

የአበበች ጎበና የእናቶችና ሕፃናት ሆስፒታል ዳይሬክተር ዶክተር አናንያ ሰለሞን በበኩላቸው፤ ሆስፒታሉ ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ለእናቶችና ሕፃናት አስፈላጊውን ሕክምና አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥም አስራ ሁለት ሺ ለሚሆኑ እናቶች የማዋለድ አገልግሎት መስጠቱን ይገልጻሉ።

ሆስፒታሉ ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠትን መርሁ አድርጎ እየሠራ ነው የሚሉት ኃላፊው፤ በሆስፒታሉ የሚሰጠውን የአገልግሎት ጥራት የሚከታተል የጥራት ቡድን መቋቋሙንና በየዕለቱ ዳሰሳ በመሥራት ለሚስተዋሉ ችግሮች መፍትሔ ይቀመጣል። በየሦስትም ወሩም የደንበኞች አጠቃላይ የአገልግሎት እርካታ ምን ይመስላል የሚለው የሚለካበት የዳሰሳ ጥናት እንደሚከናወንም ይጠቁማሉ።

ሆስፒታሉ በእናቶችና ሕፃናት ሕክምና የልህቀት ማዕከልና በዘርፉ ከፍተኛ የምርምር ተቋም እንዲሆን ታስቦ የተከፈተ ነው የሚሉት ዶክተር አናንያ፤ እስካሁን ድረስ የቅድመ ምረቃ ሕክምና ተማሪዎችንና የሕክምና ስፔሻሊቲ ተማሪዎችን እያስተማረ ሲሆን በቀጣይነት የተለያዩ የሰብ ስፔሻሊቲ የትምህርት ክፍሎችን ይጀምራል።

አበበች ጎበና የእናቶችና ሕፃናት ሆስፒታል ወረቀት አልባ አገልግሎት መስጠቱ ከሌሎች ሆስፒታሎች እንደሚለየው የሚጠቅሱት ዶክተር አናንያ፤ ይህም በየዕለቱ የተሠሩ ሥራዎችን በቀላሉ ለመከታተልና ተጠያቂነትን ማስፈን አስችሏል። በዚህም ኢትዮጵያ የእናቶችን ሞት ለመቀነስ የያዘችውን ግብ ለማሳካት የበኩሉን በጎ ተጽዕኖ ለማሳረፍ በትኩረት እየሠራ ነው ይላሉ።

እናቶች ከወለዱ በኋላ ጽኑ ሕመም ቢያጋጥማቸው ክትትል ማድረግ የሚያስችል የጽኑ ሕሙማን ክፍል መኖሩን ጠቅሰው፤ ክፍሉ የመተንፈሻ መሣሪያን ጨምሮ በሌሎች አስፈላጊ ዘመናዊ መሣሪያዎችና ብቁ ባለሙያዎች የተደራጀ ስለመሆኑ አብራርተውልናል።

# መንግሥት ያስቀመጠውን የሰላም አማራጭ ሁሉም ወገኖች ተግባራዊ በማድረግ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና ልማትን ማረጋገጥ ይገባል

<u>አዲስ አበባ</u>፡- መንግሥት ያስቀመጠውን የሰላም አማራጭ ሁሉም ወገኖች ተግባራዊ በማድረግ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና ልማትን ማረጋገጥ እንደሚገባ የቀድሞ የኢትዮጵያ መሪዎች ገለጹ።

መንግሥት በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ያለውን ችግር በሰላም አማራጭ ለመፍታት መወሰኑን መግለጹ የሚታወስ ሲሆን፤ ይህንን ሥራ በዋናነት የሚያከናውንና ሰባት አባላትን የያዘ ቡድንም አቋቁሟል።

የሰላም ሂደቱም ሕገ-መንግሥታዊ መርሆን ያከበረ፣ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለድርድር የማያቀርብና ሂደቱም በአፍሪካ ኅብረት አስተባባሪነት የሚመራ እንዲሆን አቋም መያዙን የፍትሕ ሚኒስትሩ ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቲዮስ መግለጻቸው ይታወቃል።

በመንግሥት ውሳኔ ዙሪያ ኢዜአ ያነጋገራቸው የቀድሞ የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሙላቱ ተሾመና የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ኢትዮጵያ ከራሷ ባለፈ የቀጣናው የሰላምና ደህንነት ጠበቃ መሆኗን አስታውሰዋል።

ዶክተር ሙላቱ ኢትዮጵያ የአፍሪካ አገራትና ጎረቤቶቿም ከግጭት ይልቅ ሰላም እንደሚበጃቸው አቋሟን በማራመድ እንደምትታወቅ ጠቅሰው፤ ከዚህ አኳያ አሁን ያጋጠማትን ችግር በመፍታት ወደሰላም



ዶክተር ሙላቱ ተሾመ

እንድትመለስ ማድረግ የግድ ነው ይላሉ።

ለዚህም መንግሥት የሰላም አማራጭ ውሳኔውን ማሳለፉን አድንቀው፤ ለኢትዮጵያ ሰላም ከኢትዮጵያውያን ውጪ ማንም ነጋሪ እንደማያስፈልግ ነው ያነሱት።

የቀድሞ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ በበኩላቸው፤ መንግሥት



አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ

የተከተለው የሰላም ውሳኔ ለኢትዮጵያ አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን ተናግረዋል።

ጦርነት ኢትዮጵያን ብዙ ዋጋ እንዳስከፈላት የተናገሩት አቶ ኃይለማርያም፤ በጦርነት የሚሳተፍ የትኛውም አካል ከጦርነት ማትረፍ እንደማይችል አብራርተዋል።

ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ ጦርነትና ግጭት ሊቆም እንደሚገባና ችግሮችን በሰላም መፍታት አስፈላጊ መሆኑን አንስተዋል።

ሰላምን በማስፈንም ኅብረተሰቡን ከስጋትና ከጭንቀት ኑሮ እንዲሁም አገሪቱን ከተጨማሪ ጉዳት ማላቀቅ እንደሚገባም እንዲሁ።

የቀድሞ መሪዎቹ አክለውም፤ የቀጣናው አገራት፣ አፍሪካና ዓለም ኢትዮጵያ ለሰላምና ደህንነት ትልቅ ሚና እንደምታበረክት ያውቃሉ፤ ለዚህም ከእኛ ብዙ ነገር ይጠብቃሉ ነው ያሉት።

ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ አቅም ለመጠቀም ያሉ ውስጣዊ ችግሮችን በውይይት በመፍታት ሰላሟን ማረጋገጥ ለነገ የሚተው ሥራ እንዳልሆነም ተናግረዋል።

በዚህም ኢትዮጵያ ከራሷ ባለፈ ለቀጣናው፣ ለአፍሪካና ለዓለም ሰላምና ደህንነት ያላትን ሚና ማስቀጠል እንደሚገባ በመጥቀስ።

በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ያለውን ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የአገሪቱ ክፍል ያሉ ግጭቶችን በዘላቂነት ለማስቆም ጠብመንጃን ወደ ጎን ትቶ በውይይት መፍታት እንደሚገባም ጠቅሰዋል።

በዚህም በኢትዮጵያ አስተማማኝ ሰላም ለመትከል ከሁሉም ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ሚና እንደሚጠበቅም መናገራቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# በዕድሜ ትንሿ ባለ ትልቅ ልብ- ሲፈን

በዚህች መከራና ግፍ በሚስተዋልባት ምድር፤ ሰዎች ክፋትን እንደ ክብር ቆጥረው በሚኖሩባት ዓለም ላይ መኖር የማይሰለቸው ቅን ልቦናን በታደሉ ሰዎች ምክንያት ነው። ብዙዎች ሮጠው ባልጠገቧት ዓለም ላይ የሚያኖራቸው የደግነት ዓለም ከብዙ መከራ ሰውሮ የሚያቆያቸውም የመልካሞች ተስፋ የራሳቸውም መልካም የመሆን ዋሻ ነው።

በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ የምትታወቅ አንድ የክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤል «ፅድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም» የምትል ስንኝ አለች። ይህቺ ስንኝ ምናልባት ልንል የምንፈልገውን ብዙ ቃላት በአንድ ስንኝ የመግለፅን ጥበብ ታሳይልናለች። እውነት ነው ሃይማኖተኛ ሰው ተስፋ የሚያደርገው የሰማዩ የፅድቅና ኩነኔ ታሪክ ኖረም አልኖረም ከክፋት ደግነት በብዙ እጥፍ ይሻላል።

አንዳንድ ሰዎች አሉ ለመስጠት ተሰጥተው በመልካምነት ኖረው ከጥሩ ሽቶ በበለጠ የሚያውደውን መልካም ስማቸው ሲጠራ ለብዙዎች ፈገግ ማለት ምክንያት መሆን የሚችሉ፤ አንዳንዶች አሉ እነሱ እንደ ሻማ እየቀለጡ ለሌላው እንጀራ ማብሰያ ማገዶ የሚሆኑ፤ አንዳንዶች አሉ ስለሚያደርጉት መልካምነት ምላሽና ሽልማት ሳይሹ በየትኛውም ስፍራ መልካም መሆንን የተሰጡ፤ ምስጋና ለእነዚያ ሰዎች።

ይሄው ቅንነት በማህበራዊ ሚዲያው ብቻ የሚያውቋቸውን ሰዎች እንኳን ባይኔ ካላየሁ ሳይሉ ሰዎችን በመደገፍ የሚዝናኑ፤ ብቸኛ ሱሳቸው ሰውን መርዳት የሆነ ከሰውም ሰው የሆኑ እልፍ አእላፍ ሰዎች አሉ። ምስጋና ሰው በሌለበት ሰው ፈላጊ በበዛበት ዘመን ሰው መሆን ለቻሉ ደጎች።

ሰውን መርዳት በብዙ የዓለም አገራት የሚኖሩ በብዙ ቢሊዮኖች ዘንድ የሚደነቁ ሰዎች መለያ ነው። ትናንታቸውን እንደ መሰላል ሆነው ለዛሬ ድልድይ ሆነው ያሻገሯቸውን ሰዎች ማግኘት ባይችሉ እንኳን እነሱም ሌሎች መኖር ምክንያት ለመሆን ብዙዎች ሌሎችን በማኖር ሕይወት ውስጥ ሲመላለሱ ማስተዋል የተለመደ ነገር ነው።

ኢትዮጵያም የነ አበበች ጎበና የነዘሚ የኑስ የነቢኒንያም በለጠ(መቄዶኒያ) አገር ናት። ብዙ በጎ አሳቢ ከራሳቸው አብልጠው ለሌሎች በመኖር ሕይወታቸውን የገፉ ሰዎች ያሉና የሚኖሩባት የደጎች መኖሪያ ናት። አሁን አሁን ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ደግሞ መልካምነት በመንግሥት ደረጃ ታምኖበት የተለያዩ የበጎ አድራጎት ተግባራት መከወን መጀመራቸው ይታወቃል።



የዛሬው የቅን ልቦና ባለቤት እንግዳችን ሲፈን ካሳሁን ትሰኛለች። በዚህች ምድር ላይ አስራ ስድስት አመታትን ኖራለች። ካየችው ትናንት የሚበልጥ ነገን በተስፋ የምትጠባበቅ፤ ትንሽ ናት። ልክ እንደ ፅጌሬዳ አበባ ሁሉም አይኑን የሚጥልባት። ውብ ናት በውብ ፈገግታዋ አኩራፊን የምታስቅ ቅን። እናትና አባቷ የሺ ኢብራሂም እና ካሳሁን እሸቱ ይባላሉ፤ ሁለት እህትና ወንድም ያላት ሲፈን አምስት ልጆች ላሉት ቤተሰቧ አምስተኛና የመጨረሻ ልጅ ነች።

ሲፈን መድኃኒዓለም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ናት። የስምንተኛ መልቀቂያ ፈተናን ባጠናቀቅነው ሳምንት የወሰደችው ሲፈን ፈተና ሂደቱ ሰላማዊና ምቹ እንደነበር ገልፃ፤ ወደፊት ተምራ ሕግ ትምህርትን የመከታተል ሀሳብ እንዳላት አውግታናለች።

ሲፈን የፓርላማ ተሳታፊ እንዲሁም የጉለሌ ክፍለከተማ የሕፃናት ፓርላማ አፈጉባኤ በመሆን የሩቅ ጉዞዋን በቅርብ ስኬት ጀምራዋለች።

ሲፈን ዕድሜ በፈቀደላት መጠን በተለያዩ የበጎ ፍቃድ እንቅስቃሴዎች ላይ ትሳተፋለች። በዕድሜዋ ልክ በጎ ብላ የምታስባቸውን መልካም ነገሮች በመከወን ነው ከትምህርት የተረፈ ጊዜዋን የምታሳልፈው።

በአሁኑም የክረምት በጎፍቃድ ላይ በአረንጓዴ አሻራ መርሀግብር ላይ ተሳታፊ የመሆን እንዲሁም ትልልቅ ድርጅቶችን በማናገር በግሏም ሆነ በጉለሌ ክፍለከተማ ስር በመሆን አስር ወላጅ አልባ ሕፃናትን በመሰብሰብ የመርዳት እቅድ ይዛለች።

ሰዎችን በመርዳት ውስጥ ትልቅ ደስታ አለ ትላለች። ገንዘብ ጊዜና ቦታ ተመቻችቶላቸው ሰዎችን ለማይረዱ ሰዎች ሰዎችን ባለመርዳታችሁ የመርዳትን ደስታ አትጡ ስትል መልዕክቷን አስተላልፋች። ሁሉም ሰው ራሱንና የሚወዳቸውን ሰዎች በተቸገሩ ሰዎች ቦታ አስቀምጦ በማየት ማንኛውም ሰው የተቸገረን በመደገፍ ሰውን መርዳት ውስጥ ያለውን ደስታ ሊያይ እንደሚገባውም ገልፃለች።

ሲፈን ለጎዳና ተዳዳሪ ልጆች እርስ በእርሳቸው እንጂ ከሌላው የማህበረሰብ አካል ፍቅር እንደተነፈጋቸው ታስባለች፤ ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ቀጥታ ብንሰጣቸው እንዲሁም የጎዳና ልጆች በአግባቡ ከተያዙና ከወደቁበት ጎዳና እንዲነሱ ከተደገፉ ለአገርና ወገናቸው ጠቃሚ ዜጎችን ማፍራት እንደሚቻል ትናገራለች።

በተለያዩ ስፍራዎች በጦርነት ምክንያት ለተፈናቀሉ ሰዎች መንግሥት የሚሰጣቸውን የአንድ ቀን ምግባቸውን ለመስጠት የመድኃኒዓለም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጥያቄ አቅርበው እናንተ ከተስማማችሁ ምንም ችግር የለውም ብሎ ጥያቄያቸውን በመቀበል ተማሪው ተስማምቶ ወስኖ እንዲመጣ ዕድል እንደተሰጣቸውም ነግራናለች።



ወይዘሮ ቅድስት ስጦታው

# በኅብረት ሥራ ማኅበራት የሕግ ክፍተቶች መኖራቸው ተገለጸ

ሙሳ ሙሐመድ

አዲስ አበባ፡- በኅብረት ሥራ ማኅበራት ውስጥ የሕግ ክፍተቶች መኖራቸውን የአዲስ አበባ ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ አስታወቀ። ክፍተቶቹን ከፍትህ አካላትና ከምድብ ችሎት ዳኞች ጋር በመሆን ለመቅረፍ እየተሠራ መሆኑም ተገልጿል።

የኤጀንሲው ምክትል ዋና ዳይሬክተርና የሬጉላቶሪ፣ የሕግ፣ ኢንስፔክሽንና ኦዲት ዘርፍ አስተባባሪ ወይዘሮ ቅድስት ስጦታው እንደገለጹት፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሉት የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚስተዋሉትን የሕግ ክፍተቶች ከፍትህ አካላት ጋር በመሆን ለመቅረፍ እየተሠራ ነው።

በከተማዋ ስር ከዘጠኝ ሺህ 320 በላይ የኅብረት ሥራ ማኅበራት መኖራቸውን የጠቀሱት ወይዘሮ ቅድስት፣ ማኅበራቱ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በሀብትና ንብረት አስተዳደር፣ በመልካም አስተዳደር ረገድ በማኅበረሰቡ ዘንድ ቅሬታዎች እየቀረቡባቸው ነው። ችግሮቹንና ቅሬታዎችን ለመፍታትም በሕግ የተፈቀዱ መብቶችንና ግዴታዎች አተገባበር ላይ ያሉ ክፍተቶችን በየደረጃው ካሉ የምድብ ችሎት ዳኞች፣ አቃቢያን ዳኞች፣ የፖሊስ አካላት፣ ከምክር ቤቶች ጋር በቅርበት በመሥራትና በመወያየት በመለየትና በሕግ አግባብ የሚፈቱበትን አሠራር ለመዘርጋት ስለሚያስፈልግ ኤጀንሲው በዚህ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው ብለዋል።

በማኅበራቱ የሚስተዋሉ በሕግ የተፈቀዱ መብቶችንና ግዴታዎች አለመከበርና በወቅቱ የሬጉላቶሬ ቁጥጥር አለመደረግ፣ ኢንስፔክሽንና ኦዲት ባለመሠራቱ በ2014 በጀት ዓመት ብቻ ከ22ሚሊዮን ብር በላይ ጉድለት እንደተገኘም ወይዘሮ ቅድስት ተናግረው ፣ ከተገኘው ጉድለት ውስጥም 33 በመቶ ብቻ ተመላሽ እንደሆነ አመላክተዋል።

በሕግ ክፍተቶቹ ሳቢያም ማኅበራቱ በወቅቱ ኦዲት እየተደረጉ አይደለም፣ አብዛኞቹ ማኅበራት ያሉባቸው ጉድለቶች በውል አይታወቁም።

ለዚህ የዳረጋቸውም በወቅቱ ኦዲት አለመደረጋቸውና በሕግ የተፈቀዱ መብቶችና ግዴታዎች አለመከበር እንደሆነ የጠቀሱት ወይዘሮ ቅድስት፣ ክፍተቶቹን ከፍትህ አካላት ጋር በመሆን መቋጫ እንዲኖራቸው ለማድረግ እየሠራን ነው ብለዋል።

የማኅበራቱ ሀብትና ንብረት በአግባቡ እንዲጠበቅ አጥፊዎችም እንዲታረሙ ከፍትህ አካላት ጋር ውይይቶችን በማድረግ በሕግ መድረክ መፈታት ያለባቸውን ችግሮችን ለይቶ ለመፍታት የፍትህ አካላትና የምድብ ችሎት ዳኞች ጋር የሚደረጉ ውይይቶች በቀጣይነት እንደሚደረጉም አመላክተዋል።

የማኅበራቱ አባላቱ መብቶቻቸውን እንዲያውቁ አድርጎ በመደገፍ ከማኅበራቱ ፍሬ ተጠቃሚና ተቆጣጣሪ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት ወይዘሮ ቅድስት፣ ማኅበራቱን በቀጣይነት መደገፍ ላይ ኤጀንሲው ይሠራል ብለዋል።

በ2014 በጀት ዓመትም በተሠሩ የኢንስፔክሽንና ኦዲት ሥራዎች ወደ 364 ሰዎች ተጠያቂ ማድረግ መቻሉን የተናገሩት ወይዘሮ ቅድስት፣ በቀጣይነትም ይህ ተግባር ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።


# «ያለንን ሀብት፣ ዕውቀት እና ክህሎት ለአገራችን ለመስጠት በጎ ፈቃደኝነት ያስፈልጋል»

- አቶ ታዬ ደንደአ

አዲስ አበባ፡- ያለንን ሀብት፣ ዕውቀት እና ክህሎት ለአገራችን ለመስጠት በጎ ፈቃደኝነት ያስፈልጋል ሲሉ የሰላም ሚኒስቴር የሰላም ግንባታ እና ብሔራዊ መግባባት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታዬ ደንደአ ገለጹ።

አራተኛው ዙር የብሔራዊ የበጎ ፈቃድ የማኅበረሰብ ልማት አገልግሎት በጎ ፈቃደኞች ሥልጠና ፕሮግራም በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የተጀመረ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ከ2 ሺህ 500 በላይ ሠልጣኞችን ተቀብሏል።

አቶ ታዬ ደንደአ ለበጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ባስተላለፉት የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት፣ የብሔራዊ የበጎ ፈቃድ የማኅበረሰብ አገልግሎት ፕሮግራም የሰላም ሚኒስቴር አንዱ ትልቅ ትኩረት መሆኑን ገልጸው፣ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች በሥልጠና እና በበጎ ሥራ ቆይታቸው ከኅብረተሰቡ ጋር በመቀራረብ ኢትዮጵያን በደንብ የሚያውቁበት እና የኢትዮጵያውያንን እውነተኛ ማንነት የሚረዱበት ፕሮግራም ነው ብለዋል።



አገራችን የሌላትን ለዜጎች ልትሰጥ አትችልም፤ ያለንን ሀብት፣ ዕውቀት እና ክህሎት ለአገራችን ለመስጠት በጎ ፈቃደኝነት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

በጎ ፈቃደኝነት የአዕምሮ መልካም ፈቃድ እና የልብ ቸርነት ይጠይቃል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ እናንተ የጀግኖች አባቶች ልጆች እና ታላቅ አገር ያላችሁ በመሆኑ በጠላት የሚሸረቡ እና ከፋፋይ አጀንዳዎችን ጠንቅቆ በመረዳት የመከላከል ሥራውን በግንባር ቀደምትነት ልትሠሩ ይገባል ሲሉም አስገንዝበዋል።

በጎ ፈቃደኝነት የአዕምሮ መልካም ፈቃድ እና የልብ ቸርነትን የሚጠይቅ መሆኑን የሰላም ሚኒስቴር የሰላም ግንባታ እና ብሔራዊ መግባባት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታዬ ደንደአ ማስታወቃቸውን ከሰላም ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

የዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሀብታሙ አበበ በበኩላቸው፣ ዩኒቨርሲቲው በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸው፣ ለአራት ተከታታይ ጊዜ የብሔራዊ የበጎ ፈቃድ የማኅበረሰብ አገልግሎት ፕሮግራም ሠልጣኞችን በመቀበል እያሰለጠነ ይገኛል ብለዋል።

ዜና

# «ዘላቂ ሰላም ለማስፈን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ማስወገድ ያስፈልጋል»

\- አቶ ከበደ ቀጀላ
የአፍሪካዊ ሙከራ ለዲሞክራሲያዊ የዓለም ሥርዓት (አሙዲአስ) ሥራ አስፈፃሚ

ዘላለም ግዛው



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት መፍታት እንደሚያስፈልግ የአፍሪካዊ ሙከራ ለዲሞክራሲያዊ የዓለም ሥርዓት (አሙዲአስ) የሲቪክ ማኅበር ሥራ አስፈፃሚ አቶ ከበደ ቀጀላ ገለጹ።

አቶ ከበደ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን በየደረጃው ያሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችና ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚመጡ አድሏዊ እና አግላይ አሠራሮች ሊወገዱ ይገባል። የአድሏዊ አሠራር መስፈን ለሙስና በር ይከፍታል፣ ይህ ደግሞ አድጎ ለግጭት መነሻ ይሆናል።

ግጭቶችን የሚፈታ፣ የሁሉንም ዜጋ መብት የሚጠብቅ፣ በሰው ልጅ ላይ የሚፈጸም ወንጀል እና በዘር ላይ የሚያነጣጥር ጥቃት እንዳይፈጸም የሚቆጣጠር እና የሚከላከል የዴሞክራሲ ሥርዓት መገንባት እንደሚገባም አመልክተዋል።

የዴሞክራሲ ሥርዓቱ የወጣቶች አፍላ ጉልበት ለግጭትና ለጥፋት አገልግሎት ሳይሆን ሥራ አጥነትና ድህነት ማጥፋት የሚችል ሊሆን ይገባል፣ እነዚህ በተገቢው መንገድ ባለመተግበራቸው በየአካባቢው የሚታዩ ችግሮች እንዲነሱ ምክንያት በመሆናቸው ለጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት እንዳለበትም ነው የጠቆሙት።

የትምህርት ሥርዓቱ ሰብአዊ እና ቁሳዊ ልማትን የሚያፋጥን፣ የዜጎችን የተመራማሪነት፣ የማሰብ፣ የማሰላሰልና የማምረት አቅም የሚያበለጽግ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑንም ነው የተናገሩት።

የመሬት ይዞታ ስሪት ከነበረበት አልፎ አልፎ ለውጦች የሚታዩበት ቢሆንም ዛሬም ለግጭት መነሻ ከመሆን አለመዳኑን የጠቆሙት አቶ ከበደ፤ የመሬት ፖሊሲው ግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባቸው የሚገባቸው ያለፉትን ቁስሎች ማከም ብቻ ሳይሆን እያደገ የመጣውን የሕዝብ ብዛት መሆን እንደሚገባውም አመልክተዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ጋዜጠኝነት የግል ፍላጎትና ስሜትን ማንጸባረቂያ መሆን የለበትም። ባለሙያዎቹ የግል ፍላጎትና ስሜታቸውን ገትተው ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም ሲሉ ሚዛኑን የጠበቀ ዘገባ ማቅረብ አለባቸው፣ ሕዝብ ለሕዝብ ሊያቀራርቡና ሊያግባቡ የሚችሉ ዘገባዎች ላይ ማተኮር ይጠበቅባቸዋል። ዘርፉም በእውቀት ላይ ተመስርቶ ሊተገበር ይገባል።

ግጭት አባባሽ ንግግሮችን፣ ጽሑፎችን፣ ሕትመቶችን፣ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ የሚተላለፉ፣ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የሚለቀቁ መረጃዎች ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል ያሉት አቶ ከበደ፤ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት መለወጥ እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

በሰው ልማት የአስተሳሰብ ደረጃ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ግንዛቤን ሊያሰፉ የሚችሉ ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለው የሥነ ዜጋ ትምህርት ሊተገበር እንደሚገባም ጠቁመዋል። ትውልድን በማስተማር የዴሞክራሲ ሥርዓት ዋና ዋና መርሆዎች የሆኑትን፤ መቻቻልን፣ መግባባትን፣ መተማመንንና መረዳዳትን መፍጠር እንደሚያስፈልግም ነው ያሳሰቡት።

መቻቻል፣ መግባባት፣ መተማመንና መረዳዳት ባሉባቸው ቦታዎች ግጭት ይቀንሳል፣ ሰላምም ይሰፍናል ብለዋል አቶ ከበደ። የመልካም አስተዳደር ችግር የግጭት አባባሽ ምክንያት በመሆኑ የሕዝብን ስሜት ግምት ውስጥ ባስገባ መንገድ ፍትሃዊ እና ሕዝባዊ አሠራር ማስፈን እንደሚገባም ነው የጠቆሙት።

## ወጣቶች የኢትዮጵያ አንድነትና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በሰላም ሚኒስቴር የፌዴራሊዝምና ግጭት አስተዳደር ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ስዩም መስፍን በዚሁ ወቅት እንደገለጹት፤ የመርሃ ግብሩ መዳረሻ ግብ ወጣቶች ማኅበራዊ እሴቶችና የሞራል አቅም እንዲጎለብት በመደገፍ በኢትዮጵያ እርስ በእርስ መደማመጥና መረዳዳትን ማምጣት ነው።

ከጭፍን ጥላቻ ወጥቶ እርስ በእርስ የተጋመደ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር በማድረግ ዘላቂ ሰላምና አገራዊ መግባባትን ማስፈን እንዲሁም ኢትዮጵያዊ እሴቶችንና መርሆዎችን ለወጣቱ ትውልድ የማስተላለፍ ራዕይ መሰነቁን ገልጸዋል።

ትናንት በጅማ፣ በሐዋሳና ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲዎች ከስምንት ሺህ በላይ ወጣቶች የብሔራዊ በጎ ፈቃድ የማኅበረሰብ ልማት አገልግሎት ስልጠና ተጀምሯል።

ከዚህ ቀደም በነበሩ የሦስት ዙር ስልጠናዎች ከዩኒቨርሲቲዎችና ከቴክኒክና ሙያ የተመረቁ 23 ሺህ ወጣቶችን በማሰልጠን ወደ ማህበረሰብ አገልግሎት እንዲገቡ መደረጉን ከሰላም ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ጅማ ዩኒቨርሲቲ ከሰላም ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በሦስት ዙር ከ7 ሺህ 500 በላይ የብሔራዊ የበጎ ፈቃድ የማኅበረሰብ ልማት አገልግሎት ወጣቶችን አሰልጥኖ ያስመረቀ ሲሆን፤ በትናትናው ዕለትም 3 ሺህ የማኅበረሰብ በጎ-ፍቃድ አገልግሎት ሠልጣኞችን በመቀበል ለማሠልጠን መዘጋጀቱ ተገልጿል።

## ከውጭ አገር የትምህርት ዕድሉች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደሚገባ አስተያየታቸውን ለግሰዋል።

ተማሪዎች በውስን ሀብትና ችግሮች ውስጥ ሆነው የሚያስመዘግቡት ከፍተኛ ውጤት የራሳቸው ጥረትና ድካም በመሆኑ የተማሪዎቹን ጥረት ዋጋ ማሳጣት ተገቢ እንዳልሆነም ጠቁመዋል።

እንዲህ ያሉ ተማሪዎች አገራቸው ቀርተው ለመሥራት የሚያስችላቸውንና በአገራቸው ተምረው ውጤታማ የሚሆኑበት ሁኔታ የሚፈጠርበትን መንገድ በፖሊሲ ደረጃ ማመቻቸትም ተገቢ እንደሆነ ተናግረዋል።

በሌላ በኩል በተለያዩ መንገዶች ተማሪዎች አገራቸውን የሚያገለግሉበት መንገድ ከመቀየስ ባሻገር በዝቅተኛ ወጪ ያስተማራቸውን ማኅበረሰብ እንዲያገለግሉ ለማስቻል ሥርዓት ማበጀት ይገባል ብለዋል።

በዚህ ረገድ የተጀመሩ ተግባራት እንዳሉ የጠቀሱት ተባባሪ ፕሮፌሰሩ፣ በተለይም የውጭ አገር የትምህርት ዕድል አግኝተው የሚማሩ ተማሪዎች የማጠናቀቂያ ጽሑፋቸውን ኢትዮጵያ መተው እንዲሠሩ የሚደረግበት አግባብ ተገቢ በመሆኑ ተማሪዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አገራቸውን እንዲያገለግሉ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መፍጠር ይገባል ብለዋል።

እንደ አሜሪካን ያሉ አገራት በሚፈለጉ የትምህርት መስኮች ተማሪዎችን በማሰልጠን ከፍተኛ ገንዘብ በመክፈል ወደ ሥራ እንደሚያሰማራው ሁሉ ኢትዮጵያ ውስጥ በከፍተኛ ማዕረግ የሚመረቁ ተማሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ አሠራር መከተል ተገቢ ነው ብለዋል።

በአሜሪካን አገር ከ25 ዓመታት በላይ በማስተማርና በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የትምህርት ፕሮግራም መሪ ሆነው ሲያገለግሉ የቆዩት ምሁሩ፣ አገራቸውን በበጎ ፍቃደኝነት ለማገልገል ወደ አገር ገብተው ዜጋን እያገለገሉ እንደሆነ ጠቅሰው፣ ዜጎች አገራቸውን እንዲወዱና ለአገራቸው የበኩላቸውን አስተዋፅኦ መወጣት እንደሚጠበቅባቸው ቅድሚያ ሊሠራበት እንደሚገባም ጠቁመዋል።

## በክልሉ ዘላቂ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኃላፊ አቶ እንግዳው ጠገናው በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የአማራ ክልልን ለማተራመስና ኢትዮጵያን ለማፍረስ የተወጠነውን ሴራ በማክሸፍ አመርቂ ተግባራት እየተከናወኑ ነው።

አቶ እንግዳው እንደገለጹት፤ ጠላት ድንበር ላይ ሆኖ ከመዋጋት በተጨማሪ ከውስጥ እና ከውጭ ኃይሎች ጋር ተናቦ ቢሠራም አልተሳካለትም። ይህን ለማክሸፍ የተጀመረው የሕግ ማስከበር ዘመቻ ስኬታማ ሆኗል። ጠላት ይህ አልሳካ ሲለው ሰሞኑን ከሌሎች ኃይሎች ጋር ተደራጅቶ በወለጋ ንፁሃን ዜጎችን ጨፍጭፏል። ይህም ታስቦበት የተደረገ ሲሆን ኦሮሚያ እና አማራ ክልል ዜጎችን እርስ በእርስ ለማጋጨትና አገር ለማፍረስ የታለመ ነው።

ከዚህም ጋር በተያያዘ ግድያውን እናወግዛለን በሚል በዩኒቨርሲቲዎች፣ በመንግሥት ተቋማትና በኅብረተሰቡ ከፍተኛ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ተደርጎም ነበር ያሉት አቶ እንግዳው፤ ሆኖም ድርጊት ማውገዝ ትክክል ቢሆንም ውስጡ አደገኛ ሴራ ነበር ብለዋል።

ሰልፉ በሚካሄድበት ጊዜ የሽብር ጥቃቶችን ለመፈፀም፣ መንግሥትን ለመገልበጥም ጭምር በተደራጀ መልኩ የተከናወነ ሴራ ነበር ያሉት አቶ እንግዳው፤ ይሁንና ሕግ ይከበርልን የሚለውን ጥያቄ ሕዝብ በሰፊው ማቅረቡንና በመድረክ ገፅ ለገፅ በተደረገ ውይይት 6ነጥብ2 ሚሊዮን ሕዝብ የሕግ የበላይነት እንዲከበር መጠየቁን ጠቁመዋል።

እንደ ኃላፊው ገለፃ፤ በክልሉ ሲካሄዱ የነበሩት ሰልፎች ፈቃድ አልነበራቸውም። በክልሉ ስጋት ባልቀነሰበት ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ሰልፉን ሲዘውሩት የነበሩት ጠላቶች ናቸው። የተፈለገው ሰልፉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ሳይሆን በፀጥታ ኃይሉ እና በኅብረተሰቡ መካከል ግጭት በማስነሳትና ንብረትን በማውደም ተቋማትን ለመምታት የታለመም ነበር ብለዋል።

በሕግ ማስከበር ዘመቻው በርካታ ውጤቶች ተገኝተዋል ያሉት አቶ እንግዳው፤ በጥፋታቸው ተፀፅተው በይቅርታ ወደ ማኅበረሰቡ ከተቀላቀሉት በተጨማሪ፤ በአሸባሪ ሕወሓት ወረራ ወቅት ከማረሚያ ቤት እንዲወጡ የተደረጉ 500 ኃይሎች በሠላማዊ መንገድ ወደ ማረሚያ ቤት ገብተዋል ብለዋል።

ሦስተኛው በፍርድ ቤት ውሳኔ አርፎባቸው በማኅበረሰቡ ውስጥ ተደብቀው ይኖሩ የነበሩትና በፋኖ ስም ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ከ500 በላይ የሚሆኑ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል ብለዋል።

ሕግ ለማስከበር በተደረገው ዘመቻ እስካሁን ከ27 በላይ የፀጥታ አካላት መሥዕዋት መሆናቸውን የገለፁት አቶ እንግዳው፤ «ሕግን ለማስከበር መሥዕዋት ለሚሆነው ኃይል የሚጮኽለት አካል የለም። ነገር ግን ሕገ ወጥ ሆኖ ሲዘርፍ ለነበረው አካል የሚጮኸው እጅግ ብዙ ኃይል ነው። ይህ በጣም ያሳዝናል፤ መስተካከልም አለበት ብለዋል።

ጠላት ብድግ ብሎ የአማራ ክልልን ሊደፍር የሚችልበት መሠረት እንደሌለውና፤ በውስጥ ያሉ ማናቸውንም ሕገወጦችን ወይንም ከመንግሥት ጋር መልካም ግንኙነት ከሌለው ማነው የሚለውን ለይቶ እየሠራ ነው ሲሉም ጠቁመዋል። በዚህም ኢ-መደበኛው ኃይል፣ ከቅማንት ጽንፈኛ ኃይሎች፤ ከጉሙዝ አማጺያን ጋርና ከሕወሓት ኃይሎች ጋር ትስስር ፈጥረዋል ብለዋል።

ክልሉ ሕግ ከማስከበር ዘመቻ ጎን ለጎን ከፌዴራልም ሆነ ከክልል መንግሥታት ጋር በቅንጅት እየሠራ መሆኑን የጠቆሙት ኃላፊው፤ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጋር በተሠራ ሥራም በርካታ ሕገ ወጥ ኃይሎችን በመቆጣጠርና ሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን በማጠናከር ጠላት በከፈተው አጀንዳ ሳይሆን በልማትና ሕዝባዊ ትስስሮች አጀንዳውን ማክሸፍ፤ ከቀያቸው የተፈናቀሉትም ወደቦታቸው ተመልሰዋል ብለዋል።

የጉሙዝ የኅብረተሰብ ክፍሎችም «የአማራ ኢ-መደበኛ ኃይል ሊያጠቃህ» ነው በሚል ወደጫካ የወሰዱትን የኅብረተሰብ ክፍልም ወደስፍራቸው መልሰዋል። ከአፋር ክልል ጋርም የተካሄዱ በርካታ መድረኮች መኖራቸውንና የፀጥታ ስጋት በነበረባቸው አካባቢዎች ላይ የአመራር ለአመራርና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ተጠናክሮ በመቀጠሉ ውጤታማ ሥራ ተከናውኗል ሲሉም አብራርተዋል።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሦስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በሚከናወንበት ወቅት፤ ኦነግ ሸኔ እና ሌሎች አሸባሪዎችና የውጭ ኃይሎች በመናበብ የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ሕዝቡ ከፀጥታ ኃይሉ ጋር በመሰለፍ ሊመክታቸው እንደሚገባም አሳስበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የትግራይ ህዝብ ሰንኮፉን ነቅሉ መጣያው ጊዜ አሁን ነው

የትግራይ ህዝብ ለኢትዮጵያ ነጻነት መስዋዕትነት የከፈለ ኩሩ ህዝብ ነው። በየዘመናቱ የመጡ ወራሪዎችን አሳፍሮ ሲመልስ የቆየና ለሀገሩ ነጻነትና ሉአላዊነት ሲዋደቅ የኖረ ነው። በአጠቃላይ ያለትግራይ ህዝብ ኢትዮጵያን ማሰብ አይቻልም፤ ኢትዮጵያም ሆነ ኢትዮጵያዊነት ሙሉ አይሆኑም።

ሆኖም ከህዝቡ የኢትዮጵያዊነት ስነልቦናና የሀገር ፍቅር ስሜት ባፈነገጠ መልኩ ጥቂቶች ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ተነስተዋል። የኢትዮጵያን ዳር ድንበር በማስከበርና አጥንቱን ከስክሶ ደሙን አፍሶ ለዘመናት ከኖረው የትግራይ ህዝብ ውስጥ አፍራሾች ተፈጥረው በኢትዮጵያ ብሎም በትግራይ ህዝብ ላይ መከራን ሲዘሩና ሲያጭዱ ለግማሽ ክፍለ ዘመን ያህል ኖረዋል። በነዚህ ዓመታትም የትግራይ ህዝብ በማያባራ ጦርነት ውስጥ ለመኖር ተገዷል።

የትግራይ ህዝብ ዋነኛ ፍላጎት ከተቀረው ወገኑ ጋር በሰላም፤በእኩልነትና በፍትሃዊነት መኖር ነው። የትግራይ ህዝብ ዋነኛ ጠላት ድህነት ነው። የትግራይ ህዝብ ምኞት ኋላቀርነትና ብልሹ አሰራሮችን ማስወገድ ነው። የትግራይ ህዝብ ዋነኛ ምኞት ንጹህ የመጠጥ ውሃ፤ የኤሌክትሪክ አቅርቦት፤መንገድና መሰል የመሰረተ ልማቶች ማስፋፋት ነው። ሆኖም ከእነዚህ መሰረታዊ ፍላጎቱ በተቃራኒ እኔ አውቅልሃለሁ በሚል መጥፎ እሳቤ አሸባሪው ህወሓት ህዝቡ በጦርነት አዙሪት ውስጥ እንዲማቅቅ ሲያደርገው ኖሯል።

ያለጦርነት መኖር የማይችለው የህወሓት አሸባሪ ቡድን በየጊዜው እየጫረ በሚለኩሰው እሳት የትግራይ ወጣቶች በገፍ እንዲያልቁ አድርጓል። በአሥራ ሰባት ዓመታቱ ጦርነት ከ60 ሺ በላይ የትግራይ ወጣቶች እንደረገፉ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተመሳሳይም ከኤርትራ ጋር በነበረው ጦርነት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወጣት ረግፏል። ለሶስተኛ ጊዜ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊትን ከኋላ ወግቶ በለኮሰው እሳት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች በከንቱ ደማቸው ፈሷል። ይህም አልበቃ ብሎ ዛሬም ለዳግም ጦርነት እየተዘጋጀ መሆኑን እያወጀ ነው።

በአንጻሩ ንጹህ ኢትዮጵያዊ የሆነውን የትግራይ ህዝብ ከተጣባው ሰንኮፍ ለማላቀቅና ነጻነትን ለማወጅ ከትግራይ ህዝብ በላይ ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት የሚችል አካል ባይኖርም የኢትዮጵያ መንግሥት ከጥንስሱ ጀምሮ የሰላም እጁን ሲዘረጋ ኖሯል። ለምጣዱ ሲባል አይጧ ትለፍ እንደሚባለውም አሸባሪው ህወሓት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሰራው በደልና ግፍ ተቆጥሮ የሚያልቅ ባይሆንም መንግሥት የትግራይ ህዝብን መከራና ስቃይ ለማሳጠር በማለም ተደጋጋሚና አሰልቺ የሆኑ የሰላም ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል።

ሆኖም ከጦርነት ውጪ የሰላም አማራጮች የማይታዩት የህወሓት ቡድን በተደጋጋሚ የተዘረጉትን የሰላም እጆች አሳፍሮ መልሷል። በምትኩም ጦርነት በማወጅና በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎችም በጥብጥና ሁከት በመጥመቅ ሀገሪቱ በማያባራ ግጭት ውስጥ እድትገባ እንቅልፉን አጥቶ በመስራት ላይ ይገኛል። ሰርክ በሚሰብከው የጦርነት አዋጅም የትግራይን ህዝብ ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ለመነጠል ያለማሰለስ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።

የሽብር ቡድኑ ባነገሰው ጦርነትና የጥላቻ ፖለቲካ ዛሬ የትግራይ ህዝብ ለበርካታ ቀውሶች ተዳርጓል። የኤሌክትሪክ አገልግሎት፤ውሃ፤የስልክ፤የባንክ እና የትምህርት አገልግሎቶችን ማግኘት አልቻለም። በየጊዜው ለሰብአዊ እርዳታ የሚገባውንም እህል ላደራጀው ታጣቂ ቡድን በማከፋፈል ህዝቡን በማስራብ ላይ ይገኛል። በአጠቃላይ የህወሓት የሽብር ቡድን በትግራይ ህዝብ ላይ ተነግሮ የማያልቅ ግፍና በደለም በመፈጸም ላይ ይገኛል።

ስለዚህም ዋነኛው መፍትሄ ያለው በትግራይ ህዝብ እጅ ውስጥ ነው። ለ50 ዓመታት ተጣብቶት የኖረውን አጥፊ ቡድን ከራሱ ላይ የሚያስወግድበት ጊዜ አሁን ነው። ከዚህ በላይ ለቡድኑ ዕድል መስጠት በራስ ላይ ማባሪያ የሌለውን ዕልቂት መጋበዝ ነውና ፤የትግራይ ህዝብ የተጣበቀበትን ሰንኮፍ ነቅሎ ነጻነቱን ሊያውጅ ይገባል።


ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# ከጦርነት ‹ሠላም› አይመጣም

**በምስጋና ፍቅሩ**

ሠላም ከሌለ ወጥቶ መግባት ቅንጦት ይሆናል። ነግዶ ማትረፍ የማይታሰብ ነው። ተምሮ ለቁምነገር መብቃት ዘበት ነው። ሀገር በዜጎቿ ጥረት እንዳታድግ እንቅፋት ከመሆን አልፎ የሌሎች ሀገር እርዳታ ናፋቂ እንድትሆን ያደርጋታል። ይህ መሆኑ ደግሞ ጊዜው ይረዝም እንጂ በቀጥታም ይሁን በእጅ አዙር በሌሎች ሀገራት የመጠምዘዙን ዕድል የሚያሰፋ ነው። ለዚህም ነው ስለ ሠላም ብዙ የተባለው፤ ስለ ሠላም ብዙ የተዜመው፤ ስለ ሠላም ብዙ የተነገረው። ይሁን እንጂ ብዙዎች ሠላምን የሚናፍቋት እንዲሁም ጥቅሟ የሚገባቸው የጦርነት አስከፊነት እና ተያይዞ በሚመጡት ችግሮች ጽዋውን ሲጎነጩት መሆኑ አስገራሚው ጉዳይ ነው።

ሀገራችን በአሁኑ ወቅት የሰላም እጦት ላይ ናት፤ በዚህም ዜጎች የተለያየ የሰላም ማጣት ችግሮች ውስጥ እየወደቁ ነው ። በተለያዩ ቦታዎች የሚሠሙ ግጭቶች ወዳልተፈለገ ደረጃ እንዳይደርሱም የብዙዎች ስጋት ከሆነ ውሎ አድሯል። ከሰሞኑም በኦሮሚያ ክልል በወገኖቻችን ላይ ከደረሰው ጥቃት በመነሳትም ብዙዎቻችን የልብ ስብራት ውስጥ ነን። ሁኔታዎች በብዙ መልኩ በዚሁ ከቀጠሉ አሳሳቢነቱ ለማንም ሊነገር የሚችል አይደለም።

በዚህ ሀገራዊ ሁኔታ ውስጥ መንግሥት ችግሮችን በሰላማዊ አማራጮች የመፍታት ፍላጎት እንዳለው በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ በኩል አስታውቋል። ይህም ሰላም ለሚፈልገውና በሰላም እጦት ውስጥ ለሚገኘው ህዝባችን እፎይታ ፈጥሯል። በተለይም መንግሥት ከአሸባሪው ህወሓት ጋር ሰላም ለማስፈን እራሱን ለድርድር እያዘጋጀ መሆኑን ማሳወቁ በራሱ ስለ ሰላም እንደ አንድ እድል እየታየ ነው (ውጤቱ በቀጣይ የሚታይ ቢሆንም)።

ጦርነት አስጨናቂ ነው ፤ ሊያስከትል ከሚችለው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ውድመት ለማንም የሚነገረው አይደለም። በተለይ እኛ ኢትዮጵያውያን ካሳለፍናቸው የጦርነት ታሪኮች አንጻር ጦርነትን ሁለንተናዊ አስከፊነት በተጨባጭ ማየት የቻልን ነን። በጦርነት ወቅት ሴቶችና ሕጻናት ግንባር ቀደም ተጠቂዎች የመሆናቸው ጉዳይ ደግሞ እኛ ሴቶች ድምጻችንን ከፍ አድርገን እንድንጮህ ፤ ለመፍትሄውም ግንባር ቀደም እንድንሆን ያስገድደናል። ።

በጦርነት ወቅት የሚከሰት ሞት፣ መደፈር፣ ስደት፣ ርሃብ፣ እርዛት፣የስነልቦና ጉዳት እና መፈናቃል በአጠቃላይ አስከፊ በደል ከሚደርስባቸው መካከል ግንባር ቀደሞቹ ሴቶች እና ህጻናት ናቸው። አረጋውያንና አካል ጉዳተኞችም ሰለባዎች ናቸው። ይህንን ቆም ብሎ በማሰብ የጦርነቱን መንገድ ገሸሽ አድርጎ ለእርቅና ይቅር ለመባባል ሁሉም እናቶች ልጆቻቸውን በመገሰጽ ለሠላም የድርሻቸውን መወጣት ይገባቸዋል።

ባለፈው ዓመት በሀገራችን የሠሜኑ ክልል ጦርነት ብናነሳ እንኳን ለነገ ሀገር ተረካቢ የሚሆኑ ዜጎች ከትምህርት ገበታቸው ርቀው፣ ተፈናቅለው፣ ቤተሰቦቻቸውን አጥተው እና መጨበጥ የነበረባቸውን እውቀት እንዳያገኙ አድርጓቸዋል። ነገሮች በዚህ ከቀጠሉ እና ጦርነቱ ዳግም የሚቀሰቀስ ከሆነም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የነገ ሕይወታቸው ላይ ጥቁር ጠባሳ ጥሉ ማለፉ የማይቀር ነው ።

በጦርነቱ ከሠው ሕይወት መጥፋት እና መፈናቀል በተጨማሪም በትምህርት ተቋማት፣ በጤና ተቋማት እንዲሁም በሃይማኖት ተቋማት በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ ውድመት ደርሶባቸዋል። እነዚህን ተቋማት ለመገንባት በጣም ከፍተኛ የሚባል በጀት እንዲሁም ጊዜ መፈለጉ በራሱ የሀገሪቱ እድገትን ምን ያህል ወደ ኋላ እንደሚያስቀራት ለመረዳት የትኛውንም አይነት ባለሙያ መሆን አያስፈልገውም።

‹አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ› የሚለው የአባቶቻችን ብሂል እኛው ላይ እንዳይደርስ የጦርነት ጉሰማ ለሚያሰማው አካል ጀርባ በመስጠት፤ የሠላሙን መንገድ ለሚያሳየው አካል ጆሮቻችንን በመስጠት ከትላንት ታሪካችን መማር ይኖርብናል።

በእርግጥ ሠላማችንን የማይፈልጉ የሀገር ውስጥም ይሁን የውጭ ጠላት እንዳሉን እሙን ነው። እርስ በእርስ ስንጋደል ካራ ለማቀበል እጃቸው በፍጥነት የሚዘረጋላቸው ብዙዎች ናቸው። እነዚህ ኃይሎች ወደ ሠላሙ መንገድ ለመምጣት ለምናደርገው ጥረት ተግዳሮት መሆናቸው አይቀርም ። ስለዚህም የማህበራዊ አንቂዎች፣ ተጽዕኖ ፈጣሪ እና ተሰሚነት አላቸው የሚባሉ ሰዎች በሀገራችን ላይ ሠላም እንዲመጣም የድርሻቸውን መወጣት አለባቸው።

በመንግሥት በኩል ሠላም እንዲሰፍን እያደረጋቸው ካሉ ጥረቶች መካከል ከህወሓት ጋር ሰላማዊ ንግግር ለማካሄድ ሰባት ተደራዳሪ ኮሚቴዎቹን ማዋቀሩን እና የብልጽግና ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴም ቢሆን ግጭቱን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት ውሳኔ ላይ መድረሱንም በበጎ ጎን መጥቀስ ይቻላል።

ይህም አሰየው የሚባል ጅምር ሲሆን፤ በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች የሚደርሱ ጥቃቶችን ግን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት በመስጠት በተስፋ መቁረጥ እና አለመቁረጥ ውስጥ የሚዋልለውን ሕዝብ ደህንነቱን የማረጋገጥ ሥራ ከመንግሥት ይጠበቃል።

የሃይማኖት ተቋማትም ቢሆኑ ሚናቸው በምድሪቱ ላይ ሠላም እንዲሰፍን፤ ሰዎች እርስ በእርሳቸው ተከባብረው እና ተዋደው እንዲኖሩ ማስተማር ነውና ወደ ጥፋት ጎዳና የሚሄደውን ሕዝባቸውን በማስተማር ብሎም በመገሰጽ ስለ ሠላም ሊሰብኩ እና ሊዘምሩ ይገባል።

እንደምናየው የችግሩ ስፋትና ውስብስብነት ስር የሰደደ እንደመሆኑ ለመፍትሄው መንግሥት፤ የሃይማኖት አባቶች፤ የማህበረሰብ አንቂዎችና የፖለቲከኞች ተሳትፎ ብቻውን በቂ አይሆንም። ህዝብ እንደ ህዝብ የጉዳዩ ባለቤት በመሆን ሊሰራቸው የሚችልን የሚገባም በርካታ ነገሮች አሉ። ወላጆች ልጆቻቸውን ስለሰው ልጅ ክቡርነት ስለ ሀገር አንድነትና ስለህዝብ ፍቅር ሳይታክቱ ሊመክሩ ይገባል። ትውልዱ በተሳሳተ ትርክት ተበርዞ እያለ እሮሮ ማሰማቱ መፍትሄ ሊያመጣ አይችልም።ስለሰላም ጉዳይ በድፍረት መወገዝ ያለበትን ተግባር ማውገዝ፤ መመስገን ያለበትን ተግባር ማመስገን የእያንዳንዳችን ኃላፊነት መሆን አለበት። በተለይም ሃይማኖታዊ በአላት ወቅት የምንለዋወጣቸው የሰላም መልእክቶችና የምናደርጋቸው መደጋገፎች ከዘወትር ተግባሮቻችን መካከል ሊሆኑ ይገባል። የሲቪክ ማህበራትም ችግር ሲደርስ ብቻ እየወጡ ከማውገዝ በዘላቂነት ሰላማዊ ማህበረሰብ እንዲፈጠር ከምንም በላይ ቅድሚያ ሰጥተው ሊሰሩ ይገባል።

ብዙዎች ‹ግንቦት 20› ሲከበር ይተቹ ነበር ወይም መከበሩን አይፈልጉትም። ምክንያታቸው ደግሞ ወንድም ወንድሙን ገድሎ እንዴት ይከበራል? የሚል አመለካከት ስላላቸው ነው። እውነት ነው። ወንድም ወንድሙን ገድሎ የሚከበር ድልም ይሁን የሚወሳ ሽንፈት በታሪካችን በድጋሚ ሊመዘገብ አይገባም።

ይልቁንም ሀገሪቱ ከተጋረጠባት የሠላም መደፍረስ፤ ከእርስ በእርስ አለመከባበር እና አለመደማመጥ አደጋ አውጥተን የሠላሙን መንገድ ማሳየት ብልህነት እና አስተዋይነት የሚጠይቅበት ጊዜው ዛሬ ነውና ሁላችምን የሠላሙን መንገድ በመምረጥ ሀገራችንን ከገባችበት የችግር አረንቋ ማውጣት ከመፍትሄዎች ሁሉ የተሻለው መፍትሄ ነው ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ሙካሽ እንደ ፋሽን

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

የሙካሽ አልባሳት በነገሥታቱ በመሳፍንቱና በመኳንንቱ ይዘወተር የነበረ የክብር ልብስ ነው። በወቅቱ እንደ ካባ ተደርጎ በለበሱት ልብስ ላይ ጣል የሚደረግ። ነገር ግን እንደ ሌሎች ካባዎች ባለመሆኑ እንዲሁም በአንገታቸው ዙሪያና ጫፋቸው ዘርፍ ተበጅቶለት በወርቅማ ወይም በብርማ ጌጣጌጦች በወርቅ ዘቦ ስፌት ተሰፍቶ ለክብር እና ለፕሮቶኮል አገልግሎት ይለበስ ነበር።

ሙካሽ የሚለበሰው በነገስታቱ አካባቢና በቤተክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ደረጃ ለክብራቸውና ለማዕረጋቸው መታያ በመሆኑ ተራው ሰው ሊለብሰው አቅሙም አይፈቅድም ። አቅሙ ቢፈቅም ይለብሰው ዘንድ እንደማይፈቀድለት በዘመኑ የነበሩ ሰዎች ያወጋሉ።

የሙካሽ ካባ ልብስን የከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤ ካባ፣ ላንቃ፣ የቤተክርስቲያን፣ የቤተመንግሥት የማዕረግ ልብስ፣ ላንቃ ያለው የመኳንንት ልብስ በሚል ይፈታዋል። ላንቃ ካባ ማለትም ዘርፍ ዘርፍ እየተደረገለት በለምድና በካባ ላይ በወርቅና በብር ጉብ ጉብ የሚጠለፍ ለምድ የማዕረግ መለዮ ልብስ ሲለው፣ የሙካሽ ጨርቅን አጥላስ ከሩጥ ሐር የተሰራ በልዩ ልዩ ዓይነት ቀለማት እያጥበረበረ የሚታይ የሐር ልብስ በማለትም ይገልጸዋል።

ከላይ እንደተገለጸው ካባ ከአጥላስ ፣ከሐር የሚሰፋ ክብ ወይም ባለኳስ ካባ ማለት መሆኑን መዝገበ ቃላቱ ያስረዳል። ካባ በልብስ ላይ ለክብር ለማዕረግ የሚደረብ ልብስ እንደመሆኑ፤ ካባ የሚለው የአማርኛ ቃላትም ፍቺው በምስጋና ላይ ምስጋና ደረበ፤ ከፍ ከፍ አደረገ እንደመሆኑ (ዝኒ ከማሁ)የሚለው የግዕዝ ቃልም ምናልባት ካባ ከሚለው ቃል ተመዞ ሊሆን ይችላል።

ሙካሽ በካባ መልክ የሚለበስ ልብስ እንደነበር ሁሉ ማሞካሸት የሚለውን ቃል ስናስበውም ሙካሽ ከሚለው ቃል የመጣ ሊሆን ይችላል። በነገሥታቱ ዘመን ለክብር ለማዕረግ፤ ለፕሮቶኮል የሚለበሰው ሙካሽ ደርግ ሲመጣ ቦታ እንዲያጣ ተደረገ። በአብያተ ክርስቲያናት፣ በዓላት አልፎ አልፎ ተለብሶ የሚታይ



ሲሆን ሰዎች ለሰርግም ለብሰው ይገለገሉበታል።

በደርግ የአድኃሪያን ልብስ ነው ተብሎ ቦታ ያጣው ካባ አሁን አሁን የተወሰነ ቦታ እያገኘ ይመስላል። በዚህም ሙካሽ እንደ ፋሽን ሲለበስ ይታያል። ከበዓል ቀናት በተጨማሪ በሰርግ፣ በልደት፣ በጋብቻ፣ በበዓል፣ ትልልቅ ሽልማት ሥነሥርዓቶች ላይ መታየት ጀምሯል። የአጸደ ሕጻናት ተማሪዎች ሳይቀሩ ሲሸለሙ እንዲሁም ልደታቸውን ሲያከብሩ ሙካሽ መልበሳቸው በዘመናችን ዳግም ፋሽን ሆኖ ለመምጣቱ አንዱ ማሳያ ነው።

ሙካሽ የሚሰራበት ጨርቅ ከሌላው ጨርቅ ለስለስ ያለ በመሆኑ አንዳንዶች የሐር ጨርቅ ነው ይላሉ። አንዳንዶች ደግሞ የሙካሽ ጨርቅን ወላንሳ ይሉታል። አይነቱ ጥሩና በጣም ለስላሳ የሆነ የማይጎረብጥ ማለፊያና የሚመች ጨርቅ እንደማለት ነው። የማይጎረብጥ፣ ሰውን የማይበድል አመለ ለስላሳ ሰውም ወላንሳ ይባላል። የሙካሽ ጨርቆች በብዛት ነጭ፣ ቀይ፣ ጥቁር፣ ሰማያዊና አረንጓዴ አይነት ናቸው።

ቀይ ከፋይ ወይም አረንጓዴ ባለወርቅ ዘርፍ፤ በዙፋንና በመከዳ ላይ የሚዘረጋ የሚነጠፍ ነው። በቲሸርት መልክ ወርቀ ዘቦ ተጠልፎበት ወጣቶችና ጎልማሶች ሲለብሱትም ይታያል። ኮረዶችና እናቶችም በጉርድ ቀሚስ መልክ ያለጥልፍ ጨርቁን የሚለብሱት ሲሆን፤ በብዛት ልክ እንደጥበብ አልባሳት ወይም ቀሚሶች ወርቀ ዘቦ ተጠልፎበትም በበዓላትም ሆነ በአዘቦት ቀናት ሲለብሱት እየታየ ነው። ይህም ለማዕረግ ብቻ የሚለበሰው የሙካሽ አልባሳት በአዘቦት ቀንም ጭምር እየለበሱት መታየቱ ልብሱ እንደ ፋሽን ለመምጣቱ ማሳያ ነው።

በመርካቶ አውቶቡስ ተራ አካባቢ በሙካሽ ጥልፍ ስራ የተሰማራው ወጣት ያሲን ተሾመ፣ የሙካሽ ስራ አድካሚ እንደሆነና ትዕግስትን እንዲሁም ጥበብን እንደሚጠይቅ ይናገራል። ስራውን በልጅነቱ በመርካቶ አካባቢ ከሚኖሩ ሰዎች እያየ መማሩንም ያስረዳል። በሙያው አምስት ዓመት እንደሆነውና በአጋጣሚ በአካባቢው የሚሰሩ ሰዎች ስለነበሩ ጥበቡንና ሙያውን ወዶት እየሰራበት እንደሆነም ይናገራል። የጥልፍ ስራውና ጉብ ጉብ ማለትም አንገት ላይ እና ደረት ላይ ጫፍ ጫፉ እንደ ዘርፍ የሚጠለፉት ብርማም ሆነ ወርቅማ ጌጣ ጌጦችም ጭምር ስላሉበት ስራው አድካሚ መሆኑን ያስረዳል። ብዙ ትጋት ይፈልጋል የሚለው ወጣቱ፤ የሙካሽ ስራው በብዛት ከፋይ ጨርቅ ላይ ቢሰራም ጥበብ ላይ ከፋይ ጨርቁ አንገት ላይና በሴቶች ቀሚስ ጫፉ ዙሪያውን ከፋይ ተደርቦበት እንሚሰራ ያስረዳል።

ከፋይ የሙካሽ ጨርቆቹ ቀሚስ፣ ካባ እና የወንዶች ቲሸርት እንደሚሰራበትና በተለይ ቀሚስና ቲሸርቱ እንደ ጥበብ ወርቀ ዘቦ ብቻ ተጠልፎበት በብዛት ሰዎች እንደሚገዙትና ተወዳጅ እየሆነ መምጣቱን ይናገራል። በአካባቢው ብዛት የሙካሽ ስራ እንደሚሰራ የሚጠቁመው ወጣት ቀደም ሲል አልባሳቱ ለንጉስና መሳፍንት ቤተሰቦች ይሰራ እንደነበር በመግለፅ የሚሰሩትም ትልልቅ ሰዎች መሆናቸውን ያስረዳል። እነዚህ ሰዎችም ሙያውን አውርሰው ስለሄዱ ወጣቶች እንደቀጠሉበት ይናገራል።

አሁን አሁን ዜጎች የሀገራቸውን ልብስና ባህል መጠቀም በመጀመራቸው ሙካሽ እንደጥበብ አልባሳት መለበሱ እየተዘወተረ ነው። ሙካሽ በብዛት የሚሰራው በካባ ብቻ ስለነበር አሁን ወጣቶችና ኮረዶች በስፋት እንደፋሽን አድርገው እያስጠለፉ ሲለብሱት ይታያል። ባህላዊው ከዘመናዊው ጋር እየተቀላቀለም ልዩ ውበት ባለው መልኩ እየተሰራ ይገኛል።

ለሙካሽ ስራ የሚያገለግሉት ወርቅማ እና ብርማ ጉብ ጉብ ጌጣ ጌጦች በተለይ ለካባው ስራ ወሳኝ በመሆኑ በብዛት ከዱባይ፣ ከቻይና እና ከህንድ፤ ጨርቁም ከቻይናና ከዱባይ እንደሚመጣ ወጣት ያሲን ይናገራል። የሙካሽ ካባዎች ዋጋቸው ውድ ስለሆነና ስለማይዘወተሩ ሰዎች በብዛት በኪራይ መልክ በዓል ሲኖርባቸው መጠቀምን እንደሚመርጡም ያስረዳል። በዚህም ልብሱን የሚሸጡ ሱቆች የበለጠ ተጠቃሚ ሆነዋል። እነዚህ ነጋዴዎች ከማከራየት በዘለለም ለደንበኞቻቸው እያዘጋጁ በመርካቶ፣ ሽሮሜዳ፣ ኮልፌና ቦሌ እንደሚሸጡና እንደሚያስረክብም ያስረዳል።

በአምስት ኪሎ አካባቢ የቤተ ክህነት አልባሳትን በማዘጋጀት ስራ የሚተዳደረው አብርሃም ይበቃል፤ ሙካሽ ለሠርግ፣ ለልደት፣ ለጋብቻ፣ ለበዓል፣ ለሽልማት ሥነሥርዓት የሚያገለግል የማዕረግ ልብስ እንደሆነ ይናገራል። ዋጋው ውድ ስለሆነ ሰዎች በብዛት ተከራይተው መገልገልን እንደሚመርጡም ያስረዳል። ነገር ግን በዘመናችን ጨርቁ ወጣቶች እና ኮረዶች እየተወደደ በመምጣቱ በወርቀ ዘቦ እያስጠለፉ ሲገለገሉበት ማየት የተለመደና ጨርቁ ከካባ በዘለለ እያገለለ እንደሚገኝ ይናገራል። ይህም ዳግም እንደፋሽን ሆኖ ስለመምጣቱ ማሳያ መሆኑን ያስረዳል።

# ማረፊያ/ትዝብት

## የግል እውነት የለም

**አቤል ገ/ኪዳን**

የእኛ ነገር ያስቀኛል። የሆነ ብኸ ያለብን ነገር ያለ ይመስላል። ምንም ነገራችን የማይያዝ የማይጨበጥ ነው። ዛሬ የወደድነውን ነገ እናራክሳለን ፤ ዛሬ የጠላነውን ነገ እናሞግሳን። ለማሞገስም ለማንኳሰስም አንፈጥናለን። ሁሉቱንም ስናደርግ ግን በማስረጃ እና በመረጃ ሳይሆን በመሰለን ነው። ሁላችንም መስማት የምንፈልገውን የሚናገርልን ሰው ስናገኝ የኔ ጀግና፣ የኔ አንበሳ፣ የኔ ደፋር ምናምን እያልን እንሰቅለዋለን። ከዚያ በተቃራኒ ሰውየው የራሱን እውነት ሲናገር እና ያ የሱ እውነት እኛ እውነት ነው ብለን ከምናስበው ነገር ጋር አልገጥም ሲል እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ አድርግን እንዘልፈዋለን። ባንዳ፣ ካድሬ፣ ከሀዲ ተከፋይ ወዘተ.. የሚል ታርጋ እንለጥፍለታለን። የራሳችንን እውነት አጽድቀን ለዚያ ማረጋገጭ የሚሆን ነገር በመፈለግ ነው ተጠምደን የምንውለው።

በሥነ ልቡና ባለሙያዎች አጠራር እንዲህ አይነቱን ሁኔታ ኮንፈርሜሽን ባያዝ ይባላል። ከብዙ የአመለካከት መዛባቶች መካከል አንዱ ነው። ይህ መዛባት ሰዎች የሚያገኙትን መረጃ በተሳሳተ መልኩ እንዲረዱ እና እንዲተነትኑ የሚያደርግ አደገኛ መዛባት ሲሆን የዚህ መዛባት ሰለባ የሆኑ ሰዎች በአንድ ጉዳይ ላይ መረጃ ሰብስበው የሚወስኑ ሳይሆኑ ወስነው ውሳኔያቸውን የሚያጠናክር መረጃ ፍለጋ የሚሄዱ ናቸው። የኛም ሁኔታ እንደዚህ ነው። በአንድ ጉዳይ ላይ አንዴ በሚጨበጥም መረጃ ይሁን በስሚ ስሚ አቋም እንይዛለን። ከዚያ በኋላ ያን አቋም መቀየር ይከብደናል። ስለዚህ እኛ ያመንበትን ነገር የሚያወሩ ሰዎችን ፍለጋ አደባባይ እንወጣለን። እነሱን ስናገኝ እናሞግሳለን። ከዚያ በተቃራኒ የሆነ ሃሳብ ስንሰማ ግን እውነት እንዳለው ብናውቅ እንኳ ለመቀበል እንቸገራለን።

ይህን እኛ ያለንበትን ሁኔታ የሚገልጽ አንድ ጥቅስ አንድ ቦታ ላይ ሰምቻለሁ። «The truth is what you choose to believe» ይላል። እውነታው አንተ ለማመን የመረጥከው ነው ማለት ነው ትርጉሙ። ይሄ ነው የብዙዎቻችን ባህሪም። የኮንፈርሜሽን ባያዝ ተጠቂ ስለሆንን የምናምነው ሀቁን ሳይሆን ለማመን የምንፈልገውን ነው። ነገሩ ግን እንደዚያ ሊሆን አይችልም። ዳንኤል ፓትሪክ ሞህኒያን የተባሉ ምሁር በአንድ ወቅት እንደተናገሩትም ማንም ሰው የራሱ አስተያየት እንጂ የራሱ ሀቅ ሊኖረው አይችልም። እውነታቸውንም ነው። ሊኖር የሚችለው አንድ ሀቅ ነው። ጸሀይ በምስራቅ ወጥታ በምእራብ ትጠልቃለች። ይህ አንድ ሀቅ ነው። በዚህ ሀቅ ዙሪያ የተለየ አስተያየት ሊኖር ይችላል። ነገር ግን ሀቁን ሊቀይር የሚችል ነገር የለም። ሁለተኛ ሀቅ ሊኖርም አይችልም። በብዙ ሀገራዊ ጉዳዮቻችን ላይም ያለው ሀቅ አንድ ነው። ነገር ግን ከብሄራችን ፤ ከሃይማኖታችን ፤ ከፍላጎታችን ወዘተ አንጻር ነገሮችን እያየን ለኛ ብሄር ለኛ ሃይማኖት ለኛ ፍላጎት የሚሆን አዲስ ሀቅ ልንፈጥር ስንማስን የምንውል ሆነናል። በዚህ መንገድም ነው ብዙ የጀግንነትም የውርደትም ታሪክ ያዋለድነው። ብዙዎቻችን ያለን ሙብት በጉዳዩ ላይ አስተያየት የመያዝ ብቻ እንደሆነ ረስተን ለኛ የሚስማማ አዲስ ሀቅ ለመፍጠር ነው ጥረታችን።

ከዚህ ጋር የሚመሳሰል አንድ ታሪክ አለ። የአሜሪካ የቀድሞ ፕሬዚደንት ዶናልድ ትራምፕ አማካሪ የነበሩት ኬሊ አን ኮንዌይ የተጠቀሙት አማራጭ እውነት (alternative truth) የተሰኘ ገለጻ ነው። በወቅቱ ወይዘሮዋ በአሜሪካ ሚዲያ በከፍተኛ ደረጃ የተተቹ ሲሆን እውነት አንድ ነው አማራጭ እና ሁለተኛ እውነት ሊባል የሚችል ነገር የለም ተብለው ሞግተዋል። በኋላ ላይ እሳቸውም ይቅርታ ጠይቀዋል። አማራጭ እውነት ያልኩት ሌላ አዲስ እውነት ለመፍጠር ሳይሆን ተጨማሪ መረጃ ለማለት ነው ብለው አስተባብለዋል። ለሁሉም ነገር የራሳቸውን አማራጭ እውነት መፍጠር የሚፈልጉ እኛም ጋር ብዙዎች አሉ። የሚያርማቸው ሰው ያስፈልጋል።

ከላይ እንዳልኩት ብዙዎቻችን በተለይ በፖለቲካው ጉዳይ የኮንፈርሜሽን ባይዝ ተጠቂ ነን። በዚህም የተነሳ እኛ ላመንበት ነገር የሚስማማ አዲስ እውነት ስንፈጥር እና ያመኑ ሰዎችን ስናፈላልግ ነው የምንውለው። እኛ መስማት የምንፈልገውን ከተናገረ ማንንም ቢሆን ለመቀበል ዝግጁ ነን። እስኪ ባለፉት ጥቂት ቀናት ውስጥ የተከሰቱትን ነገሮች እንኳን እንመልከት። በመንግሥት ላይ ቅሬታ ያላቸው ሰዎች ድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን ሙዚቃ ሲያወጣ በምን አይነት ስሜት እንደተቀበሉት። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የሆኑት ሰው በኦሮሚያ ክልል እየተካሄደ ስላለው ጭፍጨፋ የሰጡትን አስተያየት እና ያን ተከትሎ የመጣላቸውን አድናቆትም እዩ ። በተቃራኒው እነዚህ ሰዎች የመንግሥት ደጋፊ በሆኑ ሰዎች የደረሰባቸውን ትችትም እዩ። ይህን ያየ ሰው እንደ ሕዝብ ምን ያህል የኮንፈርሜሽን ባያዝ ተጠቂ እንደሆንን በበቂ ሁኔታ መገንዘብ ይችላል። ይህ ባህሪያችንም ነው መጠቀሚያ የሚደርገን። ማንም መስማት የምንፈልገውን እየነገረ በተግባር ግን ከዚያ በተቃራኒ እያደረገ ሊጫወትብን ይችላል።

እና መፍትሄው ምንድን ነው? መፍትሄው ቀላል ነው። እኛ የምንፈልገውን እውነት ሳይሆን እውነት የሆነውን እውነት መፈለግ መጀመር አለብን። ምክንያቱም የሀገራችን ችግር በእኛ የእውነት ፍላጎት እና አረዳድ ልክ ሳይሆን በነባራዊው እውነታ ላይ ተመስርቶ ነው ሊፈታ የሚችለው። እገሌን ጀግና ነው ብለን ስለተስማማን ጀግና አይሆንም። እገሌ ጨፍጫፊ ነው ስላልንም እንዲሁ ጨፍጫፊ አይሆንም። እኛ ሆኗል ብለን ስላመንን አይሆንም ፤ አልተፈጸመም ብለን ስለካድንም ነገሩ አይሰወርም። እውነቱ በቦታው ነው ያለው። ስለዚህ የሁላችንም ጉዞ ወደ እውነቱ ነው መሆን ያለበት። መድከም ያለብን እውነቱ ላይ ለመድረስ ነው እንጂ የራሳችንን እውነት ለመፍጠር አይደለም። ማመን ያለብን ጆሯችንን ሳይሆን የሚታይ የሚዳሰሰውን ሀቅ ነው። አካሄዳችን ከመረጃ እና ማስረጃ ተነስቶ ወደ ድምዳሜ መጓዝ እንጂ ድምዳሜ ይዞ ከዚያ ለዚያ የሚሆን መረጃ እና ማስረጃ ወደ መሰብሰብ አይደለም። በተለይም የኢትዮጵያን ችግርን መፍታት የሚፈልግ ሰው ድካሙ በሙሉ እውነትን በማግኘት ላይ መሆን አለበት። ምክንያቱም አሁን የገባንባቸው ችግሮች በሙሉ ዋነኛ ማጠንጠኛ በሀሰት የተፈበረኩ ትርክቶች ናቸውና።

# ነፃ ሃሳብ

# እውቀታችንን ለነውጥ ሳይሆን ለለውጥ እንጠቀም

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ህይወት የትክክል ነገር ቅደም ተከተል ናት። ረጋ ብለን ካስተዋልን ህይወት በልብና በአእምሮ እውነት ስር የተዋቀረች እንደሆነች እንደርስበታለን። እንደሚታወቀው መነሻችን የፈጣሪ ህልውና ነው። በፈጣሪ ህልውና ውስጥ ደግሞ ጎደሎነት የለም። ጎደሎነታችን ሁሉ በምድር ያገኘናቸው የራሳችን የእጅ ስራ ውጤቶች ናቸው። በፈጣሪ አምሳያ ፈጣሪን መስለን ነው ሰው የሆነው። ፈጣሪን ለብሰን፣ ፈጣሪን ወርሰን ነው የተፈጠርነው።

ራሳችንን ስንገዛና ሀሳቦቻችንን መቆጣጠር ስንጀምር ምንም ነገር በእኛ ላይ ኃይል አይኖረውም። በተቃራኒው ሀሳቦቻችን ሲገዙንና ለስሜቶቻችን እጅ ስንሰጥ ሚዛናዊነት ርቆን ለስህተት እንዳረጋለን። ሰው ሀሳቡን ሲገዛና በሀሳቡ ሲገዛ የተለያየ ነው፡ ሀሳባችን ሲገዛን ለጥፋት ነው የምንሮጠው። በሌሎች ላይ ስቃይን ለመፍጠር ነው የምንጣደፈው። የትዕግስትንና የመነጋገርን ስፍራ አናውቀውም። ሩጫችን ሁሉ ወደ ውድቀት ነው የሚሆነው።

ሀሳባችንን ስንገዛው ግን በእውቀትና በምክንያት ነው የምንኖረው። በስሜት መሸቶ የሚነጋ አንድም የህይወት ማለዳ አይኖረንም። ከሰዎች ሁሉ ጋር በፍቅርና በመቻቻል፣ በምስጋናም የሚኖር አእምሮና ልብ እናበጃለን። በማህበራዊ መስተጋብራችን ጤነኛ እንሆናለን።

“የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሄርን መፍራት ነው“ ይላል የመጻፍ ቅዱስ ቃል፤ የእውቀት ቀዳማይ ደግሞ ራስን ማወቅ ነው ይባላል። እኚህ ሁለት እውነታዎች እስከ ህይወት ፍጻሜአችን ድረስ የሚከተሉን የሰውነት አልፋ ናቸው። ሰው እግዚአብሄርን ካልፈራ ምንም ነው። ሰው ራሱን ካላወቀ ምንም ነው።

እግዚአብሄርን መፍራትና ራስን ማወቅ በምድርና በሰማይ ክብርና ዋጋ የሚያሰጠን የጽድቅ መንገድ ነው። ነፍስ እግዚአብሄርን ስትፈራ መጀመሪያ የምታደርገው ኩነኔን መሸሽ ነው። ነፍስ እግዚአብሄርን ስትፈራ መጀመሪያ የምትማረው የጽድቅን ስራ ነው። ምክንያቱም ኩነኔ የሰውን ልጅ ከእግዚአብሄር መንፈስ የሚያርቅ ስለሆነ ነው። ምክንያቱም ጽድቅ እግዚአብሄርን የማፍቀር ምልክት ስለሆነ ነው።

ሰው ራሱን ሲያውቅ መጀመሪያ የሚረዳው በሰውነቱ ለሌሎች መከራ ሳይሆን ደስታ እንዲሆን የተፈጠረ መሆኑን ነው። አሁን ላይ ያጣነው እኚህን ጥበቦች ነው። ወይ እግዚአብሄርን አንፈራ ወይ ሰውነታችንን አንረዳ በስሜት እየጋለብን ስህተት መስራት የሰውነት ግብራችን ሆኗል። ፈርሀ እግዚአብሄር የሞላት አገራችን የግፈኞችና የነውረኞች መኖሪያ ከሆነች ሰነባብታለች። ከሩቅ አገር የሰማነውን ዛሬ አገራችን ላይ በአይናችን እያየን ነው።

እግዚአብሄርን መፍራት ትተናል። አባቶቻችን ያስተማሩንን አብሮ የመብላት ባህል ዘንግተናል። አገር የሚያስፈልጋት በጥበብ ፈጣሪውን የሚፈራ፣ በእውቀት ደግሞ ራሱን የተረዳ ትውልድ ነው። አገር የሚያስፈልጋት በይቅርታ ለጠላቶቹ ምህረት የሚያደርግ፣ በትዕግስት ሀያላኖችን የሚያሸንፍ መንፈስ ነው።

እግዚአብሄርን ስንፈራ በየትም ቦታ ሙሉ ነን። በየትም ቦታ አሸናፊዎች ነን። መቼም የትም በጠላቶቻችን ላይ የበላይ ነው የምንሆነው። አድዋ እንዴት መጣ? ዘመናዊ የጦር መሳሪያ የሌላት ድሀ አገር እንዴት ሀያላኖቹን አሸነፈች? ብለን ስንጠይቅ ‹በእግዚአብሄር በሚያምኑና እግዚአብሄርን በሚፈሩ ኢትዮጵያዊ ነፍሶች የመጣ ድል› የሚል መልስ እናገኛለን። ፈጣሪውን የሚፈራ ትውልድ፣ ፈጣሪውን የሚፈራ መሪ ለአገር የሚሆን ብዙ ነገር አለው።

ትውልድ እግዚአብሄርን ሲፈራ፣ መንግስት ፈጣሪን ሲፈራ ፈልጎ የሚያጣው አንዳች ነገር የለም። ተዐምር የሆነች አገር ላይ ተፈጥረን፣ በተዐምር ተከበን እየኖርን ተዐምር ያጣነው ከእግዚአብሄር ስለራቅን ነው ።

ሰው አእምሮና ልቡን ከተጠቀመ ተዐምር መስራት ይችላል። አይደለም ራሱን፣ አይደለም ቤተሰቡን፣ አይደለም አገሩን አለምን የመቀየር ሀይል ይኖረዋል። ግን አእምሮና ልባችንን በክፉ ሀሳብ አቆሽሸናቸዋል። ለራሳችንም ለሌላውም እንዳንሆን አድርገን የለውጥ ሀይላችንን በገዛ እጃችን ሽባ አድርገነዋል። እውነት ገብቶን የልብንና የአእምሮን ተፈጥሮ ብንመረምር አስደናቂ እውነትን እናገኛለን።

ልብ የፍቅር፣ የእውነት፣ የፍትህ ምልክት ነው። ልብ የይቅርታ፣ የተስፋና የቸርነት ማህጸን ነው። ልብ የናፍቆት፣ የራሮት፣ የደስታ አጥቢያ ነው። ልብ በደልን የመተው፣ ቅያሜን የመርሳት የስሜት ደሴት ነው። ልብ ሁሉን የማመን፣ ሁሉን ተስፋ የማድረግ ተፈጥሮ ነው። የደግነት፣ የጭካኔም ዙፋን ነው። የትላንትና የዛሬ የነገም ቀለም ነው። አዳፋና ውብ ታሪክ መከተቢያ ድርሳን.. የትላንት፣ የአሁንና የነገ፣ የዘላለምም ቀለም። ከሁሉ በላይ ሁሉን የሚችል የእግዚአብሄር ማደሪያ ነው።

ወደ አእምሮ ስንመጣ ተመሳሳይ ተፈጥሮ እናገኛለን። አእምሮ የህይወት ቋት ነው። መኖራችን፣ ራዕያችን፣ ህልማችን፣ ነጋችን ሳይቀር በአእምሮ የበላይነት ውስጥ የወደቁ ናቸው። መሄድ መምጣታችን፣ መግባት መውጣታችን፣ ስራችን፣ ትዳራችን፣ ቤተሰባችን፣ ታሪካችን ሁሉ በአእምሮ ስርዐት የሚተዳደር ነው።

> **እግዚአብሄርን መፍራትና ራስን ማወቅ በምድርና በሰማይ ክብርና ዋጋ የሚያሰጠን የጽድቅ መንገድ ነው። ነፍስ እግዚአብሄርን ስትፈራ መጀመሪያ የምታደርገው ኩነኔን መሸሽ ነው። ነፍስ እግዚአብሄርን ስትፈራ መጀመሪያ የምትማረው የጽድቅን ስራ ነው**

ፈጣሪ አምላክ ፈጥሮ እንደጨረሰን በነጻ ፍቃድ ለአእምሯችን ነው ያስረከበን። አእምሯችን የህይወታችን ፈላጭ ቆራጭ ህገ መንግስታችን ነው። የምንመራውና የምንተዳደረው በእሱ እውነት ስር ነው። እኛ ለአእምሯችን ህዝብ ነን። አእምሯችን ለእኛ መንግስት ነው። ይህ ማለት አእምሯችን እኛን፣ እኛም አእምሯችንን ማዘዝም ሆነ ማስገደድ እንችላለን ማለት ነው።

መንግስት የህዝብ ውጤት ነው። አእምሮም የእኛ ውጤት ነው። መንግስት ከህዝብ፣ በህዝብ፣ ለህዝብ ነው። አእምሮም ከእኛ በእኛ ለእኛ ነው። መንግስት በህዝብ ድምጽ እንደሚመራ ሁሉ አእምሮም ከእኛ በሚሰማው፣ እኛ በምንነግረው እኛን ይመራናል። አእምሮ የሚያስበው፣ አስቦም የሚተገብረው እኛ የምንነግረውን ነው። በራሱ የሚፈጥረው አንዳች እውነት የለውም። ጥላቻን ከነገርነው በጥላቻ መንፈስ ውስጥ ነው የሚያኖረን።

ፍቅርን ከነገርነው ደግሞ በፍቅር መንፈስ ውስጥ ነው የሚያኖረን። ህይወታችን እኛ ለአእምሯችን በምንነግረው ሀሳብ የተገነባ ነው። አሁን ላይ መልካም ህይወት ከሌለን ሀሳቦቻችንን መቆጣጠርና በበጎ መቀየር ይኖርብናል። አሁን ላይ አገራችን ላይ የአንድነት ሀሳብ፣ የአንድነት መንፈስ የጠፋው ትላንት ላይ በተነገረን የጥላቻ ወሬ ነው። አእምሮና ልብ ከሰው ልጆች ጋር በዚህ መንገድ ነው የተዋቀሩት።

እኔና እናንተ የአእምሯችን አበባዎች ነን.. አገራችን ደግሞ የእኛ ፍሬ። አገር የምትገነባው በዜጎቿ በጎ ሀሳብ ነው። የአንድ አገር ስልጣኔ፣ የአንድ ማህበረሰብ ዘመናዊነት ከሚረጋገጥባቸው መንገዶች ውስጥ ዋነኛው በሀሳብ መዘመን ነው። ዛሬ ላይ በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ አቅማቸው ክንዳቸውን ያፈረጠሙ ሀያላን አገራት የልዕልናቸው መነሻ ሀሳብ ነው። በሀሳብ ዘምነው፣ በእውቀት ከፍ ብለው፣ በምክንያታዊነት የተራመዱ ናቸው።

በሀሳብ የበላይነት ችግሮቻቸውን እያሸነፉ፣ ነውሮቻቸውን እየጣሉ ከምንምነት የተነሱ ናቸው። ፍቅርን የስርዐት ሁሉ ፍጻሜ አድርገው፣ በመነጋገርና በመቻቻል ጸንተው የቆሙ ናቸው። የብሄር ፖለቲካን ሽረው፣ ለሰውነት ከፍ ያለ ዋጋ ሰጥተው፣ ለለውጥ በበረቱ፣ ለስኬት በተጉ ተስፈኛ ልቦች መከራቸውን የተሻገሩ ናቸው። እኛም ፍቅርን በዋጀ የወንድማማችነት መንፈስ አገራችንን ማሻገር አለብን። በሀሳብ እጦት፣ መነጋገር ባለመቻል ያጣናቸው በርካታ ነገሮች አሉ። በእልህና በማን አለብኝነት ታሪክ አበላሽተን እናውቃለን። እያማጥን እስከመች እንቆያለን?

ጊዜው ያለፈ ያልተወለደ ሰላም እያማጥን በመከራ መኖር የለብንም። ሰላምን አምጠን መውለድ አለብን። አንድነትን አምጠን መውለድ አለብን። ወንድማማችነትን እሹሩሩ ብለን ማሳደግ አለብን። ፍቅርን ለአለም ያስተማረች አገር የፍቅር መልክ ጠፍቷት ስትሰቃይ ማየት ያማል። ሰላምን ለምድር ያስተዋወቀ ህዝብ ሰላም ጠፍቶት ሲኅሳቆል ማየት ያማል። በልጆቿ ፍቅር አንድነትን አምጣ የወለደች ጦጵያ፣ ኢትዮጵያዊነትን ወልዳ ያሳደገች አቢሲኒያ ዛሬ ላይ እኚህ ሁሉ ርቀዋት በምንምነት ውስጥ ማጎንበሷ ያማል።

የእኛ ሰላም መች ነው የሚወለደው? ቆይ የኢትዮጵያ አንድነት መች ነው የሚመለሰው? አገሬ አገር ወልዳ በልጆቿ የአንድነት ክንድ ላይ መች ይሆን የምትታረሰው? ይሄ ጊዜ ናፍቆኛል። እርግጠኛ ነኝ እናንተም ናፍቋችኋል። ታዲያ ከናፈቀኝና ከናፈቃችሁ በጋራ ሀሳብ የጋራ አገር መገንባት ለምን ተሳነን? እንቃ.. አሁኑኑ ለለውጥና ለእድሳት እንነሳ። ሀሳቦቻችንን በበጎ አክመን፣ በአእምሯችን ሀይል አገር ለመፍጠር ትክክለኛ ጊዜ ላይ ነን። ስልጣኔአችንን የሰወርነው ራሳችን ነን። እድገታችንን፣ ከፍታችንን የሸሸግነው እኛው ነን። አለም በሀሳብ ሲዘምን እኛ በሀሳብ እየተገፋፋን፣ አለም የጋራ ታሪክ ሲፈጥር እኛ የብቻ ታሪክ እየሰራን አገራችንን አቆርቁዘናት ኖረናል። አሁን ግን ይብቃን..

ህይወት ከማሰብ እንደሚጀምር ሁሉ ማብቂያውም የሀሳብ እተት ነው። አገር በማሰብ ነው የምትቆመው። አገሩን በሀሳብና በፍቅር ያላቆመ መንግስትና ህዝብ የታሪክ ተወቃሽ ከመሆን አያመልጥም። የሰው ልጅ አስቦ ወደ ፊት ካልተራመደ፣ ተምሮ ራሱንም ሆነ ሌላውን ካልወጠ ዋጋ የለውም። እኛ አገር እየተስተዋለ ያለው ይሄ ነው። ብዙ እውቀት፣ ብዙ ድግሪ ይዘው አገር ከመለወጥ ይልቅ ነውጥ ፈጣሪ ሆነው የቆሙ ብዙ ናቸው። ከስማቸው በፊት ብዙ ክብርና ማዕረግ ይዘው አገር ለማፍረስ ረፍት ያጡ እልፍ ናቸው።

አባት ሆነው ልጆቻቸውን የሚደፍሩ፣ ወንድም ሆነው እህቶቻቸውን የሚያስነውሩ፣ በወንድነታቸው የሴት እህቶቻቸውን ክብር ዝቅ የሚያደርጉ ብዙ ናቸው። አገራችን የተወረረችው በነዚህ አይነት ኃላፊነት በማይሰማቸው ሰዎች ነው። እነኚህ ሰዎች ከነውር በቀር ለክብር የሚሆን አንዳች እውቀት የላቸውም። በአደባባይ ስለአገራቸው እየተናገሩ በስውር አገራቸውን የሚያፈርሱ ናቸው። ከሂሳብና ከእንግሊዝኛ እውቀት ሌላ ከአእምሯቸው ተርፎ ወደ ልባቸው የሚሄድ፣ ከልባቸውም ዘልቆ ወደ ማህበረሰቡ የሚፈስ የእውቀት ባህር የሌላቸው ናቸው።

በራስ ወዳድነት ተፈጥረው በራስ ወዳድነት የጎለመሱ የአገር ጠላቶች ናቸው። ራሳቸውን ፈጥረው ራሳቸውን ያሳደጉ የራሳቸው አብራኮች ናቸው። ጊዜ የማያሰማን የለም..በፊት መሀይም ማለት ማንበብና መጻፍ የማይችል ነበር አሁን ላይ መሀይም የተማረው ሆኗል። ድግሪና ማስተርስ ያለው፣ ዶክተርና ፕሮፌሰሩ ነው። ከትላንት እስከዛሬ አገር እያፈረሱ ያሉት በእውቀት የተካኑት ምህራን ናቸው።

ኢትዮጵያ አገራችን ዛሬም ድረስ ታፍራና ተከብራ የኖረችው ማንበብና መጻፍ በማይችለው መሀይም የማህበረሰብ ክፍሎች ነው። ፍቅርን የሚያውቁ፤ ተከባብሮና ተቃቅፎ መኖርን የተካኑ፤ ለባህልና ወጋቸው ያደሩ እነሱ ናቸው። ከዘር፣ ከብሄር፣ ከቋንቋ ከሀይማኖት በላይ ሆነው አገር ያጸኑ እነሱ ናቸው። ትህትናና አክብሮት ስፍራቸው ማንበብና መጻፍ ከማይችለው ከባላገሩ ቤት ነው።

በኢትዮጵያዊነት ወግ ዝቅ ብሎ ተረከዝ የሚይዝ እሱ ነው። ኢትዮጵያ ከነመልኳ፣ ከነወዟ፣ ከነታሪኳ የቆመችው በእሱ ነው..በመሀይሙ ባላገር። እኔና እናንተ የሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ስልጡን የአገራዊ ችግርና ሥጋት ምንጮች ነን። እውቀታችንን ለነውጥ ሳይሆን ለለውጥ እንጠቀም።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የግብርና ሜካናይዜሽን ለመዋቅራዊ የኢኮኖሚ ሽግግር

አንተነህ ቸሬ

የኢትዮጵያ መንግስት የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በዚህም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት የሚያስችሉ በርካታ ተግባራት ሲከናውን ቆይቷል። በዚህም የግብርና ምርምር ተቋማት፣ የህብረት ስራ ማህበራት፣ እና የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት እንዲሁም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጭምር ርብርብ ያደረጉ ሲሆን፣ ይህን ተከትሎም የአገሪቱን ምጣኔ ሀብት ያሳደጉና የሕዝቡን፣ በተለይም የአርሶ አደሩን ሕይወት ያሻሻሉ ውጤቶች ተመዝግበዋል። ከግብርና የሚገኘው ምርት በየዓመቱ ጭማሬ አሳይቷል፤ እንደ ሀገር የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥም ተችሏል፤ የአርሶ አደሩ ህይወት መቀየር ጀምሯል፤ በርካታ አርሶ አደሮችም ወደ ኢንቨስተርነት የገቡበት ሁኔታ ታይቷል።

ይሁን እንጂ እነዚህ ተግባራት ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ ካላት አቅም አንፃር ሲመዘኑ ለሀገሪቱ የምግብ ዋስትና፣ የስራ እድል ፈጠራና የምጣኔ ሀብት እድገትም ሆነ ለዘርፉ ችግሮች አስተማማኝ መፍትሄ የሰጡ አይደሉም። አሁንም ግብርናውን ኋላ ቀር የአስተራረስ ዘዴን ነው እየተከተለ ያለው፤ ከዝናብ ጥገኝነት መለቅቅ አልተቻለም፤ አርሶ አደሩ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ከመጠቀም የራቀ ሆኖ ቆይቷል። በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ አልተቻለም፤ ሚሊዮኖች ከድህነት ወለል በታች እየኖሩ ነው።

እንደ ሀገር ተግባራዊ ተደርገው በነበሩት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዶች የሀገሪቱም ኢኮኖሚ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ማሸጋገር አልተቻለም። አሁንም ኢኮኖሚውን እየመራ ያለው ግብርናው ነው። እናም የምጣኔ ሀብት መዋቅራዊ ለውጥን እውን ማድረግ አልተቻለም።

የግብርናውን ዘርፍ በማሳደግ ሀገሪቱ የግብርና አቅሟን በመጠቀም ከድህነት እንድትላቀቅ ለማድረግ ከሚቀርቡ ምክር ሃሳቦች መካከል አንዱ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ነው። ከአምስት ዓመታት በፊት የተቋቋመው የግብርና ሚኒስቴር የግብርና ሜካናይዜሽን ዳይሬክቶሬት የግብርና ሜካናይዜሽን እንዲስፋፋና ምርታማነት እንዲጨምር በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ሜካናይዜሽን ዳይሬክተር አቶ በረከት ፍርሲዶ በኢትዮጵያ ስላለው የግብርና ሜካናይዜሽን እንቅስቃሴና ስለዘርፉ የወደፊት ተግባራት በተለይ ለ‹‹አዲስ ዘመን›› ጋዜጣ የሰጡትን ማብራሪያ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

### የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ

የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ፣ ሜካኒካል ወይም ኤሌክትሮ ሜካኒካል የሆኑ ቴክኖሎጂዎች የሰውና የእንስሳት ጉልበትን በመተካት ወይንም በመደገፍ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል አሰራር ነው። አሰራሩ ከተለያዩ የኃይል ምንጮች የሚገኙ ቴክኖሎጂዎች በግብርና ልማት ላይ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚተገበሩበት የቴክኖሎጂ ግብዓት ነው። የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች የመስኖ ልማትና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራዎች፣ የእንስሳትና ሰብል ልማት እንዲሁም ሌሎች የግብርና ተግባራት ከአየር ንብረትና ከተፈጥሮ ሀብት ጋር ተስማሚ ሆነው ምርታማነታቸው እንዲጨምር የሚያስችሉ ናቸው።

ከእነዚህ ቴክኖሎጂዎች መካከል አንዳንዶቹ የሰው ኃይልና የእንስሳትን ጉልበት ተክተው የሚሰሩ ሲሆኑ፤ ሌሎቹ ደግሞ ከሰው እና ከእንስሳት ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩ ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ የዘመኑ ቴክኖሎጂ ያፈራቸውና ያለሰው ኃይል ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ (Unmanned) የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችም አሉ።

### የግብርና ሜካናይዜሽን በኢትዮጵያ

የግብርና ሜካናይዜሽን ትግበራን ውጤታማ የሚያደርጉና በግብርና ሜካናይዜሽን ስትራቴጂ ውስጥ የተቀመጡ መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ የጥናትና ምርምር ማዕከል እንዲጠናከር ተደርጓል። የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂው ለአርሶ አደሩ ተደራሽ እንዲሆን የሚያስችሉ መዋቅሮች ተዘርግተዋል። የቴክኖሎጂው ተቀባይነትና የአፈፃፀም ደረጃ ግን በየክልሎቹ የተለያየ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ገና ታዳጊ ነው። ሀገሪቱ ውስጥ በአብዛኛው ጥቅም ላይ እየዋሉ ካሉት የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች መካከል ለመሬት ዝግጅት (ከመጀመሪያ እርሻ እስከ ዘር መዝራት ድረስ) የሚውለው



በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ስምንት ሺ ትራክተሮች በስራ ላይ ይገኛሉ

ትራክተር አንዱ ነው። በትራክተር የፊትና የኋላ የመቆጣጠሪያ ክፍሎች ላይ በመገጠም የሚከናወኑ የእርሻ ኮንስትራክሽን ስራዎች፣ ማለትም የመስኖ ቦዮችና ጉድጓዶች ቁፋሮ እንዲሁም የመኖ ማጓጓዝ ተግባራትም በአሁኑ ወቅት እየተለመዱ መጥተዋል። በትራክተር ላይ በተገጠሙ የውሃ ፓምፖች ውሃን ከወንዝ የመሳብ ቴክኖሎጂም በዚህ ረገድ ይጠቀሳል።

መጠናቸው እንደየትራክተሮቹ የፈረስ ጉልበት የሚወሰን በትራክተር ላይ የሚገጠሙ መውቂያ ማሽኖችም አሉ። ሁለገብ የመውቂያ መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ አምራቾችም እየተመረቱ ነው። እነዚህ ሁሉ መሳሪያዎች ከትራክተር ጋር እንዲገናኙ ተደርገውና ትራክተሩ የኃይል ምንጭ ሆኗቸው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

የእርሻ፣ አረም፣ አጨዳና ውቂያ ተግባራት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወኑት በሰው ኃይልና በእንስሳት ጉልበት ነው። የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በመሆን ብዙ የሰውና የእንስሳት ጉልበት እንዲሁም ረጅም ጊዜ ይፈጅ የነበረውን ስራ በአጭር ጊዜ ማከናወን ተጀምሯል። ለምሳሌ ሁለገብ መውቂያ ማሽኖች በሰዓት እስከ 20 ኩንታል እህል መውቃት ይችላሉ፤ ለበቆሎ መፈልፈያ ከሆነ ደግሞ በሰዓት ከ40 እስከ 60 ኩንታል መውቃት ይችላሉ። እነዚህ ማሽኖች ምርቱ አፈር ሳይነካውና ሳይባክን ወደ ማጠራቀሚያ በቀጥታ እንዲከማች ማድረግ ያስችላሉ።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የእነዚህ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም እየጨመረ መጥቷል። በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት፣ በግብርና ሚኒስቴርና በአጋር አካላት ትብብር፣ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች በስፋት መተዋወቅና አገልግሎት ላይ መዋል ችለዋል።

ቴክኖሎጂዎቹ ከመገዛታቸው በፊት ተለይተው ለናሙና የቀረቡት ውጤታማነታቸው እንዲፈተሽ ይደረጋል። ቴክኖሎጂዎቹን ለማስተዋወቅ በተደረገው ጥረት አርሶ አደሩ የቴክኖሎጂዎቹን አስፈላጊነትና ለምርት መጨመር ያላቸውን አበርክቶ በመገንዘቡ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ባህሉ እያደገ መጥቷል።

የኢትዮጵያ የዘር ወቅቶች የተለያዩ በመሆናቸው ትራክተሮቹን በተለያዩ አካባቢዎች እያዘዋወሩ የመጠቀም ተግባር እየተስፋፋ ነው። ይህም የግብርና ሜካናይዜሽን ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ቁጥር እንዲጨምር አድርጓል። የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ በመፈቀዱ በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ቁጥር ጨምሯል።

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ውስጥ ስምንት ሺ ትራክተሮች በስራ ላይ ይገኛሉ። ከሰባት ሚሊዮን በላይ አርሶ አደሮች በተለያዩ የግብርና ሜካናይዜሽን ዘርፎች ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። በአስር ዓመቱ ሀገራዊ የልማት እቅድ ላይ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ቁጥሩን በመጀመሪያው አምስት አመት ማጠናቀቂያ ላይ ወደ 50 በመቶ፣ በሁለተኛው አምስት ዓመት ማጠናቀቂያ ላይ ደግሞ ወደ 70 በመቶ ለማሳደግ እቅድ ተይዟል። ይህን ለማሳካት ደግሞ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በጥምረት መስራት ያስፈልጋል።

### የግብርና ትራንስፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎች ጥራት

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎቹ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ መሟላት ያለባቸው ግብዓቶች አሉ። የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲሁም የጥገናና የምህንድስና ባለሙያዎችን ጨምሮ ሌሎች የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ያስፈልጋሉ። በስራ ላይ ያሉት ትራክተሮች ቢያንስ በሁለት ፈረቃ እንዲሰሩ ለማድረግ 16ሺ ኦፕሬተሮች ያስፈልጋሉ፤በተጨማሪም ረዳቶችና የጥገና ስራ የሚሰሩ ባለሙያዎችም ያስፈልጋሉ። ይህም የዘርፉ የሰው ኃይል ፍላጎት ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል።

ፍላጎቱን ለማሟላትም የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ። ለአብነት ያህል በአላጌ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ የጥገናና ኦፕሬሽን ሙያ ትምህርት ክፍል ተቋቁሞ የጥገና ባለሙያዎችና ማሽን ኦፕሬተሮች እየሰለጠኑ ነው፤እስካሁን ድረስ ሦስተኛ ዙር ሰልጣኞች ተመርቀዋል። ስልጠናውን በሌሎች አካባቢዎችም ለማስፋት ጥረት እየተደረገ ነው።

ከሰው ሀብት ልማቱ በተጨማሪ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚመረቱት ማሽኖች ጥራት ጉዳይም ትኩረት ይፈልጋል። ጥራታቸውን ያልጠበቁ ማሽኖች ገብተው አርሶ አደሩም ሆነ ሀገሪቱ እንዳይጎዱ ለማድረግ ግብርና ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር በመተባበር ለ250 የግብርና ሚካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ደረጃ (Standard) አውጥቷል። እነዚህ ደረጃዎች ማሽኖቹ ከተቀመጠው የጥራት ደረጃ ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጫ ይሰጣሉ።

ይሁን እንጂ ደረጃውን በተግባር ለመፈተን የሚያስችል የመፈተሻ ቴክኖሎጂ እጥረት ስላለ ከደቡብ ኮሪያ መንግሥት ጋር በመተባበር የግብርና ሜካናይዜሽን የልኅቀት ማዕከልን ለማቋቋም እየተሰራ ነው። ግንባታውም በቅርቡ ይጀመራል። በማዕከሉ ውስጥ የሚሰሩ የጥራት ፍተሻ ባለሙያዎች (Test Engineers) ስልጠና ስለሚያስፈልጋቸው ስልጠናውን ለመስጠት ከአዲስ አበባ እና ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የመግባቢያ ስምምነቶችን ለመፈራረም ዝግጅቶች ተጠናቀዋል። ከፌደራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ጋርም በትብብር ለመስራት የመግባቢያ ስምምነት ተፈርሟል። ስለሆነም ማዕከሉ ተገንብቶ ሲጠናቀቅ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚመረቱት ማሽኖች ጥራታቸው በባለሙያዎች እየተፈተሸ ወደ ተጠቃሚው ይደርሳሉ ማለት ነው።

የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን በሀገር ውስጥ ለማምረት የሚደረገው ጥረት መሻሻሎችን እያሳየ ነው። በሞተር ኃይል የሚሰሩ የመውቂያ መሳሪያዎች፣ የበቆሎና የለውዝ መፈልፈያዎች እና የማጓጓዣ ጋሪዎች በሀገር ውስጥ ከሚመረቱት መካከል ይጠቀሳሉ። በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ተሰማርተው ያመርቱ የነበሩ አምራቾች ባገኙት ስልጠና ከውጭ ይገቡ የነበሩ ሁለገብ የመውቂያ መሳሪያዎችንና የለውዝ መፈልፈያ ማሽኖችን ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አስማምተው ማምረት ችለዋል። ማሽኖቹን ለአርሶ አደሩ በማስተዋወቅና የገበያ ትስስር እንዲፈጠር በማድረግም አርሶ አደሩ መሳሪያዎቹን ገዝቶ እንዲጠቀም ማድረግ ተችሏል። ይህ ስራ ጥሩ ውጤት ማስገኘቱን ተከትሎ ባለሀብቶች በዚህ ዘርፍ ተሰማርተው ማምረት ጀምረዋል።

የግብዓቶችን ጥራት ለመጠበቅ የግብርና ማሽኖች አስመጪዎችን አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ የሚያስገቡ መመሪያዎች እንዲወጡ ተደርጓል። መመሪያዎቹ አስመጪዎች ላስገቧቸው ማሽኖች ለተወሰኑ ዓመታት መለዋወጫዎችን እንዲያቀርቡና የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ የሚያደርጉ ናቸው።

ከደቡብ ኮሪያ መንግሥት ጋር በትብብር የሚቋቋመው የግብርና ሜካናይዜሽን የልኅቀት ማዕከል ከሚያከናውናቸው የፍተሻና የጥራት ማረጋገጫ ተግባራት በተጨማሪ ከውጭ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎች በሀገር ውስጥ ሊመረቱ የሚችሉበትን ክህሎት ለመፍጠር እገዛ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል። ከዩኒቨርሲቲ የሚወጡ ምሩቃንና ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ ባለሙያዎች እንዲሁም በማምረቻ ዘርፎች የተሰማሩ ባለሙያዎች በዚህ የክህሎት ማዳበር ስልጠና ተካፋይ ይሆናሉ። ከዚህ ቀደም የነበሩና በአሁኑ ወቅት ብዙም እንቅስቃሴ የሌላቸው የምርት ማሻሻያ ተቋማትም በዚህ አሰራር እንዲነቃቁ ጥረት ይደረጋል።

### የግብርና ሜካናይዜሽን ያስገኛቸው ውጤቶች

በአጠቃላይ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ትግበራ የግብርና ስራው በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን፣ ምርት እንዲጨምርና የሀብት ብክነት እንዲቀንስ አድርጓል። የግብርናው ዘርፍ በሰለጠኑ ባለሙያዎች የታገዘ እንዲሆንም እድል ፈጥሯል። የዘርፉ ፍላጎት እያደገ በመምጣቱ ብዙ ባለሙያዎችና ተቋማት የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን በማምረት ላይ እንዲሰማሩ አስችሏል። አርሶ አደሩ ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ምርቱን ማሳደግን ቅንጦት ሳይሆን አስገዳጅና አስፈላጊ እንደሆነ በመረዳቱ ለግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ያለው ፍላጎት ጨምሯል።

### እቅዶች

በቀጣይ ጊዜያት የሰብልና እንስሳት ልማትን አቀናጅቶ በመስራት ምርታማነትን የሚጨምሩ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ለማስተዋወቅና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል። በሜካናይዜሽን በመታገዝ የወተት፣ የስጋና የዶሮ ሀብት ልማትን ማሳደግም ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ነው። ትልቅ የግብርና አቅም ያላቸው ቆላማ አካባቢዎችም የሜካናይዜሽን ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል።

የግብርና ሜካናይዜሽን ትግበራ መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን ለማሳካት ቁልፍ ሚና እንዳለው በመገንዘብ አርሶ አደሮችን ስለቴክኖሎጂው ማሳወቅ፤ ባለሀብቶችም በዚሁ ዘርፍ እንዲሰማሩ ማድረግ እንደሚገባና ግብርና ሚኒስቴርም ድጋፍ እንደሚያደርግ አቶ በረከት ፍርሲዶ ገልጸዋል።

ማህበራዊ
# አስኳላ

# ትምህርትን ከጥራቱ ጋር ያገናኛል የተባለለት ራስ ገዝነት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**



አውሮፓውያን በዩኒቨርሲቲዎች የራስ ገዝ አስተዳደር ላይ ብዙ ሠርተዋል። እ.ኤ.አ. በ2009 ባወጡት መረጃም የራስ ገዝ አስተዳደርን አንድ ላይ ሰብስበው የአገራትን የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓቶች በአራት ዘርፎች ከፍለው እስከማስቀመጥም ደርሰዋል።

ዘርፎቹ በድርጅታዊ፣ በገንዘብ፣ በሰራተኞች እና በትምህርት የሚሉ ሲሆኑ፤ ከእነዚህም ውስጥ መቶ በመቶ ከመንግስት ቁጥጥር ነፃ የሆኑት አሸናፊ መሆናቸውን አትቷል። በአገሮች መካከልም ሆነ በአገር ውስጥ ሊለያዩ እንደሚችሉም አመላክቷል።

ሁኔታው ከውጭ የገንዘብ ድጋፍ ከመሳብ ችሎታ አንጻር ሲታይ ከገንዘብ ገዝ አስተዳደር ጋር ያስተሳስሩታል። ከፍተኛ የሰራተኞችን የመሳብ ችሎታን ሲያነሳ ደግሞ ደመወዝን ከማቀናበር ጋር ያይዘዋል። ለምሳሌ በዚህ ሪፖርት ካስቀመጣቸው መካከል ፈረንሣይ አንዷ ነች። የዩኒቨርሲቲ ሥርዓቷ የተማሪዎችን የመምረጥ፣ ሥርዓተ-ትምህርቶችን የማዘጋጀት እና የተማሪ ቁጥሮችን የመያዝ ችሎታን የሚያካትተው ትምህርታዊ የራስ ገዝነት አስተዳደሯ ሁኔታ ከማንኛውም አገር በጣም ዝቅተኛ ነው። ሆኖም በገንዘብ ራስ ገዝ አስተዳደር ረገድ የሚደርስባት የለም።

እንደውም እ.ኤ.አ. በ2011 የተደረገው ማሻሻያ የተወሰኑ የራሳቸውን ሕንፃዎች ሊገዙ እንደሚችሉ ሪፖርቱ ያሳያል። ከዚህ አንጻር ግሪክ በአራቱም ደረጃዎች ዝቅተኛ ስትሆን ዩናይትድ ኪንግደም በተከታታይ በከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ መረጃውም አስቀምጧል። ይህንን የአውሮፓን ተሞክሮ ያነሳነው ያለምክንያት አይደለም። ራስ ገዝነት በምን መስክ ያሻግራል የሚለውን ከዩኒቨርሲቲዎች አንጻር ለመዳሰስ ስለወደድን ነው። በቅርቡ ውይይት የተደረገበት የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝነት ደግሞ መነሻችን ነው።

የሌሎች ተሞክሮ ምን ይመስላል የሚለውን በማንሳትም የተጀመረው ነገር እኛን እንዴት ያሻግረናል የሚለውንም የሚመለከታቸው አካላትን ስላነጋገርን ብዙ መረጃ እንድንጨብጥበትም ያደርገናል። በተለይም እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ምን አይነት እንደሆነና እንዴት ልንጠቀምበት እንደሚገባ ከባለሙያዎቹ ሀሳብ ብዙ እናገኛለንም።

ራስ ገዝነትን በተመለከተ ትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የተጀመሩ ሥራዎች ላይ የጋራ መግባባት ለመፍጠር በ2014 ዓ.ም አዲስ ከተመደቡ የዩኒቨርሲቲ የቦርድ አባላት እና ፕሬዚዳንቶች ጋር ውይይት አድርጓል።

በውይይቱ ወቅት የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንዳሉት፤ በትምህርት ስርዓቱ ላይ የሚስተዋለውን የጥራት ችግር ለመፍታት የተጀመሩ የሪፎርም ሥራዎች አሉ። አንዱና ዋነኛው ደግሞ ዩኒቨርሲቲዎችን ራስ ገዝ ማድረግ ነው። በአሁን ወቅት በአገራችን 47 የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ይገኛሉ። ይሁን እንጂ የትምህርት ጥራት ጉዳይ አጠያያቂ ደረጃ ላይ ነው። በመሆኑም በየደረጃው እየታዩ ራስ ገዝነታቸውን በማረጋገጥ ትምህርት ተኮር ሥራ እንዲሰሩ ይደረጋል።

የትምህርት ጥራትን ከማረጋገጥ አኳያ ከሁሉም በላይ ዩኒቨርሲቲዎችን ነጻ ሆነው መስራት አለባቸው የሚሉት ፕሮፌሰሩ፤ ጅማሮው በአንድ ዩኒቨርሲቲ ላይ ይከናወናል። ምክንያቱም ሁሉም ላይ ከተደረገ አደጋው ሊከፋ ይችላል። እናም በቅርብና ብዙ ነገሮች የተሟሉለት ዩኒቨርሲቲ ተመርጦ የተቀመረው ተሞክሮ በአገርኛ እሳቤ እንዲተገበር ይደረጋል። ለዚህ ደግሞ ተመራጩ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሆኗል። በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው ላይ በመቶ ቀናት ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል። ችግሮች እየታረሙም ወደ ሌሎቹ ዩኒቨርሲቲዎች ይቀጥላል ብለዋል።

ራስ ገዝ መሆናቸው በዋናነት የሚጠቅማቸው ከፖለቲካ ተጽዕኖ ተላቀው ሥራቸውን በነጻነት እንዲሰሩ፤ የትምህርት ተቋማት የእውቀት ማዕከላት ናቸውናም የፖለቲካ አጀንዳ ማስፈፀሚያዎች እንዳይሆኑ ነው። ልዩ ትኩረታቸው ትምህርት ብቻ እንዲሆንም ያደርጋቸዋል። በተለይም ዛሬ ላይ ላለው አገራዊ ሁኔታ ይህ የሚመጥን ሥራ እንደሚሆን አያጠያይቅም። ስለዚህም ከማንኛውም ተጽእኖ ነጻ የሆኑ ብቁ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ምሁራን መፍለቂያ እንዲሆኑ ይሰራል፤ አሁንም ብዙ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ መሆናቸውን አንስተዋል።

ራስ ገዝነት በብዙ መልኩ ሊተነተን ይችላል። በአብዛኛው ግን በአስተዳደርና በኢኮኖሚ ራስን ማስተዳደር እንዲሁም ከማንኛውም የፖለቲካዊ ተጽኖ መላቀቅ ነው ተብሎ ይታመናል ያሉት ሚኒስትሩ፤ የራስ ገዝ አስተዳደር ሉዓላዊነት፣ ራስን በራስ ማስተዳደር፣ ነፃነት እና ኃይል ማሰባሰብ በሚለው ውስጥ ተካቶ የሚሰራበት ነው። ስለዚህም ራስ ገዝነት ውሳኔዎችን የማድረግ እና ከራስ ጋር በሚዛመዱ ጉዳዮች ላይ እርምጃ የመውሰድ ችሎታ ማግኘት ነው። የራሱ ደንቦችን እና የአስተዳደር አካላትን ለማቋቋም የሚቻልበትም ነውና ይህ እውን እንዲሆንም ያላሰለሰ ጥረት እንደሚደረግም ይናገራሉ።

የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ በበኩላቸው እንዳሉት፤ ትምህርት ሚኒስቴር እንደ አዲስ ከተደራጀ በኋላ አዲስ የሥራ አመራር ቦርድ መድቦ እየሰራ ነው። ይህ ቦርድ ደግሞ ከሚሰራቸው ጉዳዮች አንዱ ዩኒቨርሲቲዎችን ነጻና ገለልተኛ ማድረግ ነው። ለዚህም ይበጃል ያለውን አሰራር ቀምሮ ራስገዝነትን ለመጀመር ውሳኔ ላይ ደርሷል። ብዙ እንቅስቃሴዎችም በመደረግ ላይ ናቸው። ሥራው የትምህርት ጥራትን ከማረጋገጡ ባሻገር በርካታ ጠቀሜታዎችን ለአገር የሚያድልም እንደሆነ ታምኖበታል።

ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ እንዲሆኑ መደረጉ በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የገለጹት ዶክተር ሳሙኤል፤ የትምህርት ጥራት ላይ አተኩረው ውጤታማ እንዲሆኑ፣ የተሻለ የሠው ኃይል እንዲያፈሩ፣ ጥራት ያለው ምርምር እንዲያደርጉ እና በሀብት አጠቃቀም ውጤታማ እንዲሆኑ ከማስቻሉም በላይ ለአገሪቱ የሀብት ምንጭ እንዲሆኑም እድል ይሰጣል። በተጨማሪም የኢትዮጵያን ታላቅ አገርነት በማረጋገጥ በአፍሪካ ደረጃ ብቻም ሳይሆን በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ ያደርጋታል። ምክንያቱም የሚወዳደሩ ዩኒቨርሲቲዎች ይበራከታሉና ነው ብለዋል።

ተመራማሪና ተግባሪ ምሁራን እንዲፈጠሩም እድል ይሰጣል። ይህ ደግሞ አገሪቱ እድገቷን እንድታፋጥን ከሚያስችላት መካከል ግንባር ቀደሙን የሚይዝ ነው። ስለዚህም ዩኒቨርሲቲዎች ነጻ ማድረጉ ላይ በስፋት ይሰራል። በእርግጥ ነጻ ሲባል ገደቦች ይኖሩታል። የመጀመሪያው ከአገር ህግና ደንብ መውጣት አለመቻል ነው። ይህንን እስከተከተሉ ድረስ ጫና ሳይበዛባቸው የእውቀት ማዕከልነታቸውን ያረጋግጣሉም ብለዋል።

እንደ ዶክተር ሳሙኤል ገለጻ፤ ይህንን ለማድረግ ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች ያስፈልጋሉ። አንደኛው ሀብት ሲሆን፤ ይህንን ሀብት በመንግሥት ብቻ ማምጣት የማይቻል በመሆኑ ሀብት እንዲያመነጩ እና ያላቸውን ሀብት በውጤታማነት እንዲቀጥሉ ያደርጋቸዋል። ሁለተኛው የተሻለ ሠው እንዲሰባሰብ ያደርጋሉ። በዚህ ደግሞ ጥራት ላይ እስከታችኛው እርከን ድረስ መድረስ ይችላሉ። የተሻለ መምህር መቅጠር፣ የተሻለ ተማሪ ማስገባትና ሰራተኞች ቀልጣፋ ሆነው በሁሉም ሁኔታ ተመራጭ እንዲሆኑም ያስችላቸዋል። ሦስተኛው ምቹ የአመራር ሥርዓት መኖር ሲሆን፤ አሁን አገር ያለችበትን የአሰራር ግድፈት በብዙ መልኩ ያስተካክለዋል። በተለይም በአቅምና በእውቀት የሚሰራ ትውልድን ከመፍጠር አኳያ የማይተካ ሚና ይኖረዋል። ከስነምግባርና አገር ወዳድነት አኳያም እንዲሁ ትልቅ አቅም ይፈጠርላቸዋል። ራስ ገዝ መሆን ዩኒቨርሲቲዎች ከሙስናና እና ከሀብት ብክነት እንዲድኑም ያደርጋቸዋል።

ዶክተሩ እንደሚሉት፤ ምቹ የራስ አስተዳደር እና ራስ ገዝነት ካለ እንዲሁም ጥሩ የሚባል ሀብት ከተገኘ በዓለም ደረጃ ጠንካራ ተቋማትን መገንባት ይቻላል። ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ ይህንን እድል ካገኙ ብዙ ነገራቸውን እንደሚለውጡ እሙን ነው። እናም በቅርብ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ምቹ የሆነው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዚህ ተመራጭ ሆኖ ይተገበርበታል። በዚያ ላይ ዩኒቨርሲቲው የ71 ዓመታት ተሞክሮ ያለው ነውና እርሱን በመጠቀም ብዙ ነገሮቻችንን ያሻግራል።

ዩኒቨርሲቲውን ራስ ገዝ እንዲሆን የፖለቲካ ውሳኔ ከተወሰነ በኋላም ቢሆን በውስጥ ያሉ ዝግጅቶች ምንድናቸው የሚለውን ከማየት አልፎ በአሁን ወቅት የዝግጅቱ ማጠናቀቂያ ላይ ደርሰናል ያሉት ዶክተር ሳሙኤል፤ በሚቀጥሉት ሁለት ወራት ውስጥ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ እንዲሆን ለማድረግ ጥረቶች እየተደረጉ መሆናቸውን ጠቁመዋል። በሁለት ዓመታት ውስጥም ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ እንደሆኑ ይደረጋሉ ብለዋል።

ለዩኒቨርሲቲዎች ራስገዝነት ሲሰጥ ያለምክንያት አይደለም። ምክንያቱ አንድና አንድ ነው። በትምህርት ተፈጥሮ ሕጎች ተመርተው ውጤታማ እንደሚሆኑ ማስቻል ሲሆን፤ በሕጋቸው ማዕቀፍ ውስጥ የራሳቸው ሕግጋት አውጥተው፤ ባለስልጣኖቻቸውን ሾመው፣ እቅዶቻቸውን እና ፕሮግራሞቻቸውን በትምህርት ነፃነት መርሆዎች ውስጥ ወስነው እንዲሰሩ ማድረግም ነው። በተለይም የምርምር ነጻነት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር የማይተካ ሚና እንደሚኖራቸው ይናገራሉ።

እንደ ዶክተር ሳሙኤል ማብራሪያ፤ ዩኒቨርሲቲዎች ንብረታቸውን በነጻነት የማስተዳደር ስልጣን ይኖራቸዋል። ለባለስልጣናት፣ ለመምህራን፣ ለተማሪዎች እና ለአስተዳደር ሰራተኞች መብቶችንና እውቅና ይሰጣልም። ለምሳሌ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ራስ ገዝ ብናደርገው የራሱን ችሎታ እና ሀብቶች በመጠቀም የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴን የመወሰን እና የማከናወን ችሎታውን እንዲያሳድግ እድል ይሰጠዋል። ተግባራትን እና አካባቢን በማጣጣም እና ድጋፎችን በመጠቀም ያለማንም አስተዋሽነትና አዛዥነት እንዲሰራም ያደርገዋል።

ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ ሲሆኑ ሌላም የሚጠቀሙበት ነገር እንዳለ የሚያነሱት ዶክተር ሳሙኤል፤ ዩኒቨርሲቲዎች የውጪው ፖለቲካ መጥቶ እንዳያተራምሳቸው ይሆናሉ። በራሳቸው ተሟግተውና የሀሳብ ፍጭትን አድርገው የተለያዩ ውሳኔዎችን እንዲያስተላልፉም በር ይከፍትላቸዋል። የራሳቸው ሕግና ደንብ ያላቸው ስለሚሆኑ እንደስከዛሬው በብሔርና በሀይማኖት የሚጨፋጨፉበት ምክንያት አይኖርም። በቀላሉ ማንንም ሳያስፈቅዱ በአወጡት ሕግ መዳዝ እንዲችሉ ያደርጋቸዋል። ግባቸው መወዳደር ሳይሆን ማሸነፍን ያደርጋሉም ይላሉ። ለዚህ ደግሞ መንግስት ብቻ ሳይሆን የቦርድ አባላቱ ሊያግዙት እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃናም የሁለቱንም ሀሳብ ይጋራሉ። በአገራችን ይህ ተግባር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነም ያነሳሉ። በተለይ እርሳቸው የሚያስተዳድሩት ዩኒቨርሲቲ መመረጡ ደግሞ ሥራውን በአግባቡ ከውኖ ለሌላው ማስተላለፍ የሚችልበት አጋጣሚ ስለሚፈጥርለት ደስተኛ ናቸው። እንደርሳቸው እሳቤ፤ ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ መሆኑ ብዙ ጥቅም እንዲያገኝ ያስችለዋል። አንዱና ዋነኛው ደግሞ በየጊዜው በበጀት ጉዳይ እንዳይጨቃጨቅ ማድረጉና የፈለገውን እንዲሰራ እድል መስጠቱ ነው።

ከዓመት ወደ ዓመት እየፈሰሰ ያለው ሀብት እንዳይባክንም እድል ይሰጠዋል። ምክንያቱም ሀብቱ በራሱ የሚመጣ በመሆኑ በአግባቡ ይጠቀማል። በጀቱንም ከዓመት ወደ ዓመት ማሸጋገር ስለሚችልና ተጠያቂነት ስላለበት ሀብቱ ትምህርት ጥራቱ ላይ አሻራውን እንዲያሳርፍ ያደርጋል።

የሀብት ማሰባሰቡ ሥራ በራሱ በዩኒቨርሲቲው የሚሰራ በመሆኑ ድካሙ ታውቆ ወደ ተግባር ለመግባትም ያስችላል ያሉት ፕሮፌሰር ጣሰው፤ አሰራሩ መዘርጋቱ ካምፓስ ጭምር የሚያዋጣቸው ድረስ ሄደው እንዲከፍቱ እድል ይሰጣል። ውጪ ጭምር ሊሆን ይችላል። ከሁሉም በላይ ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት ያስችላል። በተጨማሪም የዩኒቨርሲቲውን አቅም ታይቶ ባንክ ጭምር እንዲያበድረውና የተሻሉ አማራጮችን እያየ እንዲሰራም በር ይከፍትለታል። በተመሳሳይ ተወዳዳሪነት ስለሚሰፋ ወላጆችም ሆኑ ተማሪዎች የሚመርጡት ተቋም እንዲሆንም ያስችለዋል ብለዋል። እኛም ትግበራው እውን ሆኖ ትምህርት ጥራቱ የሚገባውን ውጤት ያግኝ በማለት ተሰናበትን። ሰላም!!

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# "እነሱ እየተቹ እኛ እየሰራን ፍሬ ስናመጣ የነሱ ልጆች ስኛ ዘብ ይቆማሉ"

## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ

በጋዜጣው ሪፖርተር

**በትናንት ክፍል ሁለት እትማችን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የሰውጡ ጉዞ ያለበትን ደረጃና ፈተናዎቹን ፣ ስለ ሰላማዊ ሰልፍ መከልከል፣በሽግግር መንግስትና ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ስተነሱ ጥያቄዎች የሰጡትን ማብራሪያ ማስነበባችን ይታወሳል። በዛሬም ክፍል ሶስት እትማችን ደግሞ በበጀት፣በኤክስፖርት ፣በፕሮጀክት አፈጻጸምና በመሳሰሉት ዙሪያ የሰጡትን ማብራሪያ ይዘን ቀርበናል።**

**ክፍል ሶስት**

ብድር እንቀንስ፤ ብድር ብዙ ጣጣ አለበት፤ ካለ አግባብ ሰብስበን ከተበደርን ቀጥሎ እንግዛ የሚባል ነገር ይመጣል፤ ብድር ብዙ ሀገራት ላይ ጣጣ አምጥቷልና ብድር መቀነስን ልክ እንደ ልማት መውሰድ አለብን። ባለፈው የነበረው የብድር ክመራ ትንሽ ቆይቶ ቴሌ ኮምን አምጡ ምናምን አምጡ ወደ ሚል ስለሚሄድ አደገኛ ነው የሚል በሪፎርማችን ስንሠራ እንደቆየን ይታወቃል። አሁንም የዚህ በጀት ዓመት ትኩረት እርሱ ነው። እርሱን ማድረግ ካልቻልንና ብድር ካልቀነስን ተከትሎ የሚመጣ ጣጣ ስላለ ማለት ነው።

ሁለተኛው የበጀት ጉድለትን መገደብ ነው፤ ፍላጎት እንዳያችሁት በጣም እየሰፋ ነው፤ የበጀት ጉድለትን መገደብ ያስፈልጋል። ሶስተኛ ያለንን ሃብት በቁጠባ መጠቀም ነው። ውሱን ሃብት ነው ያለን፤ ፍላጎታችን እጅግ ግዙፍ ነው፤ ያን ቆጥበን መጠቀም ካልቻልን የፊዚካል ኮንሶሌሺን ማረጋገጥ አንችልም። አንዱ የሚያተኩረው እዚህ ላይ ነው።

ሌላው የዋጋ ንረትን ማረጋጋት ነው፡ የዋጋ ንረት ላለፉት 17፣ 18 ፣ 19 ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ በቀጣይነት በየዓመቱ እያደገ የመጣ ጉዳይ ነው። ባለፈው እንዳነሳሁላችሁ ለሁለት አስርት ዓመታት ሳይቋረጥ የዋጋ ንረት ኢትዮጵያ ውስጥ ይካሄድ ነበር። አንዳንድ ጊዜ እድገትም እንደዚህ አይነት ችግር ያስከትላል። ባለፉት ሁለት ሶስት ዓመታት ዋጋ ንረቱን ለመከላከል ሰፊ ሥራ ባይሠራ ኖሮ በነበርንበት ውጊያ፣ በነበርንበት ኮሮና፣ አሁን በዩኩሬን ባጋጠመው ችግር እጅግ የገዘፈ ነገር ያጋጥመን ነበር። ግን ቀደም ሲል ሙከራዎች ስለነበሩ የዚያ ሙከራ ውጤት በተወሰነ ደረጃ አግዞናል፤ሙሉ በሙሉ መቅረፍ ባንችልም አግዞናል። አሁንም የዋጋ ንረትን ለማረጋጋትና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ህይወት እየደረሰባቸው ያለውን ፈተና በተወሰነ መልኩ ለማቃለል መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይጠበቅበታል። ከዚህ ውስጥ አንደኛው የገንዘብ አስተዳደርን በጥብቅ መቆጣጠር ነው። ገንዘብ ያለአግባብ ኢኮኖሚው ውስጥ ከተረጨ የሚያስከትለው ጣጣ ስላለ ያን ለመቀነስ የገንዘብ አስተዳደርን በጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል። የእናንተም አንድ አንኳር ሥራ እርሱ ይሆናል።

ሁለተኛው ፕሮዳክቲቪቲን ማሳደግ ነው። በግብርና የጀመርነውን አስደማሚ ውጤት ማስቀጠል ነው። ሁላችሁም ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ወረዳዎች ስለመጣችሁ በየቦታው ከግብርና ጋር ተያይዞ በተለይ አምራች አካባቢዎች ላይ የመጣውን ለውጥ ታውቁታላችሁ። ዛሬ ይህንን ንግግር እያደረግን ወደ 20ሺ የሚጠጋ ፓምፕ እየገጠምን እንገኛለን፤ ዛሬ። ፕሮዳክቲቪቲ ላይ የጀመርነው ነገር ፓምፖችን በማብዛት የውሃ አጠቃቀም በማብዛት፤ በብዛት ማምረት ከቻልን ገበያ ለማረጋጋትም ይሁን ሸጠን ለመጠቀም ያግዛል። በጀቱ ይህንን ጉዳይ እንደ አንኳር ሀሳብ ይወስዳል።

ሶስተኛው ፕሮጀክትን ማጠናቀቅ ነው። ፕሮጀክቶች ካላግባብ እየተራዘሙ ሲሄዱ ኢኮኖሚን በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳሉ። ፕሮጀክት ማጠናቀቅ ሲባል፤ የምናወራው ስለ ቢሊዮን ዶላር ነው፤ ትንሽ ብር አይደለም፤ ግድቦቻችን ብቻ በጣም ብዙ ቢሊዮን ናቸው ። በመንግሥት የሚሠሩ ኢንቨስትመንቶች በጣም ሰፊ ስለሆኑ ሁሉም ማለቅም አለባቸው። ፕሮጀክት ካላለቀ ብዙ ጣጣ ስላለበት ነው።

አራተኛው የመልሶ ግንባታና ሰብአዊ እርዳታ ነው። የተፈናቀሉ፣ የተጎዱ ሰዎችን መልሶ ማቋቋም፣ መርዳት አቅም በፈቀደ በመንግሥትም በሁሉም ሪሶርስ ሕይወታቸው ወደ ቀደመው እንዲመለስ ማድረግ የበጀቱ ትኩረት ነው።

አምስተኛው የሀገርን ደህንነትና ሰላም ማስጠበቅ ነው። ቀደም ሲል እንዳነሳሁት ሀገራችንን ለማፈራረስ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለ ስለምናውቅ ተቋማቱን በእጅጉ ማጠናከር አስፈልጓል፤ ይህንን ሥራ እናስቀጥላለን። በድምሩ ሙሉ አቅማችንን በመጠቀም የጀመርነውን እድገት ማስቀጠል ነው። ባለፈው ዓመትም ፖዘቲቭ እድገት ኢትዮጵያ ውስጥ ታይቷል። በችግር ውስጥ ሆነን፤ አሁንም ከአፍሪካ ውስጥ ሻል ያለ እድገት ካላቸው ሀገራት ከመጀመሪያ ተርታ ኢትዮጵያ ትመደባለች።

ይህ የዓለም የፋይናንስ ተቋማት ያረጋገጡት ነገር ነው። ባለፈው ዓመት ያቀረብኩላችሁን ሪፖርት እንዳለ አይ ኤም ኤፍ ተቀብሎታል። የኢትዮጵያን እድገት የባለፈው ዓመት ለፓርላማ የቀረበውን እንዳለ ተቀብሎታል፤ ዘንድሮም ፖዘቲቭ እድገት እንዳለ ያምናሉ ። አጠቃላይ ውጤቱ የሚታወቀው መስከረም አካባቢ ቢሆንም ሻል ያለ እድገት ይጠበቃል።

ከዚህ በመነሳት የመንግሥት ገቢ የ12ኛው ወር የሰኔ ስላልተጠናቀቀ እስከ ግንቦት ያለውን የ11 ወር ስንመለከት እቅዳችን 330 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ነበር። በ11 ወር ውስጥ፤ ያስገባነው 309 ቢሊዮን ብር ነው። ከዕቅዳችን 93 በመቶ መሰብሰብ ተችሏል። የተከበረው ምክር ቤት ይሄንን ነገር ማየት የሚገባው አምና 11 ወር ከሰበሰብነው ዘንድሮ በ11 ወር የሰበሰብነው በ50 ቢሊዮን ብር ጭማሪ አለው። ወይም ከአምናው በ19 ነጥብ 4 በመቶ ጭማሪ አለው፤ ገቢያችን።

ገቢን እናሳድጋለን ብለን የነገርናችሁ ጉዳይ እያመጣ ያለው ውጤት ብዙ የኢትዮጵያ ቀጠና ውስጥ በግጭት ምክንያት የገቢ መሰብሰቢያ ቢሮዎች ተዘግተው እያሉ፤ ብዙ ቦታ ባለው የንግድ ሥርዓት መዛባት ምክንያት በገቢ ወጪ ንግዶች ላይ ጫና የፈጠረ እንኳን ቢሆን ገቢያችን በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ እያለ የ50 ቢሊዮን ብር ጭማሪ ወይም 19 ነጥብ 4 በመቶ እድገት አምጥቷል። ይህን ያመጣው አንደኛ በገቢ መሥሪያ ቤት ያሉ ሠራተኞችና አመራሮች በከፍተኛ ጥረት ሥለሠሩ ነው። ምስጋና ይገባቸዋል።

በገቢ ተቋማችን ችግር የለም፣ ኮራፕሽን (Cor-ruuption) ዜሮ ነው፣ ሰርቪስ (service ወይም አገልግሎት) በጣም ተሻሽሏል ብለን መፎከር ባንችልም ለውጥ እያመጡ ስለሆነ ገቢ ማሻሻል ችለዋል። ምስጋና ይገባቸዋል።

ሁለተኛ የኛ ነጋዴዎች ሙሉ በሙሉ ባይባልም ብዙዎቹ ዋና ብድር/ ግብር ከፋዮች የሚጠበቅባቸውን ብድር ለመክፈል እያሳዩ ያሉት ልምምድ በጣም ጥሩ ነው። የሚሸሹ እንዳሉ ሁሉ ቀደም ብለው የሚጠበቅባቸውን በመክፈል ለሀገርና ለመንግስት የሚጠበቅባቸውን ግዴታ የሚወጡ ነጋዴዎች እየተበራከቱ ስለመጡም ጭምር ነው። እነርሱም እንደዚሁ ምስጋና ያስፈልጋቸዋል።

ነገር ግን መጠናከር አለበት። አሁንም ኢትዮጵያ መሰብሰብ ከሚገባት ገቢ እጅግ አነስተኛ ነው። ዘንድሮ የፌዴራል መንግሥትን ነው ያነሳሁላችሁ ። በየክልሉም እንዲሁ ከፍተኛ የገቢ እድገት አለ ፤ አዲስ አበባን ጨምሮ። አቅም እንዳለ ያሳያል። ይህ መጠናከር አለበት።

ወጪ በሚመለከት ግን 500 ቢሊዮን ገደማ ነው ያወጣነው በ11 ወር። 309 ቢሊዮን ብር ገቢ አስገብተን 500 ቢሊዮን አወጣን ስንል የወጪና ገቢ ዴፊሲቱ (def-icit/ ኪሳራ) የሚሞላበት መንገድ በጣም በጣም ወሳኝ ነው። ወጪያችንን ካበዙ ጉዳዮች አንደኛው እና ዋነኛው እዳ ነው። በዚህ ዓመት አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ዶላር



ፎቶ - ዳኜ አበራ

**7ቢን እናሳድጋለን ብለን የነገርናችሁ ጉዳይ እያመጣ ያለው ውጤት ብዙ የኢትዮጵያ ቀጠና ውስጥ በግጭት ምክንያት የገቢ መሰብሰቢያ ቢሮዎች ተዘግተው እያሉ፤ ብዙ ቦታ ባለው የንግድ ሥርዓት መዛባት ምክንያት በገቢ ወጪ ንግዶች ላይ ጫና የፈጠረ እንኳን ቢሆን ገቢያችን በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ እያለ የ50 ቢሊዮን ብር ጭማሪ ወይም 19 ነጥብ 4 በመቶ እድገት አምጥቷል**

እዳ ከፍለናል። አልሞስት (almost/ ትንሽ የቀረው) መቶ ቢሊዮን ብር ገደማ እዳ ነው የከፈልነው።

ከነበረን ሀብት ቀንሰን ማለት ነው። ለምን? እዳ እንዳልኳችሁ ነው እየቆየ ሲሄድ ጣጣ አለው። ልክ ልማት ላይ ርብርብ እንደምናደርገው እዳችንን በፍጥነት ከፍለን ከስጋት ቀጠና ነጻ ለመውጣት ባለን ቁርጠኝነት ምክንያት ከፍተኛ ሃብት ለዕዳ አውለናል። ይሄን ስላችሁ እንግዲህ ከውጭ የምንጠብቀው ብዙ ሀብት እንደምታውቁት ሆኖ ሳይመጣ ቀርቶ ማለት ነው።

ሌላው ቃል የገባንላችሁ እና እጅግ ከፍተኛ ውጤት ያገኘንበት የማክሮ ቲሙን ማመስገን የሚያስፈልግበት አጠቃላይ ኢኮኖሚ ሴክተር ላይ የተሳተፉ ግለሰቦች፣ ባለሀብቶች እና የመንሥት ሠራተኞች ምስጋና የሚያስፈልጋቸው ኤክስፖርት ላይ ነው። ኤክስፖርት ላይ ያመጣነው እምርታ በጣም በጣም ግዙፍ ነው። ይሄንን ነገር ጠብቀን ለጥቂት ዓመታት ማስቀጠል ከቻልን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የንግድ መዛባትና የውጭ ምንዛሪ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል።

ኢትዮጵያ በ2002 ዓ.ም ሁለት ቢሊዮን ዶላር ኤክስፖርት አድርጋ ነበር፤ ጉድስ (goods/ ሸቀጦች)። ከ2002 እስከ 2012 ዓ.ም ሶስት ቢሊዮን ለመድረስ ትንገዳገድ ነበር። ትንሽ የቀረው። በ10 ዓመት ውስጥ አንድ ቢሊዮን ገደማ ነው የጨመርነው። ባለፈው ዓመትና በዘንድሮው ዓመት በሠራነው ሪፎርም በሁለት ዓመት ውስጥ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ በመጨመር ዛሬ በጉድስ እና ሰርቪስ ኤክስፖርት ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ አግኝተናል፤ በጉድስና በሰርቪስ ።

ጉድስ ባለፈው ዓመት ከነበረው ዘንድሮ ጭማሪ አሳይቶ ከአራት ቢሊዮን ዳላር በላይ ኤክስፖርት ውጤት ተገኝቷል። ሰርቪስ ደግሞ በ25 ፐርሰንት አድጎ ከስድስት ቢሊዮን በላይ አግኝተናል። በሰርቪስና በኤክስፖርት አስር ቢሊዮን ስንገባ በሁለቱ ከ2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዳላር አካባቢ የሚገመት ተጨማሪ ሃብት አፍርተናል። የሰርቪስ ከፍ ይላል፤ በዚህ ደግሞ በሁለቱ ዓመት ውስጥ አንድ እንጨምርበታለን። ይሄ በጣም ትልቅ እምርታ ነው። ግን ሊያዘናጋን አይገባል ከምንፈልገው አሁንም ሩቅ ስለሆንን ብዙ ሥራ ይጠበቅብናል።

በኤክስፖርት የተገኘው ውጤት ግን የሪፎርሙን ስኬት የሚያሳይ እጅግ ተስፋ ሰጪ ጅማሮ መሆኑን ያመላክታል። ያ እንደተጠበቀ ሆኖ ከየት መጣ ደሞ ያላችሁ እንደሆነ ግብርና ካገኘነው ከጉድስ ኤክስፖርት አልሞስት ሃያ ፐርሰንት እድገት ያመጣው ግብርና ነው።

# ወቅታዊ

ቡና በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ 1 ነጥብ 3 ቢሊዮን ዳላር ኤክስፖርት አድርገናል። ይሄ የግሪን ሌጋሲ ውጤት ነው። በያመቱ የምንተክላቸው የምንጎነት(ድ)ላቸው የቡና ምርት ውጤት እያመጣ ነው።

በሻይ የጀመርነውን ካፋጠን፣ በአቦካዶ በማንጎ የጀመርነውን ካፋጠን በፍሩት በቪጅቴብልስና ቡናና ሻይን ጨምሮ ከፍ ያለ ገንዘብ ልናገኝ እንደምንችል እርግጠኞች እድሉ እንዳለ ያመለክታል። ትምህርት ወስደን አበክረን ከሰራን በጉድስ የተገኘው ሰርቪስ የማደግ እድሉ ሰፊ ነው። ሰርቪስም ቢሆን በሰርቪስ ኤክስፖርትም ቢሆን ከአምናው የተሻለ የቱሪዝም ዴስቲኔሽን እያሰፋን ስለሆነ በሚቀጥለው አመት ቱሪዝማችን የተሻለ ከፍ ይላል።

ከሁለት ከሶስት ዓመት በኋላ ግን በደንብ ያድጋል ተብሎ ይጠበቃል። ሰላማችን እየተረጋገጠ ሲሄድ መዳረሻዎች ደግሞ እየተዋወቁ ሲሄዱ ብዙ ውጤት እንጠብቃለን። ኤክስፖርት በሰርቪስም በጉድስም ከአስር ቢሊዮን ዳላር በላይ ማግኘታችን ትልቅ ድል ሲሆን የእናንተ ቁጥጥርና ድጋፍ የህዝቦች ተሳትፎ የአርሶ አደሮች ቁርጠኝነት የማክሮ ቲሙ የእለት ተእለት አመራር ውጤት ነው። በዚህ ሁላችንም ደስ ሊለን ይገባል። ነገር ግን እንዳንዘናጋ ደግሞ ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

ነገ ከሀምሌ አንድ ጀምሮ የአዲሱን ዓመት ኤክስፖርት መምራት ይፈልጋል። ነገ ካልጀመርን ከአስር ወር ከአስራ አንድ ወር በኋላ የምንፈልገውን ውጤት ልናገኝ እንቸገራለን። እና ከኤክስፖርቱ አንጻር እጅግ ጥሩ ውጤት ታይቷል ሊባል ይችላል። ሁለተኛው ፎሬይን ዳይሬክት ኢንቨስትመንት ነው፤ ኤፍ.ዲ.አይ ነው። ኤፍ.ዲ.አይ ኢትዮጵያ ላይ መከራና ችግር ቢወራም ከባለፈው አመት ዘንድሮ አስር ፐርሰንት እድገት አለው።

ከሶስት ቢሊዮን ዳላር በላይ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ኢትዮጵያ መጥቷል። አንዳንዴ ግራ ያጋባል፤ ኢትዮጵያ ችግር ነው ይላሉ በየቦታው ስትሄዱ ችግሩን የሚያባብሱ ሰዎች ያጣብቡታል፤ እንጦጦን የሞሉት እነሱ ናቸው። ኢትዮጵያ ችግር ነው ይላሉ እኛ ለኢንቨስትመንት ብዙ ድጋፍ ባልሰጠንበትና ባላመቻቸንበት ሁኔታም እያደገ ነው ያለው። ግን እዚህ አገር ተስፋ አለ፤ ከገባን ከሰራን ተስፋ እንዳለን ያሳያል።

ኤክስፖርታችን ማደጉ ገቢያችን ማደጉ ፎሬይን ዳይሬክት ኢንቨስትመንት ማደጉ የኢኮኖሚው አካሄድ ምን ምልክት እንዳለው ያመለክታል። ሶስተኛ አራተኛ ፋይናንሻል ሴክተር ነው። ፋይናንሻል ሴክተር በየዓመቱ በቀጣይነት እንዳቀረብኩላችሁ ሪፖርት ከሪፎርም ማሻሻያ በኋላ ሃያ ሰባት ፐርሰንት ቦንድ አንዳንድ ክልከላዎች ካነሳን በኋላና ብድር ወደ መንግስት የሚሄደውን ወደ ፕራይቬት ሴክተር እንዲፈስ ካደረግን በኋላ ከፍተኛ መነቃቃቶች ታይተዋል።

የባንኮች አጠቃላይ ሃብት 2 ነጥብ 3 ትሪሊዮን ብር ደርሷል። እዚህም ሃያ አንድ ፐርሰንት አድገናል፤ አጠቃላይ ሃብታችን። የቅርንጫፍ ቁጥር ደግሞ ስትመለከቱ 8242 ደርሷል። ቅርንጫፎች ከአምናው በአስራ ሰባት ፐርሰንት አድገዋል። ተደራሽነት ሰፍቷል ማለት ነው። ቅርንጫፎች እየሰፉ በመሄዳቸው ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የባንክ ደብተር ያላቸው ተገልጋዮች ከስተመሮች 82 ነጥብ 4 ሚሊዮን ህዝብ የባንክ ደብተር አለው።

አንዳንዱ አራት አምስት ሊኖረው እንደሚችል ታሳቢ አድርጋችሁ ማለት ነው። በቡክ ደረጃ ግን 82 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሰው ቡክ አለው። እነዚህ ቡክ ካላቸው ሰዎች ውስጥ ዲፖሲት የተደረገው ገንዘብ 1 ነጥብ 6 ትሪሊየን ብር ነው። ቅርንጫፍ በበዛ ቁጥር ደንበኛ በበዛ ቁጥር ሴቭ የሚያደርገውም ቁጥር ስለሚያድግ ከዚያ ሴቭ ከምናደርገው ሃብት ላይ ለማበደር ትልቅ እድል እናገኛለን ማለት ነው።

ዘንድሮ ለብድር የዋለው ሃብት 353 ቢሊየን ብር ነው ። ከዚህ ውስጥ ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ዋናውን ድርሻ የሚወስደው የግሉ ዘርፍ ነው።በገቢ ተስፋ ሰጪ እድገት አለ። በኤክስፖርት ተስፋ ሰጪ እድገት አለ። በቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንት ተስፋ ሰጪ እድገት አለ ። ፋይናንሺያል ሴክተሩ በቀጣይነት እያደገ ነው ።

ይሄንን ትተን በሴክተር ብንመለከት ግብርና ከንግግር ወጥቶ ምርታማነቱ እንዲያድግ አንደኛው ያልነው ኩታገጠም ያልነው ሀሳብ ሁለት ጎን ለጎን ያሉ መሬቶች አስተሳስሮ ማረስ ብቻ ሳይሆን ፤ ሁለት አርሶ አደሮች አርቴፊሻል ድንበር አበጅተው ምርታቸው እንዳያንስ አዕምሯቸው ውስጥ መደመር ነው ፤ አዕምሯቸው ውስጥ ማስተሳሰር ነው። በጋራ ብናለማ፣ ማሽን ብንጠቀም የተሻለ ምርት እናገኛለን ብለው እንዲያምኑ ማድረግ ነው።

ሰው በአዕምሮው ሲደመር መሬት ማስተሳሰር ቀላል ስለሚሆን ኩታ ገጠም ትልቅ ውጤት እያገኘንበት ነው። አሁንም ስራ ይፈልጋል። የተፈጥሮ ማዳበሪያ ዘንድሮ በተለያየ አለም እንደሰማችሁት አለም የመሰከረው ጉዳይ ነው ። ማዳበሪያ ውድ ሲሆን መንግስት ጫና ሲፈጥር መንግስት ከፍተኛ ሃብት ልክ እንደ ብድሩ ወደ አንድ ነጥብ 23 የሚጠጋ ቢሊየን ዶላር ለማዳበሪያ አውጥተናል፤ ከአምናው እጥፍ ነው ያወጣነው። ያ በቂ ስላልሆነ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በየአካባቢው እንዲመረት ሰፊ ስራ ተሰርቷል። ትልቅ ውጤት ተገኝቶበታል። ይሄም በቂ አይደለም ።

**ሁሳችንም መረባረብ አለብን። ይሕ ምክር ቤት ከደመወዙ ቀንሶ ደመወዝ የለውም አዎ ከደመወዙ ቀንሶ አንድ ሁለት ሶስት አሮጊቶች ቤት ቢያድስ በሚቀጥለው የተሻለ ምክር ቤት ይሆናል። የሚጠይቅ ብቻ ሳይሆን ችግር የሚፈታ ሲሆን ማለት ነው። ስሴላውም አርአያ ስለምትሆኑ፣ በየተቋማት ስለምትሄዱ ስንት ቤት ገነባህ፣ ስንት ቤት አደስክ ስለምትሉ የእናንተ መሳተፍ በእጅጉ ስለሚያግዝ መስራትም፤ መምራትም ይጠበቅባችኋል**

ኩታ ገጠም፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ካደረግን በኋላ ቅድም እንደተነሳው ደግሞ ለግብአት የሚሆን ፣ ለማሽነሪ ግብአት ታክስ እንዲነሳ ተደርጓል። ግብርናውን ለመደገፍ እንዲቻል። የውሃ አጠቃቀም ላይ አሁንም ብዙ ሥራ የሚጠበቅብን ቢሆንም ባለፉት ሁለት ዓመታት በሺህ የሚቆጠሩ ፓምፖች መጠቀማችን ከአንድ ጊዜ በላይ ለማምረትና ምርት ለማሳደግ አግዘውናል። ማሽነሪ አጠቃቀማችን እያደገ ነው። ኮምባይነር ፣ትራክተር በየቦታው እያደገ ነው።አሁንም ግን ሰፊ እንቅስቃሴ አለ።

የፋይናንስ አቅርቦትን በሚመለከት በበጀት ለግብርና ሚኒስቴር ለቆላማና ሎላንድ ሚኒስቴር ከተሰጠው በጀት በተጨማሪ በብድር ቅድም ያነሳሁላችሁ ብድር ፕራይቬት ከፈሰሰው ሃብት 34 በመቶው ለአርሶ አደር ለግብርና የሄደ ነው። አልነበረም የግብርና ኢንቨስትመንት ያንሳል፤ ሃብቱ ወደዛ ማፍሰስ አለብን ባልነው መሰረት 34 በመቶ ብድር ከግብርና ጋር ለሚያያዝ ኢንቨስትመንት የዋለ ነው። በዚህ ምክንያት ነው ውጤቱ እየተሻሻለ የመጣው። እዚህ ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት ኤስኤምኤስ ናቸው።

እነዚህ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ከአነስተኛ ጥቃቅን ጋር በመሆን ከአርሶ አደር ጋር በመሆን እየሰሩ ያሉት ነገር ምንም እንኳን ውስን ሃብት ያላቸው ቢሆንም በጣም ከፍተኛ ነው። የማይክሮ ፋይናንስ ዘንድሮ ለ3 ነጥብ 8 ሚሊየን አርሶ አደሮች ብድር አቅርበዋል። ቅድም ያነሳሁላችሁ በትሪሊየን የሚቆጠር ብር የሚያንቀሳቅሱ ባንኮች 350 ሺህ ሰው አይሞላም የተበደራቸው ። ከ100 ሚሊየን ውስጥ 350 ሺህ ሰው የማይሞላ ነው የባንክ ሃብት ላይ በብድር የሚነቃነቀው። በማይክሮ ፋይናንስ ካላቸው ጥቂት ሃብት ግን 3 ነጥብ 8 ሚሊየን የሚጠጋ አርሶ አደር ብድር አግኝቷል።

እነዚህ እንደ አግሪካልቸር ባንክም የሚያግዙ ስለሆነ የክልል መንግስታት እናንተ እኛ ተጋግዘን አቅማቸውን ከፍ ብናደርግ ተደራሽነታቸው ሰፊ ስለሆነ በግብርና ላይ ከፍተኛ ውጤት ያመጣሉ ተብሎ ይጠበቃል። በፋይናንስና በተሰጠው አመራር ምክንያት የግብርና ምርታማነት ያው ሁላችሁም እንደምትታዘቡት አድጓል።

ባለፈውም ብዬዋለሁ አሁንም እደግመዋለሁ ! ንፁሃን አለአግባብ እየተገደሉም፤ በየቦታው ከሳሾች ጠዋት ማታ እየነዘነዙን በሚቀጥለው አመት ስንዴ ኤክስፖርት እናደርጋለን ። ስንዴን ኤክስፖርት ማድረግ እንዳንችል ሲያደርጉ ተሳክቶላቸዋል ። ስንዴን ኤክስፖርት ማድረግ ችለን መስዋዕትነት ካስከፈሉን አሸንፈናቸዋል ። ድላችን የሚረጋገጠው ያሰብነውን በማሳካት ነው።

ስንዴን ኤክስፖርት እናደርጋለን፤ ለዛ የሚያበቃ ሰፋፊ ስራ በዚህ ክረምት በሚቀጥለው በጋ እየተሰራ ነው። ኤክስፖርት ቅድም እንዳነሳሁት ትልቅ ውጤት ነው ያገኘነው። በግብርና አትክልትና ፍራፍሬ መጨመር በተወሰነ ደረጃ ሻይ ካስፋፋን ፤ቡናችን ካደገ ፤ማእድን ላይ የምንሰራውም ተስፋ ከሰጠ በሚቀጥለው አራት አመት አንዱ ትኩረት ማድረግና ውጤት ልናመጣ የሚጠበቀው ኤክስፖርት ላይ ነው።

በኤክስፖርት አመርቂ ስራ የሰሩ አገራት ናቸው የተሻለ የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥ የቻሉት። ይሕ ሁሉ መልካም ዜና እያለ ግሽበት ግን አሁንም የኑሮ ውድነት እያስቸገረን ነው። የኑሮ ውድነት ባለፉት አመታት እንዳልኩት ለሁለት አሰርት አመታት ኢትዮጵያ ውስጥ እያደገ የመጣ ጉዳይ ነው። በዚህ ላይ በአለም አቀፍ ደረጃ የሚያጋጥሙ ቀውሶች ኢምፖርት ግሽበት ስላላቸው የራሳቸው የሆነ ጣጣ አምጥተውብናል። ነገር ግን በጀት ከኑሮ ውድነት ጋር ያለው ትስስር በጀት ስለሆነ እያየን ያለነው አንደኛ የበጀት ጉድለት ከየት ይሞላል ነው። ይሕ በጀት የኑሮ ውድነት ያባብሳል ወይንስ ይገራል ተብሎ የሚጠየቀው ጉድለት ከየት አምጥተት እንሞላላን ነው። ቀጥታ ከብሄራዊ ባንክ የምንበደር ከሆነ ግሽበት ይባባሳል። በተቻለ መጠን ጉድለታችንን ለማሟላት የምንጥረው ከግምጃ ቤት ሰነድ ሽያጭ ነው። ይሕ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ አለው። በተቻለ መጠን ከብሄራዊ ባንክ በቀጥታ ብድር ላለመሸፈን ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። አሁንም በቁጥጥር የምንመራው እሱን ይሆናል።

ሁለተኛ የገንዘብና ፊዚካል ፖሊሲ ቁጥጥርን ማጣናከር ነው። የሚፈሱ ሃብቶች በትክክለኛ መንገድ የሚፈሱ መሆናቸውን ይበልጥ መቆጣጠር ያስፈልጋል። ሶስተኛ ለድህነት ተኮር ዘርፎች ቅድሚያ ሰጥቶ በጀቱን መጠቀም ነው። ይሕ ሲባል ጤና፣ትምህርት ፣መሰረተ ልማት ያካትታል።

ለምሳሌ ጤናን ብንመለከት አዲስ አበባ ውስጥ በጣም በርካታ የግልና የመንግስት ሆስፒታሎች እየተሰሩ ነው። ጳውሎስ ብቻ ብትሄዱ ከአንድ ሺ አልጋ በላይ አቅም ያለው በዋና ዋና የኢትዮጵያ ችግሮች ላይ የሚያተኩር በካንሰር በኩላሊት ንቅለ ተከላ ላይ የሚያተኩር የሆስፒታል ማስፋፊያ ከ 80 በመቶ በላይ ደርሷል። ምናልባት በሚቀጥለው አመት እናጠናቅቃለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ይሕ በህክምና አካባቢ ያለውን ችግር በእጅጉ የሚፈታ ነው። በትምህርት ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት በጣም በርካታ ሁለተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እየተገነቡ ነው። እነዚህ ነገሮች የሚደግፍ በጀት መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። 59 በመቶው የሚሆነው የዘንድሮው በጀት የሚውለው ድህነት ቅነሳ ላይ ነው። ይሕን በቁጥጥር እና ክትትል ስኬታማ ማድረግ ከቻልን ዜሮ ባያደርገውም ለድህነት ቅነሳ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል። ሌላው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው አቅመ ደካሞች አዛውንቶች ቤት መስራትና ቤት ማደስ ነው። ይሕ ነገር ጨዋታ አይደለም። የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት የአሮጊቶች ቤት ማደስ ጨዋታ አይደለም። ትልቅ ስራ ነው። ተረባርበን ልናደርገው ይገባል። በየቦታው የእነርሱን ጩኸት እና ለቅሶ በእጅጉ ዋጋ ይደግፋል። የእናቶችን ከንፁህ ልብ የሚቀዳ ፀሎትና እንባ ፈጣሪ ያያል። ለእነርሱ የምናደርገው ማንኛውም ድጋፍ መልሶ አገር ይደግፋል። ብዙ ሙከራዎች አሉ። የግሉ ዘርፍ ከምትጠብቁት በላይ በዚህ ጉዳት ላይ እያገዘን ነው።



# ወቅታዊ



ሁላችንም መረባረብ አለብን። ይሕ ምክር ቤት ከደመወዙ ቀንሶ ደመወዝ የለውም አዎ ከደመወዙ ቀንሶ አንድ ሁለት ሶስት አሮጊቶች ቤት ቢያድስ በሚቀጥለው የተሻለ ምክር ቤት ይሆናል። የሚጠይቅ ብቻ ሳይሆን ችግር የሚፈታ ሲሆን ማለት ነው። ለሌላውም አርአያ ስለምትሆኑ፣ በየተቋማት ስለምትሄዱ ስንት ቤት ገነባህ፣ ስንት ቤት አደስክ ስለምትሉ የእናንተ መሳተፍ በእጅጉ ስለሚያግዝ መስራትም፤ መምራትም ይጠበቅባችኋል።

እንደምታውቁት 25 በመቶ የሚጠጋው የኢትዮጵያ ምግብ ነክ ነገር ከውጭ ነው እየገባ ያለው። ይህን ተሸክመን ኢንፍሌሽን ኢምፖርት እንዳይደረግ ማድረግ አንችልም። ሁሉም ይቅር እንዴት የማንጎ ጁስ ኢምፖርት እናደርጋለን። ማንጎ በአንዳንድ አካባቢ በኢትዮጵያ ውስጥ ከዛፍ ላይ ወድቆ እንደ ቡና ከመሬት ይለቀማል። ልናመርት፣ልናስፋፋ አንችላለን። ሙዝ ላይ የጀመርነው ፣አቡካዶ ላይ የጀመርነው፣ ማንጎ ላይ የጀመርነው ጉዳይ፤ በከተማ ውስጥ ሰላጣ ቆስጣ በርበሬ ድንች የጀመርነው ጉዳይ ቢስፋፋ ብዙ ችግር ሊያቃል ይችላል። ስንጀምረው ቀልድ ነው እየቆየን ስንሄድና ባህል ስናደርገው ግን ውጤቱ ከፍተኛ ነው።

ይህን ታሳቢ አድርገን ብንረባረብ ምርት ካደገ የገንዘብ ስርአትን ከተቆጣጠርን ግሽበት ዘንድሮም ቢሆን ከብዙ ሀገራት አንጻር የጀመረነው ነገር ስላገዘን ጥሩ ነገር አለ። የበለጠ ይጠናከራል። አሁን ግን ዛሬ አነስተኛ ገቢ ያላቸው የመንግስት ሰራተኞች ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች በጥቅሉ በእለት መኖር እየተሰቃዩ ነው። በእለት መኖር ኢትዮጵያ ውስጥ ፈተና እየሆነ ነው። ይህንን ጉዳይ ለመፍታት እንደው የግሽበትን ጉዳይ ምን እናድርግ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ባለው አቅምና ቦታ መስራት እኛ ደግሞ ባለን ሃላፊነት ገንዘብ ላይ ቁጥጥር ማድረግ፤ፖሊሲዎቻችንን መፈተሸ ምርታማነትን ማሳደግና አንድም ማረጋጋት ሁለተኛም ደግሞ የሚበላ ነገር እንዲበዛ ማድረግ ይኖርብናል። በዚህ አካሄድ ከሄድን ምን አልባት የተሻለ ውጤት እናገኛለን ተብሎ ይጠበቃል።

የህዝብ ቆጠራ ሳይደረግ በጀት ሲመደብ ኢፍትሃዊ አይሆንም ወይ ለተባለው፤ ቆጠራ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። የህዝብ ቆጠራ ለሁሉም አይነት ጋኒክ ያግዛል ማንኛውም የምናስበው ነገር ይሄ ከጠባቂነት ከፌዴራል መንግስት ከሚሰጠው ገንዘብ አንጻር ሳይሆን ለማንኛውም ፕላኒንግ ቆጥረን አውቀን የምናደርገው ነገር ጠቃሚ ነው። እና ቢሰራበት የሚለው ምክረ ሀሳብ እንደ ጥሩ ነገር ነው የሚወሰደው።

ነገር ግን አሁን ፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀመር ሲወስኑ ሙሉ ስልጣኑ የእነሱም ቢሆን እናንተ ስልጣናችሁ በቀረበው ቀመር ላይ በጀት ማጽደቅ ቢሆንም

**የታችኛው ቤተ መንግስት እድሳት ተጀምሯል። መሀል ላይ ያለው ቆሻሻ ቦታዎች ፈርሰዋል። ታችናው ቤተ መንግስት ውስጥ ያሉት የኢትዮጵያ ሀብቶች ታሪኮች በትክክል ግልጥ ብለው ለህዝብ ከታዩ ብዙ ችግር ይፈታሉ። ሌላው አሁን የምንጣላባቸው የወሰን ጉዳዮች ቁልጭ ብለው በካርታ የዛሬ መቶ አመት ቤተ መንግስት አለ**

እንኳን ግን ፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀመር ሲያጸድቅ ሁላችሁም እንደምታውቁት ሳይንሳዊ ፕሮጀክሽን ታሳቢ አድርጎ ነው። ዝም ብሎ አይደለም ፤ሙያተኞች አሏቸው አጥንተው፣ ክልሎች ተወያይተው ነው የሚወስኑት። ያ ነገር ትክክል አይደለም ካልን በተናጥል የሚጎዳው፤በተናጥል የሚጠቅመው ሰው የለም። ምክንያቱም የተቆጠረ ሰው ወይንም ክልል የለም፤ሁሉም ክልል አልተቆጠረም።አደገኛ የሚሆነው ከፊሉ ተቆጥሮ ከፊሉ ያልተቆጠረ ቢሆን ነው።

አሁን የነበረውን ቆጠራ አዲስ ቆጠራ አድርገን እስክናስተካክል ድረስ ሳይንሳዊ ፕሮጀክሽን እያደረጉ ከፍ ከፍ ያለ በጀት የሚጠቀሙ ክልሎች ደግሞ አሁን አሁን ፌዴሬሽን ሲሰበሰብ ሰምታችሁ ከሆነ እየተነጋገሩ እየቀነሱ አነስተኛ ገቢ ላላቸው ክልሎች ኮታቸውን እየለቀቁም ጭምር ነው።ትክክል የሆነ የቁጥር ስራ ብቻ ሳይሆን የድርድር ነገርም ያለበት አቀራረብ ስለሆነ ከፍትሃዊነት አንጻር ችግር አለበት ብዬ ብዙ አልገምትም።

ግን ቆጠራው ያስፈልጋል፤ ቆጠራ አድርገን ፕላን እናድርግ የሚለው ሀሳብ ትክክል ይመስለኛል። ወደፊት ሁኔታዎች ሲስተካከሉ ወደዛ መሄድ ይኖርብናል ። አሁን ለግዜው ግን ፌዴሬሽን ምክር ቤት ባቀረበው ቀመር መሰረት የእኛ ስልጣን በዚህ አግባብ መወሰን ስለሆነ እሱን ማየት የሚሻል ይመስለኛል።

መሰረተ ልማትን በሚመለከት ብዙ ጥያቄዎች ተነስተዋል። በመንገድ፣ በኤሌክትሪክ ፣በውሃ ፣በስኳር፣የመንገድን መሰረተ ልማት ብቻ የተከበረው ምክር ቤት ግንዛቤ እንዲኖረው ወደ ሶስት መቶ ሰላሳ አንድ የግንባታ ፕሮጀክቶች የፌዴራል መንግስት (ኢራ) ያስተዳድራል። ከአርባ ዘጠኝ በላይ ከባድ ጥገና እየተሰራ ይገኛል። ከሶስት መቶ ሰላሳ አንድ የግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ ሁለት መቶ ሀያ ስድስቱ ብቻ ሶስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ቢሊየን ብር ፋይናንስ ይደረግባቸዋል።

ኢራ የምንለው ትንሽ ተቋም በመቶዎች በሚቆጠር ፕሮጀክት በቢሊየን የሚቆጠር ብር ያስተዳድራል። በዚህ ምክንያት ብዙ ኮንትራት የሚያስተዳድር ስለሆነ እያንዳንዷን ፕሮጀክት ተቆጣጥሮ ሁሉን በእኩል ፍጥነት ማስኬድ ምን ያክል አዳጋች ስራ እንደሚሆን እናንተም መገመት ትችላላችሁ። መቶ አምስት የሚደርሱ ፕሮጀክቶች በዲዛይን በጨረታ ፕሮሰስ ላይ ያሉ ናቸው።

አንዳንዴ ዲዛይኑና ጨረታው ካለቀ በኋላ የፌዴራል መንግስት በጀት ይዞ በራይት ኦፍ ዌይ ምክንያት ክልሎች በሚፈጥሩት በጣም አስቸጋሪ ጉዳይ ፕሮጀክቶች አይጀመሩም ይጓተታሉ። ከተጀመሩም በኋላ ግማሹ ሄዶ ግማሹ ላይ እንደምታውቁት ችግር አለ። ነገር ግን ኢራ በአዲሱ ሪፎርም በከፍተኛ ደረጃ ፕሮጀክት መጨረስ የሚለው ሀሳብ አንዱ ኢምፕልመንት የምናደርገው።እነሱ ጋር ስለሆነ በጣም ስለሚረባረቡ እንደተቋም ስለሚረባረቡ እየተገኘ ያለው ውጤት ከፍተኛ ነው ሊባል ይችላል።

የጀመርናቸው አብዛኛው መንገዶች በግጭት ራይት ኦፍ ዌይ አይነት ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር የተጀመሩት መንገዶች በሙሉ በጥሩ ሂደት ላይ ይገኛሉ። አልፎ አልፎ ቀደም ሲል እንደተነሳው ችግር ያለባቸው ፕሮጀክቶችም አሉ። ለምሳሌ ከአርበረከቴ እስከ መቻራ ሐረር አካባቢ የሚሰራው የተጀመረው የዛሬ 7 ዓመት አካባቢ ነው፤ የቆየ መንገድ ነው። እና ይሄ መንገድ በቆየ ኮንትራት ውስጥ ከመኖሩ ባሻገር መጀመሪያ ራይት ኦፍ ዌይ ችግር ነበረበት። እሱ ሲፈታ ኩባንያው ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋር የማይግባባበት ከግብር ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ሁለት ዓመት ሙሉ አካውንት ተዘግቶበት ነበር።

ኩባንያው በዛ ምክንያት ሥራው ተጓቷል፤ በቅርቡ ተፈቶላቸው ሥራ ጀምረዋል። በፍጥነት እንደሚጠናቀቅ ተስፋ እናደርጋለን፤ አመራርም እየተሰጠበት ነው ያለው። እንደተባለው የሐረር አካባቢ ማሕበረሰብ ሕይወቱን ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ከፕሮጀክት አንጻር የተጀማመሩ ነገሮች አሉ ።ያን አጠናክረን እንቀጥላለን። ቀድሞ የተበላሸውን እናስተካክላለን፤እኛ የጀመርነውን እናፋጥናለን፤ እናንተም በቁጥጥር ታግዛላችሁ፤ እንደሚሳካ ተስፋ አለኝ።

ከጎዴ ጊኒር የሚሄደው መንገድ እንዲህ ቀላል አርገን የምናነሳው መንገድ አይደለም። 220 ኪሎ ሜትር ይሸፍናል። ከሆነ ክፍለ ሀገር አዲስ አበባ ያለ ዋና ዋና መንገድ ብላችሁ አስቡት። ከጎዴ ጊኒር የሚሄደው መንገድ 220 መሆኑ ብቻ ሳይሆን ላንድስኬፑም ቀላል አይደለም። ዳገታማ፣ ሞቃታማ አካባቢ ሰፊ የዲዛይን ሥራ የሚጠይቅ ቦታ ነው።

መንገዱ ሲሳካ በከፍተኛ ደረጃ ሱማሌን ከመካከለኛው ገበያ ጋር የሚያገናኝ ስለሆነ እጅግ ጠቃሚ ነው። እና ተለቅ ያለ ፕሮጀክት አሁን ዘንድሮ ከያዝናቸው ሰፋፊ ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ መሆኑን ከግምት ማስገባት ፤ይሄም በብዙ ሎት ተከፋፍሎ የሚሰራ ነው፤ ሰፊ ስለሆነ። የመጀመሪያው ሎት በቅርቡ ይጀምራል። እናንተም ድጋፍና ቁጥጥር ካረጋችሁ በተያዘለት ጊዜ ይከናወናል የሚል ተስፋ አለኝ።

ኤሌክትሪክ በሚመለከት፤ ያው ኤሌክትሪክ አንደኛ ኃይል ማመንጨት፣ ሁለተኛ የመነጨውን ኃይል ማስተላለፍ፣ ሦስተኛ የተላለፈውን ኃይል ማከፋፈል፣ የተከፋፈለውን ኃይል ደግሞ ማሰራጨት የሚባሉ አራት አንጓዎች አሉት። ስላመረትን ብቻ ሄዶ ኢነርጂ አይሆንም። ካመረትነው ምርት ውስጥ በማስተላለፍ ሲስተም ውስንነት ምክንያት ከ30 ፐርሰንት ያላነሰ ሎስ ያጋጥማል።

ኢነርጂው እያለ ከአንዱ ጫፍ አንዱ ጫፍ እስኪሄድ ይንጠባጠባል ኃይል፤ ያው ኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን በነበረው አሰራር እንደምታውቁት ናሽናል ግሪድ ነው የምንጠቀመው፤ የትም ተመርቶ ኢነርጂው ወደ ናሽናል ግሪድ ገብቶ ኢነርጂው ይሰራጫል። ይሄ የራሱ ጥቅምም ጉዳትም አለው።

እንደ ኢትዮጵያ ያለ እዚህም አንድ ሺ ሰው እዛም አንድ ሺ ሰው ከተማ ከተማ የሚባልበት የተበተነ ሕዝብ ሲኖር በጣም አስቸጋሪ ነው። እኛ አርባናይዝ አይደለንም፤ በሦስት አራት ከተማ የምንኖር ሕዝቦች አይደለንም። በየቦታው ስትሄዱ ትናንሽ መንደሮች አሉ። ሁሉም ደግሞ ኤሌክትሪክ ዲማንድ ያደርጋል፤ ይፈልጋል።

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ 110 ሺ ኪሎ ሜትር የማሰራጫ መስመር አለ። 110 ይፈለጋል፣ ይበጠሳል። ከተበጠሰ በኋላ ጥገና በጣም አስቸጋሪ ነው። አሁን ለምሳሌ ሲዳማም የራሱ ሎካላይዝ የሆነ ግሪድ የሚጠቀም ቢሆን ጥገናውም ምናምን ይቀንሳል። አርባምንጭም የራሱ የሚጠቀም ቢሆን ይቀንሳል፤ እዛው እያመነጨ የሚጠቀም ቢሆን ከተወሰነ ቦታ መንጭቶ ትራንስፖርት ሲደረግ ግን ችግር አለበት።

ሲዳማ ባልተፈጠረ ችግር አዳማ ባለ ችግር ሲዳማ ጨለማ ውስጥ ሊያድር ይችላል። ከናሽናል ግሪድ ስለሚሄድ ማለት ነው። ይሄንን ችግር ለመፍታት በሂደት ናሽናል ሄድን ወደ ኦፍ ግሪድ የምንቀይርባቸውን መንገዶች በተለይ ለአዲስ ፕሮጀክቶች እያሰብን እየሰራንበት እንገኛለን። ሁለተኛ ደግሞ አርበናይዜሽን እየሰፋ ሲሄድ በተወሰነ ደረጃ ይሄንን ይቀንሰዋል የሚል እምነት አለ።

አሁን ባለው ሁኔታ ግን በአራቱም በማምረትም፣በማስተላለፍም፣በማከፋፈልም በማሰራጨትም በጣም ሰፊ ሀብት ፈሶ እየተሠራ ነው። ኢትዮጵያ አሁን የያዘችውን ፕሮጀክቶች ስታጠናቅቅ አሁን ካለው ኢነርጂ እጥፍ በላይ ታገኛለች። በምርት ማለት ነው። ምርቱ ብቻውን በቂ አይደለም። ህዳሴ እኮ ምርት አልጀመረም በምንልበት ጊዜ ምርት ከህዳሴ ወደ ናሽናል የሚያስተላልፈው መሥመር ከተሰራ ሥንት አመት አልፎታ፤ተቀምጧል ኢነርጂው ሳይኖር። አሁን ሲጀመር ደግሞ ጠግኑኝ ይላል ማለት ነው። ብዙ ዓመት ስለተቀመጠ ጠግኑኝ ይላል። ቴስት መደረግ ስላለበት። በዚህ አግባብ ቢታይ ጥሩ ነው ።

ሲዳማ ላይ አራት ሰብስቴሽን ነው ያለን ሐዋሳ ቁጥር አንድ፣ ሐዋሳ ቁጥር ሁለት ፣ይርጋም እና አዋራ ላይ ሰብስቴሽኖች አሉ። 70 ኪሎ ሜትር የሚጠጋ መካከለኛ ጥገና ዘንድሮ አካሂደናል። ሲዳማ ክልል ብቻ። 33 ኪሎ ሜትር ዝቅተኛ መስመር ግንባታ ሰርተናል ። 27 የሚጠጉ ትራንስፎርመሮች አቅማቸው ከፍ እንዲል ተሰርቷል። በዚህም ከ83 ሚሊዮን በላይ ወጪ አድርጓል የፌዴራል መንግስት። ለሲዳማ ክልል ብቻ ። ኤሌክትሪክ ላይ ማለት ነው።

ከይርጋለም ወደ አለታ ወንዶ የሚሄደውን መሥመር በሚመለከት ከወርልድ ባንክ ጋር ድርድር ጀምረናል። ፋይናንሱ ሲገኝ የሚጀመር ይሆናል። ሁላችሁም እንደምታውቁት ኢትዮጵያ ሁለም ጫፍ መንገድ ይፈልጋል፤ሁሉም ጫፍ መብራት ይፈልጋል፤ ሁሉም ጫፍ ከፍተኛ ሰርቪስ ይፈልጋል። ይሄን አንድ ጊዜ ማሟላት ይከብዳል። አቅም በፈቀደ መጠን ግን

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ



**ጎርጎራ የሚባለው ፕሮጀክት አሜሪካ ማለት ነው። ጎርጎራ የምትባለው ከተማ ኢትዮጵያ ማለት ነው። ይሄን ፕሮጀክት የሚመጥን የህዝብ ኑሮ አብረን ማሰብ ካልቻልን እዚህ ጋር ገነት እዚህ ጋር ረሀብ ማስተናገድ አይቻልም**

ለመመለስ ጥረት እየተደረገ እንዳለ ከግምት እንዲገባ ነው።

ውሃን በሚመለከት የጎዴ መስኖ በደርግ ጊዜ የተሠራ ነው። በጣም ትልቅ ጠቀሜታ ያለው ፕሮጀክት ነው። ባለፉት 30 ዓመታት ግን ምንም ጥገና ሳይደረግለት ስለ ቆየ ያ ፕሮጀክቱ በጣም ሰፊ ሥራ ይፈልጋል። የመስኖ እና ሎላንድ ሚኒስትሪ አንዱ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ከለበት ፕሮጀክት ውስጥ የጎዴ መስኖ ነው። ከተሳካልን ብዙ ሺህ ሄክታር ልናርስበት እንችላለን። ቀላል ሥራ ግን አይደለም።

ረዥም ጊዜ የቆየ ነው፤ በጣም ብዙ ሀብት እና ጊዜን ይጠይቃል። የሸናሌ ከርሰ ምድር እንደዚሁ በሚኒስትሪው እየተሞከረ ነው ያለው። ሚኒስትሪው አዲስ በዚህ ዓመት የተቋቋመ ስለሆነ በፕራዮሪቲ ለይቶ እየሠራባቸው ካሉ ሴክተሮች እና ፕሮጀክቶች መካከል ውስጥ ስላሉ በእነሱ ውስጥ ውጤቱን ወደ ፊት የምናይ ይሆናል።

ስኳርን በሚመለከት በቀደም እንስቼላችኋለሁ። አምስት ተጨማሪ ፋብሪካዎች ጨምረን ምርት ለማሳደግ ሞክረናል። አሁንም ሠፊ ሥራ ያስፈልጋል። በተለይ አገዳ ላይ ። ፋብሪካ ሲሠራ አገዳ የለም ፤ አገዳው ሲመጣ ፋብሪካው አይሠራም ።እንደዚህ አይነት ችግር ፈተን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ እና በሀገር ውስጥ ያለውን ፍጆታ ማሻሻል ያስፈልጋል።

ስኳር ኢምፖርታንት ነው። በሌላ መንገድ ደግሞ በተቻለ መጠን ምቹ ሁኔታ ሲያጋጥም ስኳር የመጠቀም ልምዳችን እንዲቀንስ ማድረግ ጥሩ ነው። ስኳር ከጥቅሙ ያላነሰ ጉዳት ስላለው በተቻለ መጠን በተለይ የምክር ቤት አባላት በተቻለ መጠን ስኳር እኛቤት በቤት ደረጃ ህግ አውጥተናል ስኳር እንዳይገዛ ብለን። ልጆቻችን ጋር ጸብ ነው።

ውድ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን ስኳር ያው የጎንዮሽ ጣጣ ስላለበት መመጠን ጥሩ ይሆናል ከተቻለ። እንደው ዜሮም ባይሆን መመጠን ጥሩ ነው ያምቢሆን ግን አምርተን ፍላጎቱ ከፍተኛ ስለሆነ ሰፊ ስራ መሥራት ያስፈልጋል። በጎን ማስተማር በጎን ማምረት ሁለቱ ጎን ለጎን ከሄዱ ውጤቱ ያማረ ይሆናል።

ደረቅ ወደብን በሚመለከት አሁን ስምንት አሉን በተለያዩ ካፓሲቲ የሚሠሩ ስምንት ደረቅ ወደቦች አሉን። በ10 ዓመት እቅዳችን ወደ 11 እናሳድጋቸው ብለናል። ወደብ ማሳደግ የሚያስፈልገው የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር በጣም ከፍተኛ ነው ።የእኛን አይነት የሕዝብ ቁጥር ያለው ወደብ የሌለው ሀገር ዓለም ላይ የለም ። ከመቶ ሚሊዮን በላይ ህዝብ ኖሮት ወደብ የሌለው ሀገር የለም። ይሄ ኢኮኖሚያችን ላይ ከፍተኛ ጫና ያመጣል። በዚህ ምክንያት በአገራችን ውስጥ ደረቅ ወደቦችን እያስፋፋን እንገኛለን።

ከባህር ላይ ስናመጣ አብዛኛውን ስራ በሀገር ውስጥ ለመስራት እንዲያመቸን። ምርት እያደገ ነው፤ ኤክስፖርት እያደገ ነው ፤ ኢምፖርት እያደገ ነው። በጣም ኢምፖርታንት ነው ይሄ ነገር። ሎጀስቲክስ ላይ ባወጣነው ስትራቴጂ መሰረት የሎጀስቲክስ መሰረት ማዘመን ካልቻልን ኤክስፖርት አያድግም። ኢምፖርት አያድግም። አጠቃላይ ኢኮኖሚው አያድግም ። ምርታማነት አለ ግን ገበያ ሊወጣ አይችልም። ሎጀስቲክስን ማጠናከር ወደፊትም ያስፈልጋል። የጀመርነውን ስራ ከዛው ጋር ተያይዞ የሚታይ ነው። ደረቅ ወደብ ለግሉ ዘርፍ ከፍተናል። መንግስት ባይሰራም የግሉ ዘርፍ ገብቶ እንዲያለማ በፖሊሲ ያሻሻልንበት ዋናው ምክንያት ኢምፖርታንት ሴክተር በመሆኑ ነው። ዘንድሮ ቡና አንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ገብተናል ።ለመጀመሪያ ጊዜ ብያችኋለሁ። በአፍሪካ ትልቁን ኤክስፖርት ያረግነው እኛ ነን ። ያገኘነውም እድገት በጣም ከፍተኛ ነው።

እዚህ እድገት ውስጥ እጥረት የንግድ ስርዓቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የሎጂስቲክስ ስርዓቱ በጣም ከፍተኛ ነው። እስካሁን እኛ ቡና በጆንያ ነበር የምንልከው። በጆንያ ስንልክ ሁለት ችግር አለ። አንድ የጥራት ችግር አለ ሁለት ደግሞ ቅሸባ አለ። በየመንገዱ ይቀሸባል። ዘንድሮ 98 በመቶ ቡና ኤክስፖርት የተደረገው በኮንቴነር ነው።

በዚህ ምክንያት ብዙ አክተሮች የለፉበት ጉዳይ ቢሆንም በሎጂስቲክስ ድጋፍ ምክንያት ኤክስፖርታችን ማዘመን ተችሏል። ለአቦካዶና ለፍሩት እንደዚህ አይነት አቅም እየፈጠርን ከሄድን የራሱ የሆነ ትራክ ስለሚፈልግ ለኤክስፖርታችን ከፍተኛ ትርጉም ይኖረዋል። እሱን በርብርብ ለመስራት ጥረት ይደረጋል።

ኮይሻ ጎርጎራ መሰል ፕሮጀክቶች የተባለው ፕሮጀክቶቻችን ቃል በተገባው መሰረት በከፍተኛ ርብርብ እየተሰራ ነው። ጎርጎራ ሙሉ ግንባታውን ለማጠናቀቅና ፊኒሺንግ ላይ ለመድረስ ለፊኒሺንግ ማቴሪያል ኮንትራት የገባናቸው በሙሉ ተሰረዙብን። የጎርጎራ የፊኒሺንግ እቃ በአንዳንዱ ለምሳሌ የሲሊንግ ማቴሪያል መብራት ሊሆን ይችላል፤ ፈርኒቸር ሊሆን ይችላል። እያንዳንዱ ፕሮጀክት ከመቶ ፐርሰንት በላይ ዋጋ ጨምሯል። ይሄ ለምነን የምንሰራው ፕሮጀክት ስለሆነ በኮንትራክተሩ ላይና በፕሮጀክት ማኔጅመንቱ ላይ ከፍተኛ ችግር አስከትሏል።

ያም ሆኖ ተጨማሪ ጥረቶች በማድረግ ጊዜውን ጠብቆ እንዲጨረስ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው። ጎርጎራ ኮይሻ ሲባል ሰዎች ቀላል አድርገው ነው የሚያዩት ጎርጎራ አጠናቀን ስራ ስንጀምር በአፍሪካ ካሉት ጥቂት ሁለት ሶስት ምርጥ ዴስትኔሽኖች አንዱ ነው የሚሆነው። እጅግ በከፍተኛ ኳሊቲ ለመቶ ዓመታት እንዲቆይ ተደርጎ ከአካባቢ ጋር ተዋህዶ የተሰራ ነው። ነገር ግን ጎርጎራ የሚሰራው ቦታና መነሻ ጋር ሲሆን ጎርጎራ የምትባል ትንሽዬ ከተማ ጎኑ አለች።

ጎርጎራ የሚባለው ፕሮጀክት አሜሪካ ማለት ነው። ጎርጎራ የምትባለው ከተማ ኢትዮጵያ ማለት ነው። ይሄን ፕሮጀክት የሚመጥን የህዝብ ኑሮ አብረን ማሰብ ካልቻልን እዚህ ጋር ገነት እዚህ ጋር ረሀብ ማስተናገድ አይቻልም። መስራታችን መልካም ነው። ይሄ ፕሮጀክት ከተሰራ ትሩፋቱ የእነዛ ከተማ ወጣቶች ድሀዎች ስራ አጦች ሂወት እንዲይዝ ሌላ ድልድይ ያስፈልጋል ማለት ነው። አለበለዚያ ሰው እዚህ ሀብታም እያስተናደ እሱ ችግር እየሆነ ይቸገራል። ስራው ግን እጅግ አስደማሚና የኢትዮጵያ ቱሪዝም ብዙ ነገር ከፍ የሚያደርግ ነው። ኮይሻም እጅግ በጣም በጣም ጥሩ ፕሮጀክት ነው ወደፊት እንግዲህ እድል ሲገኝ እየሄዳችሁ ታዩታላችሁ። ከሚቀጥለው ዓመት የመጀመሪያው ኳርተር አካባቢ ጀምሮ አብዛኛዎቹ መመረቅ ይጀምራሉ። ጊዜውን ጠብቀው ይጠናቀቃሉ ለህዝባችን ቃል በገባነው መሰረት ከሰራን በኋላ ተመልሰን ገበያ የሚመጣበትን መንገድ እንሰራለን።

ከነዚህ ውጪ ያጠናናቸው ቦታዎች አሉ። በርከት ያሉ ቦታዎች ያጠናናቸው አሉ ነገሮች ሲረጋጉና ገንዘብ የምናገኝባቸው መንገድ ሲፈጠር እነሱን እያለማን ሀያ ሰላሳ አርባ ዴስትኔሽን ኢትዮጵያ ውስጥ እንፈጥርና ወደ ውጪ የወጣውን ገበያ በተለይ ሎካል ቱሪዝሙን እናስቀራለን።

ለምሳሌ እዚህ አካባቢ ሁሌ የምታነሱት ከላይብረሪ ጀምሮ ሳይንስ ሙዚየም ፓርኪንግና ዩኒቲ ፓርክ ሙሉ ለሙሉ መስከረም ስራ ላይ ይውላሉ። እስከ መስከረም የምንቆየው ክረምቱን ሳሩ አበባውን ለመትከል እንጂ ፕሮጀክቱ እንዳያችሁት እያለቀ ነው። ይሄ በሚጠናቀቅበት ሰዓት በአለም ላይ ዋሽንግተን ፓርክ፣ እንግሊዝ ለንደን ከተማቸው መሀል እንደዚህ አይነት መዳረሻ የላቸውም።

የናንተ ስለሆነ እንዳትንቁት እዚህ ቦታ ላይ ታሪክ አለ የመጀመሪያው አልፋ ቤት አለ ፤የመንግስታት ታሪክ አለ፤ ጥንታዊነት አለ፤ላንደስኬፕ አለ ፤ኔቸር አለ ፤ እርሻ አለ። ብዙ ኪሎ ሜትር ሰዎች በእግራቸው ተጉዘው ብዙ እውቀት የሚቀስሙበት ነው ። ለንደን ከሄድን አንዱን እዚህ ጋር አንዱን ማዶ ታገኛለህ እንጂ አንድላይ አታገኝም። ዋሽንግተን ከሄድ አታገኝም። ከነሱ የምንማረው ብቻ ሳይሆን ከእኛ የሚማሩት እንዳለ ማሰብ ጥሩ ነው፡፤

ይሄ ብቻ አደለም የታችኛው ቤተ መንግስት እድሳት ተጀምሯል። መሀል ላይ ያለው ቆሻሻ ቦታዎች ፈርሰዋል። ታችናው ቤተ መንግስት ውስጥ ያሉት የኢትዮጵያ ሀብቶች ታሪኮች በትክክል ግልጥ ብለው ለህዝብ ከታዩ ብዙ ችግር ይፈታሉ። ሌላው አሁን የምንጣላባቸው የወሰን ጉዳዮች ቁልጭ ብለው በካርታ የዛሬ መቶ አመት ቤተ መንግስት አለ። አያውቀውም ህዝቡ። እሱን ስናወጣ ታሪካችን ሲወጣ ቱሪዝም ብቻ አይደለም ልካችንም ከፍ ይላል።

ይሄንን ሰዎች ስለማያውቁ ሲያናንቁት ይታያሉ። በዚህ አትቸገሩ ይሄን ማወቅና ማልማት ቢችሉ ለምን ደሀ ሆነን ቀረን። ስላልቻሉ ነው እኮ ያልሆነው። እነሱ እየተቹ እኛ እየሰራን ፍሬ ስናመጣ የነሱ ልጆች ለኛ ዘብ ይቆማሉ። አሁን ያለው ሰው አልተረዳም በሚል መቸገር የለባችሁም ። የሚሰራው ፕሮጀክት ሁሉ የኢትዮጵያን ከፍታ አሁን ካለበት ወደሚቀጥለው ደረጃ የሚወስድ ነው። ይሄን አስበን አጥንተን አልመን በኢምጅነሪ ፓወር የምንሰራው ስለሆነ ብዙ የሚያሰጋ ነገር አይኖርም ፤እናንተም እያያችሁ ድጋፍ ማድረግ። ባለፈው እንደጎበኛችሁት ብዙ ግብዓት እንደሰጣችሁ አውቃለሁ። እሱን ማጠናከር ያስፈልጋል። በጊዜው ያልቃል የሚል ተስፋ አለኝ።

**(ይቀጥላል)**

# ዓለም አቀፍ

## ቤተ መንግሥታቸው በተቃዋሚዎች የተወረረው የሲሪላንካ ፕሬዚዳንት ሥልጣን ሊለቁ ነው



ተቃዋሚዎች የሲሪላንካውን ፕሬዚዳንት ቤተ መንግሥት ጥሰው መግባታቸውን ተከትሎ ፕሬዚዳንት ጎታባያ ራጃፓክሳ ሥልጣናቸውን እንደሚለቁ አስታወቁ። ተቃዋሚዎቹ በደረሱበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆነ ፕሬዚዳንቱ በቅጥር ግቢው ውስጥ አልነበሩም።

በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ተቃዋሚዎች በመዲናይቱ ኮሎምቦ አደባባይ ወጥተው ፕሬዚዳንት ራጃፓክሳ ሥልጣናቸውን እንዲያስረክቡ ጠይቀዋል። ይህም በአገሪቱ በኢኮኖሚ አስተዳደር እጦት ምክንያት ለወራት ከዘለቀው የተቃውሞ ሰልፍ በኋላ መሆኑም ተዘግቧል። ፕሬዚዳንት ራጃፓክሳ ከቀናት በኋላ ሥልጣን ይለቃሉ ተብሏል። ከእርሳቸው በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዊክሬሜሲንጌ ከሥልጣን ለመልቀቅ ተስማምተዋል።

የፓርላማው አፈ-ጉባዔ ፕሬዚዳንቱ ከሥልጣን ለመልቀቅ የወሰኑት «በሰላማዊ መንገድ የሥልጣን ርክክብ እንዲኖር ነው» ሲሉ ሕዝቡም «ሕግ እንዲያከብር» ጠይቀዋል። የፕሬዚዳንቱ ውሳኔ በከተማዋ ውስጥ ከፍተኛ ፈንጠዝያን ፈጥሯል፤ በርካቶችም ርችቶችን በመተኮስ ደስታቸውን እየገለጹ ይገኛሉ። በትናንትናው ዕለት ተቃዋሚዎች የፕሬዚዳንቱን መኖሪያ ጥሰው መግባታቸውን ተከትሎ አሜሪካ የአገሪቱን የምጣኔ ሀብት ችግር ለመፍታት አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ የሲሪላንካ አመራሮችን ጠይቃ ነበር።

በፕሬዚዳንቱ ቤተ መንግሥት ለተቃውሞ ወጥታ የነበረች ፊዮና ሲርማና የተባለች ግለሰብ «ፕሬዚዳንቱን እና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ከሥልጣን በማስወገድ ለሲሪላንካ አዲስ ዘመን የምንቀዳጅበት ጊዜ አሁን ነው» ስትል ተናግራለች። «ቀደም ብለው ከሥልጣን ባለመውረዳቸው በጣም አዝኛለሁ፤ ምክንያቱም ቀደም ብለው ቢሰናበቱ ምንም ዓይነት ውድመት ባልደረሰም ነበር» ስትል ለሮይተርስ ዜና ወኪል አስረድታለች።

በቅዳሜው ተቃውሞ በርካታ ዜጎች የቆሰሉ ሲሆን፣ የኮሎምቦ ዋና ሆስፒታል ቃል አቀባይ ለአጃንስ ፍራንስ ፕሬስ እንደተናገሩት፤ ሦስት ሰዎች በጥይት ተመትተው ሕክምና እየተደረገላቸው ነው። ሲሪላንካ በከፍተኛ የዋጋ ግሽበት እየተናጠች ሲሆን በአገሪቱ በ70 ዓመታት ውስጥ ያልታየ በተባለው አስከፊ የኢኮኖሚ ቀውስ ምግብ፣ ነዳጅ እና መድኃኒት ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት እየታገለች ነው።


የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ክምችት ተመናምኖ ያለቀ ሲሆን፣ ለግል ተሽከርካሪዎች ቤንዚን እና ናፍታ ሽያጭ ላይ እገዳ ተጥሏል። ከዚህም ጋር ተያይዞም ነዳጅ ለማግኘት ለቀናት በርካቶች ረጃጅም ሰልፎች ላይ ታይተዋል። የቅዳሜው ያልተለመደ ክስተት በሲሪላንካ ውስጥ ለወራት የተደረጉ የተቃውሞ ሰልፎች ማክተሚያ ይመስላል።

በፕሬዚዳንት ራጃፓክሳ መኖሪያ ቤት ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአገሪቱን ሰንደቅ አላማ የያዘ ሕዝብ መፈክሮችን በማሰማት አጥሩን ጥሰው ገብተዋል። ከስፍራው የወጣ ቪዲዮ ተቃዋሚዎች በግቢው ውስጥ ሲዘዋወሩ እና በፕሬዚዳንቱ የመዋኛ ገንዳ ውስጥ ሲዋኙ፣ ሌሎች ደግሞ የፕሬዚዳንቱን ዕቃዎች ሲበረብሩ እንዲሁም አንዳንዶች የቅንጦት መታጠቢያ ቤታቸውን ሲጠቀሙ ያሳያል።

ቅንጡ የሚባለው የፕሬዚዳንቱ ቤተ መንግሥት እና 22 ሚሊዮን ሕዝብ ነዋሪ ያሳለፈው የመከራ ወራት ልዩነት ተቃዋሚዎች በዝምታ ሊያልፉት አልፈለጉም። «መላው አገሪቱ እንደዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ ባለበት ወቅት ሰዎች የተሸከሙት ጫና ለማስተንፈስ ወደዚህ መጥተዋል። በዚህ ቤት ውስጥ ያለውን የቅንጦት ሁኔታ ስንመለከተው ለአገር ለመሥራት ጊዜ እንደሌላቸው ግልፅ ነው» በማለት ቻኑካ ጃያሱሪያ የተባሉ ግለሰብ ለሮይተርስ መናገራቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# የ12ተኛ ክፍል ዳግም ፈተና ዝግጅት




በሰሜኑ ክልል በነበረው ጦርነት እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች በነበረው የጸጥታ ችግር ምክንያት የ2013 ዓ.ም የ12ኛ ብሄራዊ ፈተና በአንድ ዙር መስጠት አዳጋች ሆኖ የነበር። በመሆኑ ፈተናው በሁለት ዙር እንዲሰጥ መደረጉ ይታወሳል። በሰሜኑ ክልል በጦርነት ተጎጂ ከነበሩት ክልሎች መካከል የአማራ ክልል አንዱ ሲሆን፤ የትምህርት ሚኒስቴርም የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ተማሪዎች ዳግም ፈተናውን እንዲወስዱ አቅጣጫ ማስቀመጡም አይዘነጋም ።ውሳኔውም ለአማራ ክልል ብቻ ሳይሆን ግጭት በነበረባቸው ክልሎች ፈተናው ዳግም ይሠጣል መባሉም ብዙዎች ተስፋ እንዲሰንቁ ይረዳቸዋል ተብሎም ታምኖበታል።

የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ የሕዝብ ግንኙነትና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጌታቸው ቢያዝን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት ፤ አካባቢው በወረራና በጦርነት ውስጥ በመሆኑ የክልሉ ሕዝብ ዋና ትኩረቱን አድርጎ የነበረው ራሱን ማዳንና መታገል ላይ ነበር። ተማሪዎችም የዚሁ አካል ነበሩ። ይህ ደግሞ ብዙ ጫና አሳድሯል። ስለሆነም በስነልቦና ተዘጋጅተው መፈተን አልቻሉም። ውጤቱ ያሰቡትን ያህል እንዳይሆንም ያደረገው ይህ ነው።

ትምህርት ሚኒስቴር በሰጠው እድል ለመጠቀም የችግሩን አሳሳቢነትና ውስብስብነት ለባለድርሻ አካላት የማሳወቅ ሥራ እንደተሠራ የጠቆሙት አቶ ጌታቸው፤ ሁሉም ትምህርት ቤት አውቆ እንዲሠራበትም አቅጣጫ ወርዷል። ውሳኔዎች ከተላለፈባቸው መካከልም ቅድሚያ የተሰጠው ውጤት ማሻሻልን የተመለከተው ጉዳይ ሲሆን፤ ጎን ለጎን የስነልቦና የምክር አገልግሎትም እንደሚደረግም ያብራራሉ። ከመደበኛ ተፈታኞች ጋር አብረው እንዲማሩና ሞዴል ጭምር እንዲወስዱም ውሳኔ ተላልፏል። በተጨማሪ ቅዳሜና እሁድ ሳይቀር እንዲማሩ የሚደረግበት ሁኔታ ተመቻችቷል። የማጠናከሪያ ትምህርት (ቲቶሪያል) እንዲሁም ከመደበኛው ተማሪ እኩል እንዲሳተፉም መደረጉንም ያስረዳሉ።

የመጽሐፍ እጥረት የሚያጋጥም ሲሆን፤ ተማሪዎች ዋይ ፋይ ባለባቸው ቦታዎች ላይ እየገቡ መጽሐፍትንና የተለያዩ ነገሮችን በማውረድ የሚያጠኑበትን አጋጣሚ ክፍት መደረጉን የገለጹት ኃላፊው፤ ቤተ መጽሐፍትም እንደፍላጎታቸው የሚጠቀሙበት ዕድል ተመቻችቶላቸዋል ይላሉ። በትምህርት ሥርዓቱ ከሰኔ 30 በኋላ ትምህርት ያበቃል። ሆኖም ዳግም ተፈታኞችም ሆኑ መደበኛ ተፈታኞች ሐምሌና ነሐሴ መዘናጋት እንዳይገጥማቸው ባለበት ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉም እየተሠራ መሆኑን ያመለክታሉ። ምን ምን ነገሮች መሟላት እንዳለባቸው ከአሁኑ ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆናቸውንም ይገልጻሉ።


ይህንን የፈተና ጊዜ ለማለፍ መምህራን ከምንም በላይ እየተጉ እንደሆነ በመጥቀስ፤ የዘንድሮ ውጤት ተማሪውን ብቻ ሳይሆን የክልሉን ነዋሪ ጭምር ልብ የሰበረ ነበር። በተለይ መምህሩ በእጅጉ አዝኗል። በዚህም ቁጭታቸውን ለመወጣት ከምንም በላይ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በማስተማር ላይ ናቸው። በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የተለያዩ የፈተና ወረቀቶችን( ወርክ ሽቶች) ያሠሯቸዋል። ተማሪዎች በሚመቻቸው ልክ ቀርበዋቸው ይደግፏቸዋል። ይህ ደግሞ ተማሪዎች በሚፈለገው መጠን እንዲዘጋጁ ያደርጋቸዋል።

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፤ ተማሪዎች ይህ እድል ሲሰጣቸው አንድም አዎንታዊ ሌላም አሉታዊ ነገር ይገጥማቸዋል። እንደቢሮ ግን የሚፈለገው አዎንታዊው እንዲሰፋ ነውና ለዚህ የሚያግዝ ሥራ እየተሠራ ነው። ይሁን እንጂ ተማሪዎች ካልተጠቀሙት እድሉ በራሱ ይዞ የሚመጣው ነገር የለም። ስለሆነም በሆነው ነገር ሳይቆዝሙ እድሉን መጠቀሙ ላይ ትኩረታቸውን ሊያደርጉ ይገባል። መምህራን፣ቤተሰብ ፣ የክልሉ ማኅበረሰብም ለዚህ ሥራ ውጤታማነት ተሳትፎን ማድረግ አለባቸው።

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንዳሉት ፤ እንደ ክልል የተሰጠው እድል ብዙ ነገር ይዞ ይመጣል። ኦሮሚያ ክልልም ብዙ የተጠቀመበት ነው። በክልሉ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዙ ናቸው። በሀገሪቱ ከሚፈተነው ተማሪ ውስጥ 42 በመቶውን ይይዛሉ። ስለሆነም ዳግም ተፈታኞችን በመደበኛው ልክ ለማገዝ አዳጋች ይሁን እንጂ በተቻለ መጠን አንዳንድ እድሎችን ለመስጠት ይሰራል። ቤተመጽሐፍትን እንዲጠቀሙ፣የማጠናከሪያ (ቲቶሪያል) ትምህርት ላይ እንዲሳተፉ ፣እንዲሁም ተማሪዎቹ በራሳቸው እንዲዘጋጁ የማድረግ ሥራዎችም ይሠራሉ፣ ይህ በመንግሥት የተመቻቸው እድል ለሁሉም ይሠራ ዘንድ እስከታች ተወርዶ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

ይህ እድል መቼም ያልሆነና ወደፊትም ሊፈጠር የማይችል በመሆኑ ተማሪዎች ከመዘናጋት ወጥተው ቤተ መጽሐፍትንና የማጠናከሪያ ትምህርት (ቲቶሪያል) ላይ ባለመቅረት የራሳቸውን ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸው የሚናገሩት ዶክተር ቶላ፤ ይህ ደግሞ የማስታወስና የማንበብ ክህሎታቸው በአለበት እንዲቀጥል ያደርጋቸዋል። ለውጤታማነታቸው እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አምነው ሊጠቀሙበት እንደሚገባም ያስገነዝባሉ።

# ስፖርት



## ኢትዮጵያ በዓለም ቻምፒዮና በመካከለኛ ርቀት ሜዳሊያዎች ለማስመዝገብ ተዘጋጅታለች

ብርሃን ፈይሳ

በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ጠንካራና ተፎካካሪ ቡድንን ይዘው እንደሚቀርቡ ከሚጠበቁ ሃገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ መሆኗ ይታወቃል። በዚህ ስፖርት ዝናና ክብርን የተጎናጸፈችው ኢትዮጵያ በዓለም ቻምፒዮናም ሆነ በኦሊምፒክ መድረኮች በርካታ ሜዳሊያዎችን የሰበሰበችው በረጅም ርቀት የመም እንዲሁም የጎዳና ላይ ሩጫዎች ነው። በአንጻሩ በመካከለኛ ርቀት ሩጫዎች ላይ ያላት የስኬት ታሪክ ጥቂት ነው።

በዘንድሮው የኦሪገን የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኢትዮጵያን የሚወክለው የአትሌቲክስ ብሄራዊ ቡድን ከ800 ሜትር ጀምሮ የሚሳተፍ ሲሆን፤ ይኸውም እአአ በ2013 የሩሲያዋ ሞስኮ አዘጋጅ በነበረችበት የዓለም ቻምፒዮና ባልተጠበቀ መልኩ በአትሌት መሃመድ አማን የወርቅ ሜዳሊያ ሊመዘገብ ችሏል። በወቅቱ ይህ ስኬት አስደናቂ ከመሆኑም ባለፈ ኢትዮጵያዊያን በእነዚህ ርቀቶችም ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ ተስፋ ሆኖ ነበር። ይሁንና በብዙ የተጠበቀው የዚህ ርቀት ስኬት በመሃመድም ሆነ በሌላ አትሌት ሊደገም አልቻለም። ተሳትፎውም ቢሆን እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

ሌላኛው የመካከለኛ ርቀት 1ሺ500 ሜትር ሲሆን፤ በዚህ ርቀትም በተመሳሳይ በሁለቱም ጾታ በድምሩ ሶስት ሜዳሊያዎች ብቻ ተመዝግቧል። የመጀመሪያው በወንዶች እአአ 2009 የበርሊን ቻምፒዮና በአትሌት ደረሰ መኮንን የተገኘው የብር ሜዳሊያ ነው። በሴቶችም እአአ በ2015 ቤጂንግ ላይ በገንዘቤ ዲባባ የተመዘገበው የወርቅ ሜዳሊያ እንዲሁም እአአ በ2019 የዶሃው ቻምፒዮና በጉዳፍ ጸጋይ የተገኘው የነሃስ ሜዳሊያ ነው። ከቀናት በኋላ በሚጀመረው በዘንድሮው የኦሪጎን ዓለም ቻምፒዮናም በእነዚህ ርቀቶች ውጤታማ ለመሆን እየተሰራ ነው።




**በዓለም ቻምፒዮናው ኢትዮጵያን የሚወክሉ አትሌቶች ከትናንት በስቲያ በስካይ ሳይት ሆቴል ተሸኝተዋል፣**

ኢትዮጵያ አትሌቲክስ ብሄራዊ ቡድን መካከለኛ ርቀት አሰልጣኙ ብርሃኑ መኮንን፤ በ17ኛው የኳታር ዶሃ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኢትዮጵያ በ800 ሜትር ሴቶች በአንድ አትሌት ብቻ መወከሏን ያስታውሳል። በአንጻሩ በዚህ ቻምፒዮና በዚሁ ርቀት በሴቶች ሶስት በወንዶች ደግሞ ሁለት በጥቅሉ በአምስት አትሌቶች ትካፈላለች። ይህም ትልቅ ለውጥ ነበር።

በዚሁ ርቀት ረጅም ጊዜ የሸፈነው ዝግጅትም ተጠናቆ አትሌቶቹ ከትናንት በስቲያ ወደ ውድድሩ ስፍራ ተሸኝተዋል። ዝግጅቱ የዓመቱን ሶስት ትልልቅ ውድድሮች ታሳቢ ያደረገ ሲሆን፤ እነርሱም የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና፣ ዳይመንድ ሊግ እንዲሁም የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ናቸው። በዕቅዱ መሰረትም አሁን የዝግጅቱ ሶስተኛውን ምዕራፍ ሲካሄድ ቆይቶም ተጠናቋል። ከአሁን በኋላ ያለው ጊዜም አትሌቶችን በስነልቦና የማብቃት ስራ እንደሚሆን አሰልጣኝ ብርሃኑ ተናግሯል። በዚህ ላይም ከአሰልጣኞች ባለፈ ታዋቂው የህክምናና ስነልቦና ባለሙያ ዶክተር ምህረት ደበበ ብሄራዊ ቡድኑ ባረፈበት ስፍራ ተገኝተው ጠቃሚ ስልጠና መሰጠቱን አሰልጣኙ ይገልጻል።

በ1ሺ500 ሜትር ወንዶች በዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና የወርቅ ሜዳሊያ ማጥለቅ የቻለው ወጣቱ አትሌት ሳሙኤል ተፈራ በዚህ ውድድርም ውጤታማ እንደሚሆን ከስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ግምት አግኝቷል። አትሌቱ በኦስሎ እና ዩጂን ዳይመንድ ሊጎች ከሚታወቅበት ርቀት ባለፈ መሮጡ ይታወሳል። አቅም እንዳለውም ማስመስከር ችሏል። በዚህም የዓለም ቻምፒዮና ተሳትፎው በሌላ ርቀት ይሳተፋል በሚል ቢጠበቅም በ1ሺ500 ሜትር ቡድኑን እንደሚመራ ፌዴሬሽኑ አረጋግጧል። በመሆኑም በአትሌቲክስ ትልቅ በሆነው በዚህ የውድድር መድረክ አትሌቱ የሜዳሊያ ሰንጠረዡ ውስጥ ይገባል የሚል ከፍተኛ ቅድመ ግምት ተሰጥቶታል።

የአትሌቱ አሰልጣኝ የሆነው ብርሃኑ አትሌቱ በርቀቱ ጠንካራ ከሆኑት መካከል የሚመደብ ቢሆንም ተፎካካሪዎቹ ቀላል እንዳልሆኑ ነው የሚገልጸው። ‹‹መካከለኛ ርቀቶች የመላው ዓለም ውድድሮች ናቸው›› የሚለው አሰልጣኙ ለአብነት ያህል በረጅም ርቀቶች በዋናነት ለሜዳሊያ የሚፎካከሩት ሶስቱ የምስራቅ አፍሪካ ሃገራት አትሌቶች ናቸው። በመካከለኛ ርቀት ግን ከሁሉም ዓለማት የተውጣጡ አትሌቶች ውድድሩ የዓለም ቻምፒዮና እንደመሆኑ ከፍተኛ ዝግጅት ያደርጋሉ። የአውስትራሊያ፣ ኖርዌይ፣ እንግሊዝ እና ኬንያ አትሌቶች በተለይ እንደ ስጋት የሚታዩ መሆናቸውንም አሰልጣኙ አልሸሸገም።

ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል፤ የቤት ውስጥ ቻምፒዮኑ ሳሙኤልም ከፍተኛ ተፎካካሪ እንደሚሆን ይጠበቃል። የተለያዩ ቴክኒኮችን እንዲሁም የሚያጋጥሙ እድሎችን በመጠቀም ውጤታማ ለመሆን ጥረት እንደሚያደርጉም አሰልጣኙ ተስፋቸውን ገልፀዋል።

ለሁለተኛ ጊዜ የወጣ የሐራጅ ጨረታ ማስታወቂያ

ልዩ የገንዘብና የዕገዛ ተቋም በአዋጅ ቁጥር 626/2001 እና 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከዚህ በታች የተገለፀውን ቤት ባለበት ሁኔታ በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል፡፡

| የተበዳሪው ስም | የአስያዡ ስም | ቅርንጫፍ | የቤቱ አይነት | የካርታ ቁጥር | የቦታው ስፋት | የቤቱ አድራሻ | ቀበሌ | የቤት ቁጥር | መነሻ ዋጋ | ሃራጁ የሚካሄድበት ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አቶ ሀብታሙ መንግስቴ | አቶ ሀብታሙ መንግስቴ | ቡታጅራ | ለመኖሪያ | ኬ/ከ/ማ/581/2012 | 507.38 ካ.ሜ | ደቡብ ሶዶ ኬላ ከተማ | 01 | -- | 300,000 | 05/12/14 ጠዋት 5፡00 |

በመሆኑም፣
1. ማንኛውም ተጫራች ወይም ህጋዊ ወኪል የጨረታውን መነሻ ዋጋ 1/4ኛውን በባንክ ክፍያ ማዘዣ ሲ.ፒ.ኦ በጨረታው ዕለት በማስያዝ መጫረት ይቻላል፡፡
2. ሀራጁ የሚካሄደው በልዩ የገንዘብና የዕገዛ ተቋም ቡታጅራ ቅርጫፍ ይሆናል፡፡
3. የቤቱን ሁኔታ ከጨረታው ቀን በፊት ባሉት ሶስት የስራ ቀናት በቅርንጫፉ በአካል በመገኘት በሚመደበው ሰራተኛ አማካኝነት ማየት ይቻላል፡፡
4. በጨረታው መሳተፍ የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች ጨረታ ከመካሄዱ በፊት ባሉት ቀናት ከታች በተገለፁት ስልክ ቁጥሮች መመዝገብ ይችላል፡፡
5. አሸናፊው ያሸነፈበትን ቀሪ ገንዘብ ከጨረታው ቀን በኋላ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ አጠቃሎ መክፈል ያለበት ሲሆን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ሙሉ ሂሳቡን ካልከፈለ ግን ለጨረታ መነሻ ያስያዘው ገንዘብ ለተቋሙ ገቢ ይሆናል፡፡
6. የስም ማዛወሪያና ተያያዥነት ያላቸውን ማንኛውም ክፍያን በተመለከተ ገዥ ይከፍላል፡፡
7. ተቋሙ ጨረታውን በማንኛውም ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥሮች ዋና መ/ቤት 0115577262/0115577263 ወይም አዲስ አበባ ከደሴ ሆቴል ወረድ ብሎ አድማሱ ጋራዥ ጎን በሚገኘው የተቋሙ ዋና መ/ቤት የህግና የውል አስተዳደር አገልግሎት ቢሮ በአካል ማናጋገር ይቻላል፡፡

ልዩ የገንዘብና የዕገዛ ተቋም

ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣ የሐራጅ ጨረታ ማስታወቂያ

ልዩ የገንዘብና የዕገዛ ተቋም በአዋጅ ቁጥር 626/2001 እና 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከዚህ በታች የተገለፀውን ቤት ባለበት ሁኔታ በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል፡፡

| የተበዳሪው ስም | የአስያዡ ስም | ቅርንጫፍ | የቤቱ አይነት | የካርታ ቁጥር | የቦታው ስፋት | የቤቱ አድራሻ | ቀበሌ | የቤት ቁጥር | መነሻ ዋጋ | ሃራጁ የሚካሄድበት ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ስመኝ ተፈራ | ስመኝ ተፈራ | ሰንዳፋ | የመኖሪያ ቤት | 167/2011 | 129.8 ካ.ሜ | አለልቱ ከተማ | 01 | -- | 150,000 | ነሀሴ 09/2014 ጠዋት 4፡00 |

በመሆኑም፣
1. ማንኛውም ተጫራች ወይም ህጋዊ ወኪል የጨረታውን መነሻ ዋጋ 1/4ኛውን በባንክ ክፍያ ማዘዣ ሲ.ፒ.ኦ በጨረታው ዕለት በማስያዝ መጫረት ይቻላል፡፡
2. ሀራጁ የሚካሄደው በልዩ የገንዘብና የዕገዛ ተቋም ሰንዳፋ ቅርጫፍ ይሆናል፡፡
3. የቤቱን ሁኔታ ከጨረታው ቀን በፊት ባሉት ሶስት የስራ ቀናት በቅርንጫፉ በአካል በመገኘት በሚመደበው ሰራተኛ አማካኝነት ማየት ይቻላል፡
4. በጨረታው መሳተፍ የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች ጨረታ ከመካሄዱ በፊት ባሉት ቀናት ከታች በተገለፁት ስልክ ቁጥሮች መመዝገብ ይችላል፡፡
5. አሸናፊው ያሸነፈበትን ቀሪ ገንዘብ ከጨረታው ቀን በኋላ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ አጠቃሎ መክፈል ያለበት ሲሆን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ሙሉ ሂሳቡን ካልከፈለ ግን ለጨረታ መነሻ ያስያዘው ገንዘብ ለተቋሙ ገቢ ይሆናል፡፡
6. የስም ማዛወሪያና ተያያዥነት ያላቸውን ማንኛውም ክፍያን በተመለከተ ገዥ ይከፍላል፡፡
7. ተቋሙ ጨረታውን በማንኛውም ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥሮች ዋና መ/ቤት 0115577262/0115577263 ወይም አዲስ አበባ ከደሴ ሆቴል ወረድ ብሎ አድማሱ ጋራዥ ጎን በሚገኘው የተቋሙ ዋና መ/ቤት የህግና የውል አስተዳደር አገልግሎት ቢሮ በአካል ማናጋገር ይቻላል፡፡

ልዩ የገንዘብና የዕገዛ ተቋም